# ናቲ እና ሜሪ



ከ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

# መግቢያ

## ስለ ★ናቲ ና ሜሪ★

ናቲ እና ሜሪ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ የፍቅር ዘውግ ያለው ትረካ ሲሆን እራሱን በእያንዳንዱ ሰው ቦታ እየተካ ለሚያነብ ሰው አስተማሪ ሊሆን ይችላል ብዬ ነው የጫርኩት።

ብዙ ወጣት በወሲባዊ ፅሁፎች ተስቦ በመመልከቴ በጣም ባዝንም። ተው አይጠቅምህም በደረቁ ከማለት በሚፈልገው መንገድ ጀምሬ በማማለል በፍፁም አሰልቺ እና አታካች ናቸው ብሎ ከማንበብ የተጠየፋቸውን የህይወት ውጣ ውረዶችን በተለየ መንገድ ለማቅረብ መምከር ፍላጎቴ ሲሆን ... ስኬቴ ደግም በእናንተ እርካታ ይለካል ባይ ነኝ።

★ እንደምትወዱት ተስፋ አደርጋለሁ አንብባችሁ ከወደዳችሁት ለጎደኛችሁ ማጋራት አትርሱ!!

★ ሌሎች ተመሳሳይ ፅሁፎቼን መከታተል ለምትፈልጉ

※Telegram channel --- @yefikir_tireka

**መልካም ንባብ!!**

# ★★ናቲ እና ሜሪ★★

ከ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

## ክፍል 1

ናቲ በፍፁም ፍቅር ሚባል ነገር በልቡ ገብቶ አያዉቅም እስካሁን 9 ጊዜ ጠብሷል ከ 1ዷ በስተቀር ሁሉም ወንድነቱን ይመሰክሩለታል ከዚህም የተነሳ ጓደኞቹ እንኳን ሚስቶቻቸውን አያሳዩትም በ አጭሩ ናቲ እትት ብሎ ማሳመን ካሳመነም በሃላ አልጋ ላይም ጎበዝ ስለሆነ የቀመሱት ሁሉ ሱስ ይሆንባቸዋል መደወል ሲያበዙ ደም ይሰለቸዋል የተለየ አዲስ ነገር የሚያገኝ ይመስል ደም ልላ ሲል ገና በ 22 አመቱ 9ኛዉን እንደቀመሰ ወደ 10ኛዋ እሩጫ ጀመረ።

ነገር ግን 10ኛዋ ባላሰበው መልኩ በ fb ነበር የተዋወቁት ,,,,,, ከብዙ txt በሃላ መደዋወል ጀመሩ እሷም እንደሱ ፍቅር እነደማይዛት ከ 1 ወንድ ልላ እደማታውቅ በሴክስ ህይወቷ 1 ቀንም ተደስታ ቀርቶ ምንም ስሜት ተሰምቷት እንደማታውቅ ስታወራዉ ልቡ ቀጥ አለ።

ሊያሳመምናት ደፋ ቀና ማለት ጀመረ ......

እንዳሰበውም ልቧን ለዛ ባለ ጨዋታዉ ጤፍ በሚቆላ ምላሱ ማታ package እየምሉ ከ 2-4 ሰዐታት ማወራታቸዉን ቀጠሉ ሳይገናኙ

በፍቅር ከነፉ ተገናኝተው እንዴት እንደምያስደስታት እያወራ የሚገናኙበትን ጊዜ አጥብቃ እንድትናፍቅ አደረጋት።

እሱ የ campus ተማሪ በመሆኑ ቶሎ መገናኘት አልቻሉም ነበር ሆኖም ግን እሱ የድሮ ሚስቱን ብር ተቀብሎ A.A እንደሚመጣ ነገራት የብሩ መገኛ ቢደብራትም ሊታገኘው ስለሆነ በጣም ደስ አላት በተባለው ቀን ሄደ Room ይዞ ደወለላት ስለመሸ ነገ ለመገናኘት ተቀጣጥረው ተለያይተው አደሩ።

ነጋ ደወላት ፀጉራን ተሰርታ በፎቶ ካያት በላይ ቆንጆ ሆና መጣች እቅፍ አድርጎ ሳማት ይዟት ወደ room ገባ የ3 ወር ናፍቆት ቢኖርባቸውም የመጀመርያ ገዜ መተያየታቸዉ ስለሆነ 20 ደቂቃ ተፋጠው አወሩ ከንፈሩን ስታየው በሳመኝ በሳመኝ ይል ጀመረ ልቧ ከንፈሩ በጣም ያምራል እሱም እሷን እያየ በዉበቷ በጣም ይደነቅ ጀመረ ተራርቆ መፋጠጡ ስላልተመቸው እንደወንድነቱ ጠጋ ብሎ ፀጉራን እያወራላት ይዳብሳት ጀመረ ወድያዉ ተፋጠጡ ከንፈሯን ከንፈሩ ለመጀመርያ ጊዜ ነካው

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል -2

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

.............ከንፈራን ከንፈሩ ለመመጀመሪያ ጊዜ ነካው በእጁ ፀጉሯን እየዳበሰ የስረኛውን ከንፈራን በሁለቱ ከንፈሮቹ ሲያረጥበው ፊቷ እንደፊም ይፋጅ ጀመረ ተሰምቷት የማያውቅ ስሜት ሙሉ ሰውነቷን ውርር ሲያደርጋት ታወቃት።

ሰውነቷን የሚፈጀው እሳት ከከንፈሩ ሚወጣ መስሎ ተሰማት ከንፈሯን ልታላቅቅ ብትምክርም ማስቲሽ እንደነካው ጫማ ከንፈሯ ሙጭጭ አለባት ጭራሽ እጁን ጡቷ ላይ ሲጭነዉ የእጁ ልስላሴ ሰውነቷን ሚነካበት መንገድ ልቧን ሲያቀልጥባት ተሰማት ......

ቀና አደረጋትና ልምዱን ተጠቅም ከላይ የለበሰችውን ቡኒ ቲሸርት ስያወልቅባት ድንዝዝ ባሉ አይኖቿ ብታየውም ለማስቆም የሚሆን ጉልበት ግን አጠራት ተራ በተራ ሱሪዋም የቲ ሸርቷ እጣ ደረሰው በመጀመሪያ ቀንማ አይሆንም ልቧ ቢላትም ስሜተን መቀጣጠር ግን አቃታት ከውስጥ ሱሪዋ በቀር ምንም አለበሰችም እያንዳንዱ አካሏ ላይ እጁ ይርመሰመስባታል ታቃስት ጀመረ የውስጥ ሱሪወን ዝቅ አደረገው ...

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-3

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

እያንዳንዱ አካሏ ላይ እጁ ይርመሰመስባታል ታቃስት ጀመረ የውስጥ ሱሪወን ዝቅ አደረገው እጁን በእጇ ድብን አድርጋ ያዘችው ልነክሰውም ፈልጋ እራቀባት።

እሱም ስትታገለው እጁን አስለቅቋት ቦታ ቀይሮ በእጁ ጭኖቿን ይነካት ጀመረ አንገቷ ስር የሚተነፍስባት ትንፋሽ ከምድር ከፍ ብላ የምትንሳፈፍ እንጂ በጭራሽ አልጋ ያለች አልመስል አላት።

ናቲቲቲቲቲቲዬዬዬ ትላለች ሰማይ እና ምድሩ ተገለባብጦባት ናቲም ከአንገቷ ስር ወቶ ወደ ደረቷ በስሱ እየሳማት ወርዶ ደረቷ ላይ እንደ መንታ ተራራ እዛ እና እዛ ጉች ጉች ካሉት ጡቶቿ ላይ ደረሰ ..... በሚገባ ሚያስፈልጋቸዉን ሰጣቸው ሜሪ ከሞቱት በላይ ከሚኖሩት በታች ሆና ደንዝዛ ብላለች ናቲቲ ናቲ ትለዋለች እሱ ወንድነቱ እየታገለው ሲመጣ ሱሪዉን ፈታዉ ...... ወድያዉ ያልጠበቀው ነገር ተከሰተ ሜሪ ናቲዬዬዬ ብላ ጮኸችና ..................................
......

**★"ቤቲ"★**

የናቲ 9ኛዋ gf ስትሆን በጣም በሚባል ደረጃ ትወደዋለች ግን ተለያይተዋል ። እሱ ብራን እንጂ ምንም አይነት ስሜት ለሷ ተሰምቶት አያውቅም።

በትምህርት ጉዳይ እንደሚመጣ ስለነገራት አሁን ከቤቲ ጋር ያለበትን Room ለ 3 ቀን ከፍላ ያያዘችለት እሷ ናት ለ እጁም ሚያወጣውን ብር ከሷ ነዉ የተቀበላት ከ campus የትራንስፖርት ብቻ ይዞ ነው የመጣው። እንደመጣ ማታ አከባቢ ተቀበለችው እራት በልተው የያዘችለት room አብረው አደሩ ነገር ግን በጭራሽ ምንም አላደረጉም።

ጠዋት ለትምህርት ጉዳይ ምሄድበት አለ ማታ እንገናኝ ብሏት ወደቤቷ ሸኝቷት ነበር ሜሪን እዛው Room 6:00 አከባቢ ይዟት የመጣው ............

★"ሜሪ"★

ናቲቲቲቲቲዬዬዬ ብላ ጮኸች አንገቱ እሰኪሰበር እየጉተተችው ናቲ ግራ ገባው ሁኔታዋ ..........

...,

.

ይቀጥላል

# ክፍል -4

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

ናቲቲቲቲዬዬዬ ብላ ጮኸች አንገቱ እስኪሰበር እየጉተተችው ናቲ ግራ ገባው ሁኔታዋ አሁን ትክክለኛው ሰዓት ሳይሆን አይቀርም አለ በልቡ ወድያው እጇን አስለቅቋት

በጣም በፍጥነት ከላይ የለበሰውን አወለቀዉ ከስር የተፈታውን ሱሪም አሽቀንጥሮ ጣለው በገላዋ ሙቀት ሲለበለብ የቀየው ሰውነቱ ልብሱን በማዉለቁ ነፃነቱን ያገኘ መሰለው

... .....

ቀና ብላ ስታየው አይኑ ፕፎ የጦዘ የጋንጃ ሱሰኛ ይመስል ቀይ ሆኗል ዝቅ ስትል ደም የዉስጥ ሱሪውን ገንጥሎ ሊወጣ ሚታገል ዘንዶ እንጂ የወንድ .. አልመስል አላት ህልም ህልም መሰላት .......

ሙሉ ሰውነቱ ሰውነቷን ይነካት ጀመረ ጡቷ ደረቱ ላይ ልጥፍ አድርጋው የማይጠገብ ከንፈራን ይስማት ጀመረ ...

ሁሉም ነገሩ ተወጣጥራል ቀስ ብሎ የውስጥ ሱሪዋን ጉትቶ አወለቀው

...........

የሱንም የውስጥ ሱሪ ዝቅ አደረገው ሊናደፍ እደተዘጋጀ ኮብራ ቀጥ ብሎ ......

እሷም እሱም እርቃናቸውን በጣም በጋለ ስሜት ላይ እንዳሉ 1 እግሯን ብድግ አድርጎ .........
ፊቷ ላብ በላብ ሆኗል ... ስጋ እንዳየ አንበሳ በምራቅ ተምልቷል ግራ ገባት እስከዛሬ እንዴት ይሄ ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም ብላ ከራሷ ጋር በ2 አቅጣጫ ትታገል ጀመር በ 1 ጎን እንዴት እንዴት ይሄ ስሜት ተሰማኝ በልላ በኩል ስሜቷን መቆጣጠር አቅቷታል ......

ናቲ የጋለ ሰውነቱን ከሰውነቷ ሊዶለው ተጣበቀባት ሁሉም ነገር ከቁጥጥሯ ውጭ ሆነ አነቀችው ጀርባውን በጥፍሯ ሙዥልቅ አደረገችው ገና ገላዋ ከገላው ሳይተዋወቁ ......
ብድግ ብላ እሮጣ bathroom ገባች ..........

ናቲ ግራ ገባው ሁኔታዋ ..........

ወድያው ስልኩ ይጠራ ጀመረ ....
ሲያየው ቤቲ ይላላ አነሳው
※ በር ላይ ነኝ..........
.
.
ይቀጥላል

# ክፍል -5

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

★ሜሪ★

ብድግ ብላ እሮጣ bathroom ገባች ገላዋን ስትነካው ዝልግልግ የሚል ፈሳሽ ተመለከተች በጣም ግራ ገባት ከራሷ ጋር ታወራ ጀመረ።

ከድሮው ፍቀረኛዬ ከሄኖክ ጋር ብዙ ግዜ sex ብናደርግም ምንም ተሰምቶኝ አያውቅም ከናቲ ጋር ስሳሳም ሲነካካኝ ግን ምን አይነት ህልም የሆነ ህይወት ውስጥ ቢከተኝ ነው sex ሳናደርግ መጨረስ የሚባለውን ነገር ያሳየኝ። ብላ ለራሷ ታወረለች።

መልሳ ደም አዎ መጨረስ ይሄ መሆን አለበት? ከዚ በላይ ስሜት ሊኖር አይችልም ትላለች ግራ ገብቷታል በሂወቷ በ sex እረክታ አታወቅም መጨረስ ብለው ጓደኞቿ ሲያወሩ ስለማታውቀው ትስቅ ነበረ አሁን ግን ሁሉንም ያወቀች ስለመሰላት ለጓደኞቿ ሄዳ እስክታወራ ቸኩላለች የሚገባቸው እንኳን አልመስል ብሏታል።

ናቲ ስሜት ውስጥ ሆኖ ስለመጣች ስትመለስ sex ለማድረግ አሰፍስፎ እንደሚጠብቃት አስባ ፈራች ስለጨረሰች የሷ ስሜት ቀዝቅዟል የመጀመሪያ ቀንማ አይሆንም አለች ውርደት መስሎ

ተሰማት ምክንያት መፈለግ ጀመረች ላለማድረግ።

ወድያዉ የ ናቲ ስልክ ሲጮህ ጆሮዋን እዛው ሆና ጣል አደረገች

.........

★ቤቲ★

ወድያዉ ስልኩ ጠራ....

ሲያየው ቤቲ ይላል

በር ላይ ነኝ የምትለው መስሎት ልቡ ክው እንዳለ

ናቲ: "ሄሎ ሄሎ" ,,,,ስል

ቤቲ: "ናቲዬ እንዴት ዋልክልኝ" አለችው በየዋህነቷ ተማርኮ ወደ ድሮው ፍቅራችን ከተመለሰ ብላ በማሰብ

ናቲ: "አለሁልሽ ቤቲ የሄድኩበት ቢሮ አንዴ ቦሌ ሲላቸው ሜክሲኮ አንዴ ሳሪስ ሲያዞሩኝ ብውልም አንድ ቦታ እንኳን ሳላስገባ ያመጣሁትን ወረቀት ከሰዐት ብለውኝ አሁን ምሳ እየበላው ነው " አላት ስልችት ብሎት ስራ የዋለ በሚመስል ድምጽ

ቤቲ : "አይዞህ የኔ ማር ማታ ልክ ስጨርስ ደዉልልኝ እንዳይደብርክ እመጣለው" አለችው አብራው እንደምታድር ለማሳወቅ ያህል

ናቲ :"ok እደወላለው" ብሏት ቻው ተባብለው ስልኩን ዘጋዉ

★ሜሪ★

ሜሪ እሮጣ ማምለጫዋን ታመቻች ጀመረች ወጣች

※ " ከ ቤቲ ጋር ነው እንዴ ምታድረው" ..አለችው ጮክ ብላ

※ "አዎ ነግሬሽ የለም እንዴ እንዴት እንደመጣው plus ከሷ ጋር ምንም እንደሌለን" .... አላት ቆፍጠን ብሎ አይን አይኗን እያየ

※ "እና የድሮ gf አንድ አልጋ ላይ ስታድር ትንሽ ለኔ አታስብም ምን ይሰማታል ብለክ ወይስ በ ስከልክ ስለነበር ፍቅር የጀመርነው ንቀኸኝ ነው" ብላ ማምለጫዋን በጭቅጭቅ አጧጧፈችው እቤት ልሂድ ብላ የውስጥ ልብሳን ከዛም ልብሷን ተራ በተራ አድርጋ ተነሳች አሱም ተከትሏት ሸኛት እንድታድር ቢወተውታትም አባቷ እንደሚያካብድ ነግራዉ ታክሲ አስይዟት ተለያዩ

"★ቤቲ★

መሸት ሲል ቤቲ ደወለችለት

※ ሄሎ

※ "እየመጣው ነው ውዴ ገብተሀል አይደል"

※ "አዎ room ነይ" አላት ጮክ ብሎ ሜሪ ባደረገችው ነገር

ተናዶ ስለነበር።

ቤቲ አንኳኳች ከፈተላት ገባች ትንሽ ቁጭ ካለች በሃላ ደክሞኛል ልተኛ ብላ ልብሷን አወለቀች እሱም ብርድ ልብሱን ለብሶ ፊቱን አዙሮ ተኛ።
ከላይ ጡት ማስያዣ ከስር የውስጥ ሱሪዋን አስቀርታ ብርድ ልብስ ውስጥ ገባች።

ፊት እንደነሳት ስታውቅ ትነካካው ጀመረ .... ከደረቱ ጀመረች ቀስ እያለች ቁልቁል እንብርቱን ተሻግር የሆዱን አቀበት ስታልፍ በጋለ ስሜት ፊቱን አዙሮ ...........................

.

.

.

.

.

ይቀጥላል።

## ክፍል -6

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

ፊት እንደነሳት ስታውቅ ትነካካው ጀመረ .... ከደረቱ ጀመረች ቀስ እያለች ቁልቁል እንብርቱን ተሻግራ የሆዱን አቀበት ስታልፍ በጋለ ስሜት ፊቱን አዙሮ አቁሚ ብሎ እጇን ወረወረው ።

በቃ ያ ሁሉ ስሜቱ እንደጤዛ ተኖ ጠፍቷል ልቡ ንፋስ እንዳየው ዛፍ ይወዛወዝ ጀምሯል በአካል አጠገቡ ካለችው ቤቲ ይልቅ ቀን አብራው ከዋለችው ሜሪ ጋር በሀሳብ የራሱን አለም ፈጥሮ ይዝናናል .... no no ምን እየሆንኩ ነው ስለ አንድ ሰው ይሄ ሁሉ ሰዐት ማስበው ይላል ከፈጠረው የምናብ አለም እንደመባነን እያለ....

★ቤቲ★

ትኩረት ስለነሳት ተበሳጭታለች የፈለገ ብንለያይ እንደፈለገው ብደብረው at least ሴትነቴን እንዴት አይፈልግም ሲሆን እንደወንዶቹ ዘሎ ሊወጣብኝ ሲገባው ጭራሽ አትንኪኝ እኔን ወይኔ ቤቲ ስንቱን ፊት እንዳልነሳው መጨረሻዬ ይሄ ይሁን ትላለች እራሷን በማንኳሰስ ስሜት።

ቀና ብላ አንሶላዋን ገለጥ ስታደርገው ሁለት ረዥም ፀጉር

ከአንሶላው ላይ አገኘች ክው አለች።

የለበሱትን ብርድ ልብስ በንዴት ከናቲ ላይ ግልጥ አደረገችው መሬት ላይ እቃ ቋቋ ብሎ ወደቀ እቃውን ለማየት ከአልጋው ላይ ዘላ ወረደች ባየችው ነገር ጭራሽ ጦዘባት ሜሪ ተበጥሶባት ጥላው የሄደችው ቀጭን ወርቅማ የሴት ሰዐት ነበረ ፀጉሯ እንደ ጃርት እሾክ ቀጥ ብሎ ሲቆም ታወቃት ልቧ እንደ ጠንቋይ ድቤ በፍጥነት ይመታ ጀመረ ለትምህርት ሳይሆን ሴት ፍለጋ እንደመጣ ገባት እሷን እያጃጃላት ብሯን ፍለጋ ብቻ እንደሚያገኛት አወቀች።

........ ጃሮዋን ይዛ ዋይይይይ ብላ ጮኸች

ናቲ ስትጮህ ዘሎ ተጠመጠመባት ሆቴል ያሉት ሰዎች እንዳይረበሹ በማሰብ ሰዓቱን እጇ ላይ ሲያይ ሁሉም ነገር ገባው ።

............ ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገባው ዝም አለ።

ቤቲ ብር ካልሰጠችው ወደ ግቢ እንኳን መመለሻ የትራንስፖርት የለውም።

ቤቲ ተረጋግታ ፊት ነስታው ተኛች አልነጋ ብሏት አደረች ገና ወገግ ሲል ለሁሉም አመሰግናለው ብላ ስባሪ ሳንቲም ሳትሰጠው እየተመናቀረች ጥላው ሄደች ናቲ ግራ ገባው ቁርሱን እንኳን ምን በልቶ እንደሚውል አያውቅም ቁርሱ ቢሳካለት እንኳን በምን ብር ግቢ ድረስ ይሄዳል...... ..ይቀጥላል

# ክፍል-7

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

.....ለሜሪ ደወለላት ሁሉንም ካስረዳት በሃላ የት እንደሚገናኙ ተነጋግረው ስልኩን ዘጋው ።

ሜሪ የደና ቤተሰብ ልጅ ስለሆነች ብዙም ስለ ብር ማጣት አየገባትም ሁሉም ነገር ትንሽ ነው ሚመስላት። ከብሩ ይልቅ የናቲ አስማታዊ ገላ የናቲ ትንንሽ ከንፈሮቹን ድጋሚ ልታገኛቸው ስለሆነ ተቻኩላ ከች አለች።

ልክ ስታየው አይኗ እቃ ሰርቆ እጅ ከፍንጅ እንደተያዘ ህፃን ከወድያ ወዲህ የይዋልላል ጀመረ ጉንጯ እንደበሰለ አፕል ቀልቶ ይፈጃት ጀመረ ሀሳቧ ዛሬም የትላንቱ አልጋ ላይ ሆነባት ማሰብ ማቆም ስላቃታት ግራ ገብቷታል።

"እንዴት አደርሽልኝ የኔ ፍቅር" ብሎ መሀል መንገድ ላይ ከንፈራን በስሱ ሳማት መልስ ሳትሰጠው ደረቱ ላይ ልጥፍ አለች። ተያይዘው እየተላፉ ቁርስ ሊበሉ restaurant ውስጥ ገቡ ሲታዩ 20 አመት አብረው ያሳለፉ ጥንዶች እንጂ በፍፁም ትላንት ነው የተገናኙ ብሎ ማንም ሊገምት አይችልም በስልክ ብዙ ሰዐት ማወራታቸው ሳይጠቅማቸው አልቀረም።

እዛው ይሳሳሙ ጀመረ ሜሪ በጡት ማስያዣ ታስረው የማያውቁት ቀጥ ያሉት የጡቶቿ ጫፎች በስሜት ተወጥረው በ ለበሰችው crop ቲሸርት ላይ ቁልጭ ብለው መታየታቸው አጉል ስሜት ውስጥ መግባቷን ያሳብቁባታል። ናቲ ብላ አስቆመችው ጭር ካለው restaurant ውስጥ አንድ አስተናጋጅ ወደነሱ እየመጣ መሆኑን ስታውቅ።

ምግቡን ካዘዙ በሁላ "ናቲ ስለ sex ማውራት አለብን እኔ አሁን ለማድረግ ዝግጁ አይደለሁም" ብላ ጀመረች እንደ ማራቶን ሯጭ ልምምድ የሚያስፈልገው ይመስል "በእውነት በደንብ ልረጋጋ እና Next month እኔ እራሴ ግቢ መጥቼ አብረን" አለችው ገና ምንም ሳይጠይቃት ችኩል ባለ ድምፅ። ችግር እንደሌለው አንገቱን በማነቃነቅ ከገለፀላት በሁላ ምግቡን በሉ።
ሙሉ ቀን ከ አንድ ሆቴል አንድ ሆቴል ሲሽከረከሩ ዋሉ ሲመሽ ሰፈሯ ድረስ ሸኝቷት ብሩን ሰጥታው Room ይዞ ብቻውን አደረ። በጠዋት መጥታ መኪና አሳፈረችው ወደ ግቢ ተመለሰ .......

★ከ 1 ወር በሃላ★

ሜሪ ቅዳሜ እንደምትመጣ ስለነገረችው አርብ አመሻሹ ላይ ሻውር ሲወስድ ልብሱን ሲያስተካክል አምሻሽቶ አረፍ እንዳለ ስልክ ተደወለለት

※ "ሄሎ"

※ "ሄሎ የኔ ፍቅር"

※ "ወዬ ተዘጋጀሽ ለነገ"

※ "የኔ ፍቅር አጎቴ ምቶ ለቅሶ ክፍለ አገር ካልሄድሽ ተብያለው ከምን Next week አናደርገውም" አለችው ባዘነ ድምፅ እሱ ግን ውሸቷን እሱን መሸንገያ መስሎት በንዴት

※ : "እሺ በቃ ቻው " ብሎ ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘጋው

ይንቀጠቀጥ ጀመረ ምነው ያኔውኑ በግድም ቢሆን ባደረግን ኖሮ ድሮም ለሴት ልጅ ፊት መስጠት ይሄ ነው ትርፉ ሙሉ ልብሳን አውልቃ የተውካት ቀን ነው ሴት የሆንኩት ብሎ ንዴት ማብረጃ ስልኩን አንስቶ ይደውል ጀመረ።

ፊቨን:- "ሄሎ የኔ ኩራተኛ ስደውልልክ ወሩን ሙሉ ስልክ አታነሳም ዛሬ ምን ተገኘ" አለችው ለስለስ ባለ ድምፅ

ናቲ:- "የት ነሽ" አላት ተቃጥሎ በጎረነነ ድምፁ

ፊቨን:- "office ነኝ" አለችው ውጪ የተከራዩ የግቢ ተማሪዎች በሚጠቀሙበት ቋንቋ

ናቲ:- "ዛሬ አንቺ ጋር ነው ማድረው ቴዲ የለም አይደል ? " አላት ኮራ ብሎ

ፊቨን:- " የለም የኔ ማር በጉጉት እጠብቅሀለው ና " አለችው ለማሳሳት እንደተዘጋጀ ሰይጣን ድምፃን አለስልሳ።

ስልኩን ዘግቶት ልብሱን ለባብሶ ከምሽቱ 2:30 ላይ በሯን አንኳኳ ማነው አለች አጭር ስስ ፒጃማዋን እየለበሰች በሩን ስከፍት ናቲ

............

.

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል -8

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

.......ማነው አለች አጭር ስስ ፒጃማዋን እየለበሰች በሩን ስከፍት ናቲ አይኑ ቀልቶ ፊቱ ጠቁሮ በር ላይ ቆሟል "ምን ሆነህ ነው ከሰው ተጣልተህ ነው ወይስ አምሀል" ብላ ፊቱን በስስ እጆቿ ዳበስ ዳበስ አድርጋው ተንጠራርታ ጉንጩን ሳመችው። ናቲ ምንም ሳያወራ መሬት ከተደረደሩት 3 ፍራሾች ሳሳ ያለችውን መርጦ ተቀመጠ።

ፌቨን የቴዲ ፍቅረኛው ስትሆን ቴዲ ደም ከናቲ ጋር 11,12 ,,,አብረው ተምረው ምርጥ ጎደኛምች ስለነበሩ ግቢም አንድ ላይ ምልተው አንድ ላይ ደረሳቸው። አሁን ሁለቱም 3ኛ አመት ናቸው።

ቴዲ ፌቨንን ከጠበሳት በሁላ የአልጋ(ቤርጎ) መያዣው ዋጋ አናታቸው ላይ ስለወጣ ቤት ተከራይተው ውጪ መኖር ጀመሩ። ናቲም መጀመሪያ ሰምን እዛ ቀን በቀን እየሄደ ይቅማል ፌቨን የሻሸመኔ ልጅ ስለሆነች እቃ(ጋንጃ) ታስመጣለች ከምርቃና በሁላ መስበሪያ አድርገዉት ነበር። ናቲ ብዙም ባይመቸውም ለመመሳሰል ወይ በጣም ሲናደድ ፈታ ለማለት ያጨስ ነበረ።

ሲፕፍ(ሲያጨስ) በጣም ስለሚስቅ እንጭጭ በቆሎ የመሰሉ ነጫጭ ጥርሶቹ ከጎን ስርጉድ በሚትለው የብይ ጉሬ በመሰለችው ዲምፕሉ ሲታጀቡ ምርጥ ፈገግታ ሰተውታል ቀን በቀን ይሄን አያየች ፈቬን

አጉል ስሜት ውስጥ መግባት ከጀመረች ቆይታለች።

ናቲ ምንም አልገባውም ነበር txt ታደርግለት ጀመረ እንደምትወደው። ግራ ገባው ያማታል እንዴ የጎደኛዬ ሚስት ሆና ብሎ ሳያበቃ ተነቦ ሚያልቅ ማይመስል 2 ገፅ ደብዳቤ እጁ ላይ ገባ። አስጠላዉ መሄድ ቀረ ከዛ በሃላ ዛሬ ለመጀመርያ ስለተናደደ ጋንጃ ሊፕፍ(ሊያጨስ) መምጣቱ ነው።

ቀጭኗ ፍራሽ ላይ እንደተቀመጠ 3 ትልልቅ የተጠቀለለ ይዛለት መጣች አጠገቡ ልጥፍ ብላበት ያጨሱ ጀመሩ ስሱ ውስጥ ልብሷ ሙሉ ሰውነቷን ፍንትው አድርጎ ያሳየው ጀመረ ጡቶቻ ተለቅ ተለቅ ብለው በግልፅ ከላይ ቂጭ ብለዋል ጎንበስ ሲል እግሮቿ መሀል ልብሷ ተወትፎ የእንትኗ ቅርፅ ሲያየው ደሙ ይምቅ ጀመረ ስሜቱን መቆጣጠር ተሳነው አንገቱ ስር ያለውን አንገቷን ቀና አድርጎ ከንፈሯን ይስማት ጀመረ ጡቶቿን በእጆቹ ሲያሻቸው ልፍስፍስ አለችበት ፒጃማዋን ከፍ አደረገው ከስር ምንም ስላላደረገች ከገላዋ ጋር ፊት ለ ፊት ተፋጠጠ ልብሱን በፍጥነት  ከላዩ ላይ አውልቆ እላዮ ላይ ወጣ ...........

.

.

.ይቀጥላል

# ክፍል -9

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

ልብሱን በፍጥነት ከላዩ ላይ አውልቆ እላዮ ላይ ወጣ over ስላጨሰ ሁሉም ነገር እንደ ህልም ሆኖበታል።

"ሜሪዬ " ይላታል ፊቨንን ዞሮበት እላዮ ወጥቶ እያያት "አልመጣም ብለሽኝ ከተፍ አልሽልኝ አይደል" ሲላት ፊቨን highgrade(ከባድ የጋንጃ አይነት) ያስጨሰችው አውቃ ስለነበር እንደዞረበት ስታውቅ ደስ አላት "አዎ ናቲዬ መጣውልህ" አለችው።

ናቲ ሜሪ አገኘው ብሎ አፍረተ ስጋውን በሰመመን ሲመለከተው አይሆኑ ሆኗል ቀስ አድርጎ ከገላዋ አዋሀደው ጡቷን በሁለት እጆቹ ይዞ እያሻሻት በጣም ሀይል የተቀላቀለበት ወሲብ ያደርጉ ጀመረ ፈቨን ስሜቷን መቆጣጠር አቃታት በጣም ታቃስት ጀመረ በመሀል ጀርባውን ጥብቅ አድርጋ ይዛው ፊቷ በወዝ ታጥቦ ጨረሰች እሱም ጨርሶ አጠገቧ ተጋደመ።

አንድ ሚያስታውሰው ነገር አልነበረም። ጠዋት ከከባድ እራስ ምታት ጋር ከእንቅልፋ ነቃ ዞር ሲል ፊቨን አጠገቡ ተኝታልች ደነገጠ ወይኔ አምላኬ ህልም በሆነ ብሎ ተመኘ ግን እንዳልሆነ ሲያውቅ ግራ ገባው።

ሲነሳ ባዶ እራቁቱን ነው አንባ ተናነቀው "የአብሮ አደግ ጓደኛዬን ሚስት እንዴት እንዴት እንሰሳ ብሆን ነው" ብሎ ይጮህ ጀመረ ። ፊሽን ደንግጣ ብድግ አለች "ናቲዬ ተረጋጋ" ትለዋለች "ውሻ የ አለም ምርጥ ውሻ ነሽ " አላት ልክ በግድ የደፈረችው ይመስል።ሁሉንም ነገር እሷ ላይ እያላከከ።

ስልኩን ሲያይ 17 ጊዜ ሜሪ ደዉላ ነበር ልብሱን በጣም በፍጥነት ለባብሶ ወደ ዶርም ሄደ።

ናቲ ከሚዋሽ አለም ላይ ያለውን ነገር በሙሉ ቢያጣ የሚመርጥ ልጅ ነው እንዳያጣት ቢፈራም ለ ሜሪም ግልፁን ሊነገራት ወሰነ።

ደወለ ....

ሜሪ:- ሄሎ

ናቲ:- እንዴት አደርሽ

ሜሪ:- እ/ር ይመስገን አለው ማታ ስደውል ስልክ አታነሳም

ናቲ:- ማታ.........ብሎ ሁሉንም ተራ በተራ ነገራት

ሜሪ ትንቀጠቀጥ ጀመረች ስልኩ ከ እጇ ላይ ወደቀ

ናቲ:- ሄሎ ሄሎ ይላል ....

መልስ የለም

.

.

.ይቀጥላል

# ክፍል -10

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

ናቲ:- ሄሎ ሄሎ ይላል ,,,,,,,,,

መልስ የለም ግራ ገባው በጣም ትልቅ ስህተት እንደሰራ ገባው።

እውነቱን መናገር ቢኖርበት እንኳን በአካል አጊኝቷት መሆን እንደነበረበት የገባው ከረፈደ በሀላ ነበር። ስልኩን ዘግቶ መልሶ ይደውል ጀመረ "የደወሉላቸው ደምበኛ ቴሌፎን ለጊዜው ጥሪ አይቀበልም" ከትላንቱ የባሰ ነገር እናዳይፈጠር እራሱን ለመቆጣጠር በጣም ይታገል ጀመረ አሁንም ስልኳን ይምክራል ...ዝግ ነው።

በህሊናው ብዙ ነገር ይመላለስበት ጀመረ በንዴት ግንፍል ብላ ስልኳን ዘግታ ተኳኩላ የሚገራርሙ ቀሚሶቿን ከቁም ሳጥን እያወጣች ተራ በተራ ትለብሳቸው ጀመረ ፊት ለፊት የተገተረው በቁመቷ ልክ የተሰራውን መስታወት የሚያሳያትን ለመመልከት አንዴ ወደ ሃላ ሲላት በጎን ቆማ ዳሌዋን እያየች ለሷ ቅርፅ ተብለው ከተሰሩት ቀሚሶቿ በጣም አጭሩን ከሃላ መቀመጫዋን አጉልቶ የሚያሳይላትን ጥቁር ቀሚስ መርጣ ሌሎቹን መልሳ ከተተቻቸው። መስታወቱን ጠጋ ብላ እያየች ትዘፍን ጀመረ " እንዳጠፋህ አጥፍቻለው እንደሸፈትክ ........" አይሆን ብሎ ከገባበት ሰመመን ነቃ ስልኳን ይምክር ጀመር ዝግ ነው።

.... ከዚ በላይ ቁጭ ካለ ትዝታዋ ሰይጣን ሆኖ እዳያሳብደው ፈራ ዛሬ ቅዳሜ እነደመሆኑ ለመጠጣት ሚጎርፊትን የግቢ ተማሪዎች ሲመለከት የሚጠጣው ፀበል ይመስል ሰይጣኑን ትዝታዬን ካጠፋልኝ ብሎ እየተክለፈለፈ ጎደኞቹ እንዳለቁበት ሽማግሌ ብቻውን መጠጥ ቤት ገብቶ ጥጉን ይዞ መጠጣት ጀመረ።

ስክር እስኪል ከጠጣ በሃላ የጥላሁን ዘፈን ከስካሩ አነቃው።

.

.

" ስቄ ተጫውቼ ካንቺ ሳልላፋ

መዳ ላይ ቀረሁኝ(2X) ቆሜ ሳንቀላፋ

ለኔ ጨረቃዬ ክዋክብቴ አንቺ ነሽ

ጣፋጭ ምሳ እራቴ (2x) የዘንባባ ማር ነሽ

የዘንባባ ማር ነሽ ወለላሽ የረጋ

አልደርስብሽ አልኩኛ አአአ እጄን ብዘረጋ "........

.

.

እያለ ጥላሁን ያደነቁረው ጀመር አብሮት ከዘፈነ በሃላ ምርር ብሎት ዛሬ ሁሉም እኔ ላይ ነው እንዴ የተነሳው ብሎ እየተንገዳገደ room ገብቶ ተኛ።

ሜሪ እንቅልፍ ለመተኛት ብትምክርም እንደመረቀነ ሰው አይኗ አልከደን አላት። "ትላንት ስላበሳጨሽኝ ንዴቴን ላበርድ ላጨስ ሄጄ ነው ጉድ የሆንኩት ስላላት ዛሬም ብዘጋው በንዴት ሌላ ጥፋት ቢያጠፋ እኔው ነኝ ምፀፀተው ደም እመጣለው ብዬ ባልቀር ይሄ ሁሉ ባልተፈጠረ ብላ እራሷን ትወቅስ ጀመረች።

ወድያው ስልኳን ከፍታ መደወል እንዳለበት ማሰብ ጀመረች 4:30 ሆኗል ስልኳን ከፍታ መደወል ጀመረች።
ስልኩ ይጠራል ናቲ እራሱን ስቶ ሰክሮ ብቻውን ኩርምት ብሎ ተኝቶ እንኳን የስልክ ጩኸት ታንክ በላዩ ላይ ቢያልፍ ሚነቃ አይመስልም።

ሜሪ ዛሬም የትላንቱ የተደገመ መስሏት ልታብድ ደርሳልች አሁንም ይጠራል ግን አይነሳም .......

.

. በጣም ተናዳ ከ አልጋዋ ተሰፈንጥራ ተነሳች ቀን ያየውን በውኑ ልታደርገው ........

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል - 11

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

በጣም ተናዳ ከ አልጋዋ ተስፈንጥራ ተነሳች ቀን ያየውን በውኑ ልታደርገው ይመስል እጆቿ ቁምሳጥን ውስጥ ከተደረደሩት ቀሚሶቿ መሀል ይተራመስ ጀመረ ካሉት ቀሚሶቿ ሶስቱን መርጣ መስታወቱ ፊት እርቃኗን ቆመች።

አይኖቿ ውስጥ የሚታዩት የእንባ ዘለላዎች የዋህነቷን ለሱ ያላትን ፍቅር ያሳብቁባታል ። ገና ምኑንም ሳታውቀው ይሄ ሁሉ ስሜት እየተሰማት በመሆኑ በማፍቀሯ ብትደሰትም ናቲ ተበሳጨው በሚል አጉል ምክንያት ገና ምኑንም ሳይጀምሩት መወስለት መጀመሩ ግን ራስ ምታት ሆኖባታል።

እንባ ያረገዙት አይኖቿ እርግዝናቸውን መሸከም አቃታቸው መስታወቱ ፊት ቆማ ታለቅስ ጀመረች " ናቲዬ አልከፋኝም እኔ ልሙት ችግር የለውም የኔ ጥፋት ነው እኔ ባልቀር አንተ በፍፁም ይሄን አታደርግም ትወደኛለህ አውቃለሁ አውቃለሁ...." እያለች አጠገቧ ያለ እስኪመስል ስሙን እየጠራች እንደሚወዳት እራሷን ለማሳመን ትምክር ጀመረ።

ከ አይኗ ቁልቁል ጉንጯን ተንተርሶ የሚወርደው እንባዋን እየጠራረገች አጠገቧ ያለ ይመስል " ናቲዬ እሮብ ብሞት አልቀርም

ከሶስቱ ቀሚሶቼ የቱ የሚያምርብኝ ይመስልሀል የቱን ለብሼ ልምጣ" ትለው ጀመረ አፉን አውጥቶ ይሄ ይላት ይመስል ቀሚሶቿን እየቀያየረች ካየቻችው በሁላ ጥቁር ቀለም ያለውን ቀሚስ ለብሳ ለመሄድ ብታስብም የናቲ ስልክ አለማንሳት በጣም ረበሻት ለሊቱን በሀሳብ ስታወጣ ስታወርድ አምሽታ ንጋት ላይ እንቅልፍ ወሰዳት።

ናቲ 4:00 ሲሆን እንደመርዶ ነጋሪ ጽዳት ሰራተኛዋ በሩን ስደበድብ ነበር ከ እንቅልፉም ከስካሩም የነቃው። እየተንገላጀጀ ልብሱነን ለባብሶ ስልኩን ሲመለከት ብዙ ጊዜ ሜሪ ደውላለች ደንግጦ መደወል ጀመረ። አምሽታ ስለተኛች ማታ በመጀመሪያው ጥሪ አልነቃችም መልሶ ደወለ

ሜሪ: "ሄሎ"

ናቲ: "ሄሎ ሜሪዬ ማታ እኮ ..................."

ብሎ ሀሉንም አስረዳት ምንም ባለመፈጠሩ ደስ አላት እሮብ እንደምትመጣ ነገረችው በጣም ደስ አለው ሁሉንም ነገር አመቻችቶ እንደሚጠብቃት ነገራት ቻው ተባብለው ስልኩ ተዘጋ።

#እሮብ

እሮብ ጠዋት መነሳቷን ነገረችው ከ 4 ሰዐታት ጉዞ በሁላ መነሀሪያ መግባቷን ስትነግረው ናቲ ፍልቅልቅ እያለ ተቀበላት ልክ ሲገናኙ ሰው አየኝ አላየኝ ሳይል የተራበው ከንፈራን ገምጥ አደረጋቸው እሷም በተመልካች ብዛት እንደማፈር ብትልምእንደሚኮራባት በማወቋ ግን ደስ አላት እንደለመዱት እየተላፉ ወደ ክፍላቸው ገቡ።

በጣም ይስማት ጀመረ ልቧ አካሏ ሁሉም ነገሯ የራሷ አልመስል አላት ሌላኛውን አለም እንድትናፍቅ አድርጎ ያሰቃያት ጀመረ ሙሉ ልብሷን ተራ በተራ አወለቀላት የራሱንም በፍጥነት አውልቆ ገላዋን ከገላው ለመጀመሪያ ጊዜ ሊያዋህደው በጣም ተቀራርበው ይሳሳሙ ጀመረ ሜሪ ብዙ ነገር ያምራት ጀመረ ናቲዬ ናቲዬ ትላለች አካሉን ከ አካሏ አዋህዶት የሚፈጠረውን ለማየት ጓጉታለች.............

.

.

.ይቀጥላል

## ክፍል-12

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

.........ናቲዬ ናቲዬ ትላለች አካሉን ከ አካሏ አዋህዶት የሚፈጠረውን ለማየት ጓጉታ። ገላዋን ከ ገላው ለመጀመሪያ ጊዜ አዋሀደው በጣም በጉልበት ያስገባባትም ያስወጣባትም ጀመረ አንዴ ወደላይ ሲሰቅላት አንዴ ወደታች ሲገለብጣት ሰርከስ የሚያሰራት እንጂ የባል እና የሚስት የአልጋ ላይ ጨዋታ በፍፁም አየመስልም ነበር ሜሪ የምታደርገው ነገር ውስጧን ወጥሮ ግራ ከሚያጋባት ስሜት ይገላግለኛል ብላ ብታስብም ሀሳቧን መገላባበጡ ይሰርቅባት ስለነበር ስሜቷ አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ እያለ ይዋዥቅባታል።

የሆነ ስሜት ሙሉ አካሏን ውርር አድርጎት የእርካታዋ ጫፍ ላይ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራት መልሶ ይጠፋባታል ...አሁንም እንደ አዲስ የደስታዋ ብርሀን ይታያታል ሙሉ አለሜ በራልኝ ስትል መልሶ ይጨልምባታል .... በመጨረሻ ግን እስር አትለው መፈታት ንዝረት አትለው ቅዠት ግራ ሚያጋባ አለም ወስጥ ተዘፍቃ የደሰታዋን መጨረሻ እንደናፈቀችው አጣጣመችው።

ናቲም ከብዙ ትግል በሃላ ጨረሰ ከተፈጠረ እንዲ ተደስቶ አያውቅም ወይ ጉድ ሴክስን ያለ ፍቅር ሻይን ያለ ስኳር መቅመስ አንድ ናቸው አለ በልቡ እስከዛሬ ስንቱን ያንተራሰበት ክንዱን እንደመጠየፍ ብሎ።

ሲሮጥ እንደዋለ ሰው ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ...ሜሪን ደረቱ ላይ አድርጎት ፀጉራን እየደባበሳት ያወራታል እሷ ግን በሀሳብ አብራው አልነበረችም ሁለት ልብ ሆናለች ....ደስ ብሏት የሆነችውን ለማስታወስ እየሞከረች ሳለች "እንዴት ነበረ?" የሚለው የናቲ ጥያቄ ከ ሀሳቧ አነቃት ። "በጣም አሪፍ ነበር ደስብሎኛል በጣም" በቃላት ብትለውም ከፊቷ ገፅታ ይነበብ የነበረው ደስታዋ ግን ከቃላት በላይ ሆነበት የኔ ፍቅር ብሎ እንደልጅ እንቅ አድርጎ ግንባሯን ሳማት።

ሜሪ ከናቲ ጋር ስትሆን ከማንም ጋር ተሰምቷት የማታውቀው ነፃነት ይሰማታል። ቀለል ያለ ነገሮችን በግልፅ ስለሚናገር ምንም እንኳን ብዙ ቀናትን አብረው ለማሳለፍ እድሉን ባያገኙትም አብረው ሚያሳልፉት ጥቂት ሰዓታት እንኳን ምን ያህል ደስታ እንደሚሰጣት ስታስበው ትገረማለች።

12:00 ሆነ እራት ለመብላት እዛም እዛም የወረወሯቸውን ልብሶቻቸው እየለቃቀሙ መልበሳቸውን ተያያዙት ሜሪ ትንሽ ቀበጥ በብዙ ደግም የልጅ በሀሪ ሲያይባት በጣም ደስ እንደሚለው ስለምታውቅ በስሱ መቅበጡንም ልጁነቱንም ታሳየው ጀመር። ልብሱን እየለበሰ በድንገት ካላለበስከኝ አልወጣም እምቢ እምቢ ብላ እንደልጅ ለምቦጫን ጣለችው ናቲ ሳቅ አፈነው እየቀለደች ነው ብሎ ሜሪዬ ልበሽና እንውጣ አላት " እምቢየው እምቢየው ቅድም

ልናደርግ ስንል እንደዛ አሯሩጠህ እንዳላወለክልኝ አሁን አላለብስሽም ትላለህ እምቢየው ... አልበላም ከፈለክ ብቻህን ብላ" ለምቦጯን ጣል አድርጋው አይናን ወደ ላይ እና ወደ ታች እያንከራተተችው ጥግ ላይ ኩርምት ብላ እንደዛ ስትለው ሚስቱ ብቻ ሳትሆን ልጁም መሆናን ተረዳ እቅፍ አድርጎ ሳማት ሁሉንም ልብሷንም ተራ በተራ አለበሳትና እራት ሊበሉ እቅፍ አድርጓት ወጡ።

እላዩ ላይ ጥብቅ ብላበት መንገዳቸውን ጀመሩት እሱም 2 እርምጃ በተራመደ ቁጥር ከንፈሯን ይስማታል እሷም እንቅ እንዳደረገችው ወደ ሚመገቡበት ሆቴል ደረሱ።
ምግብ ላይ ያላቸው ፍላጎት ተቃራኒ ሲሆን ናቲ በጣም አብዝቶ ሚወደው ጥሬ ስጋ ከሱ በመቀጠል ግን በ እንጀራ ጠቅለል ተደርጎ ሚጎረስ የትኛውም ምግብ ውስጡ ነው ስለ ውጪ ምግብ ፍላጎቱም እውቀቱም የለውም ሜሪ ደም በርገር እና ፒዛ በፍቅር ምትወደው ምግብ ሲሆን ከእንጀራ ነክ ደግም ፍርፍር ታዘወትራለች ምሳ በናቲ ምርጫ ስለበሉ አሁን ደም ሜሪ የምግብ እውቀቷን የምታሳይበት ሰዐት ነው። ጥግ ላይ ካሉት ወንበሮች አንዱን ሳብ አድርጎ ሜሪን ካስቀመጣት በሃላ አጠገቧ ካለው ወንበር ላይ ቁጭ አለ።

ሜሪ ሜኑውን እያየች በርገር ይሁን ፒዛ አለችው ሁለቱም ስለማይመቸው የፈለግሽውን ምረጪ አላት።

እሺ በርገር ....

ሀም ይሁን ቺዝ አስተናጋጁ ፊቱ ተገትሮ ስታፋጥጠው ተናደደ ስለማላውቀው ነገር ከማውራ ብሎ ባላዬ ፊቱን አዞረ ፀጥ አለ። ሜሪ ዝም ያለበት ምክንያት ባይገባትም 2 ቺዝ በርገር አለችው አስተናጋጁን። ምግቡም ከጥቂት ደቂቃዎች በሃላ ቀረበላቸው የቀረበውን በልተው ጨረሱ እጃቸውን ለመታጠብ እየታገሉ መታጠቢያ ክፍል ገቡ ይሳሳማሉ ጭራሽ አቅል አጣ ፍቅራቸው ምንም ቦታ መምረጥ ሚባል ነገር አልፈጠረባቸው። እንደለመዱት እየተላፋ ወደ room ተመለሱ። በተደጋጋሚ sex አደረጉ ናቲ በፍፁም መጥገብ አልቻለም ነገር ግን ሜሪ በጣም ስላመማት ማቆማቸው ግድ ሆነ።

ጠዋት ቁርሳቸውን በልተው መነሀሪያ መኪና አሳፍሯት ተመለሰ።

ሜሪ የ 1ሰዐት መንገድ ከተጓዘች በሃላ ደወለችለት ስልኩ ይጠራል አይነሳም ተኝቶ ይሆናል ብላ ዘጋቺው ......

ከ 4ሰዐታት የመኪና ጉዞ በሀላ እቤቷ ደርሰች በሰላም መግባቷን ልነግረው ብትደውልም አሁንም አያነሳም በጣም ደነገጠች ለዚ ነበር .....

.

.

.

.ይቀጥላል

# ክፍል-13

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

★ሜሪ★

....መግባቷን ልነግረው ብትደውልም አሁንም አያነሳም በጣም ደነገጠች ለዚ ነበር እንዴ የፈለገኝ ብላ ሴትነቷን ያረከሰባት መስሎ ተሰማት።

ያደረችበት ሁኔታ በረጅሙ የመኪና ጉዞዋ ላይ ተደምሮ አኳሏን ሲቀጠቀጥ እንደዋለ እስረኛ ቢያሽመደምደውም ከዚያም በላይ የሆነባት የናቲ ዝምታ ግን እሾህ ሆኖ ፍራሿ ስር የተጎዘጎዘ ይመስል ምቹ አላጋዋ ከወትሮው በተለየ አልመችሽ አላት። አንዴ በግራ ጎኗ አንዴ በቀኙ እራሷን ለማመቻቸት ብትገላበጥም አይኗ ፍጥጥ ሀሷቧም ትላንት ከነበረችበት አልጋ አልላቀቅ ብሏት መከራዋን አበዛው።

በድንገት ከአልጋዋ በስተግራ በኩል ካለው ኮመዲኖ ላይ ያስቀመጠችው ስልኳ ሲጠራ ፈጣሪ ሀጥአንን በግራ ቅዱሳኑን በቀኙ ሊያቆም የመጣ ይመስል በርግጋ ተነሳች ስልኳን እየተንደፋደፈች ልታነሳው ስትምክር ተንሸራቶ መሬት ላይ ወደቀ ኡፋፋፋ ብላ መንጫጫቱን ያላቆመውን ስልኳን ከመሬት አነሳችው።

እንደጠበቀችው ናቲ ሳይሆን አዳሯን ለማወቅ በጉጉት ስትጠባበቅ የቆየችው ጓደኛዋ ፌቨን ናት። አሪፍ ሙድ ላይ ባለመሆኗ የሷን እረጅም ጥያቄ ለመመለስ ጊዜ ሊኖራት እንደማይችል አስባ ስልኩን ሳታነሳ ዝም አለችው ጠርቶ ጠርቶ ዘጋ።

★ ናቲ★

ናቲ ከሷ እንደተለየ ልብሱን ዶርም ቀያይሮ ሻወር ለመውሰድ እየተጣደፈ በወጣበት ሰዐት አውልቆት ሎከር ውስጥ ካስቀመጠው ሱሪ ወስጥ ነበረ ስልኩ የመጀመሪያውን የሜሪ የስልክ ጥሪ ያስተናገደው።

ሻወሩን ወስዶ ሲመለስም ሌላ ልብስ ቀይሮ ከጓደኞቹ ጋር ስለ ትላንት አዳሩ የባጥ የቆጡን ሲጠይቁት ስልኩን ሳያስተውል እዛው እረስቶት ለምሳ በመውጣቱ ቀጣዩቹ የሜሪን ጥሪዎች መመለስ አልቻለም።

ስልኩን መርሳቱን ያስተዋለው ምሳቸውን ከማዘዛቸው ከጥቂት ደቂቃ በሃላ ሜሪ መግባቷን ለማረጋገጥ ለመደወል ባሰበበት ቅፅበት ነበረ። ስልኳን በቃሉ ባለማወቁ በጓደኞቹ ስልክ ለመደወል እንኳን ባለመቻሉ ቢረበሽም ምንም ማድረግ ባለመቻሉ ዶርም እስኪመለስ መታገስ ግድ ሆነበት።

"ናቲሻ ናቲሻ እየተበላ እንደማይወራ ማሚ ቆንጥጣ ስላሳደገችኝ ባውቅም breaking news እንኳን ምን የመሰለ ዜና አሳግቶ ፊውቸሪንግ በመሀል
ይገባ የለ። አዳርህን ከ google ላይ ሳልጎለጉለው አንተው ንገረን" አለ አይኑን አብረተው እንደለቀቁት ባትሪ ቦግ ያደረገው ጓደኛው። ንግግሩ ስላዝናናው ሳቅ ብሎ "እዛው በሜዳችን ይሻላል ብሩኬ በሰው ሜዳ አታሳቀኝ" አለ ለመብላት የተሰበሰቡትን የግቢ ተማሪዎች ገርመም አድርጎ እየተመለከተ።

በስመአብ ተብሎ ወዲያው ተመስገን የሚከተለው ያዘዙት ምግብ ከተፍ አለ። ሲበሉ አቀርቅሮ እንኳን ለመነሳት ሰቀቀን ነው ውሃ ለማወራረድ ተብሎ ተጠቅም የሚያውቅ የነናቲ ጀማ የለም ቢያንቃቸው በቀጣዩ ጉርሻ ያወራርዱታል እንጂ ውሀ ፍለጋ መንከራተት ለመፆም ከማሰብ አይተናነስም።

የቀረበውን ምግብ ረሀብ ያክለፈለፈው ጀለስ ግማሿን እንጀራ ቆረስ አድርጎ ወጡ ላይ ሲጥለው ተባረከ። ሲጠቀልለው ጭቃ ለመለጠፍ የተዘጋጀ ግንበኛ እንጂ በፍፁም ሊጎረስ የተዘጋጀ ምግብ አይመስልም። አምስቱም ሲያነሱት አፋቸው ውስጥ ጥለውት ሲመለሱ በእጃቸው የሚይዙትን ብዛት አድርሰው የሚመለሱበትን ፍጥነት ለተመለከተው በከባድ የኮንስተራክሽን ስራ ላይ ከተጠመደ እስካቫተር ጋር ቢያመሳስሏቸው አይደንቅም።

አስተናጋጁ አቅርቦላቸው ውሀ ይዞ ሰከመለስ ባዶ ትሪ ጠበቀው ስለሚያውቃቸው እየሳቀ ውሀውን ቀድቶላቸው ትሪውን ይዞ ተመለሰ። ጣጣቸውን ጨርሰው ውሎዋቸውን ለማሳመር ከምግብ ቤቱ ተክተልትለው ወጡ "ያንተማ ስራ ሰፋ ያለ ሰዐት ስለሚፈልግ እየተቃመ ነው ሚወራው" ብሎ ዶርም ገብቶ ለሜሪ የመደወል ሀሳቡን አስረስቶ አቅጣጫቸውን ቀይረው ውጪ ለመዋል ወደሚቀመጡባት ጠባብ ክፍል አቀኑ።

ይወራ ጀመረ "እስቲ ስለ ልጅቷ ይነገረን" አሉ አራቱም በአንድ ድምፅ ናቲም ጉትጓታው ቢበዛበት ስለ ሜሪ ማውራቱን ቀጠለ "እውነት እኔ ግን እስከዛሬ ኖርያለው በፍፁም አልኖርኩም" ብሎ ሳይጨርስ ሁሉም ሳቁ "አንተ ቆይ ሼም አይዝህም ከህንድ እስከ እብድ አጋድመህ ስታበቃ ሴት አልነካም ብለህ በመቁረቢያ ሰአት ፍቅር ያዘኝ ልትል ከሆነ ማወራትህን አቁም!!" አንዱ ሚስቱን የቀማበት ይመስል በሚያወራው ነገር ተበሳጭቶ።

"እንግዲህ ካለስማቹኝ ላቁመው እገደዳለው ግን እውነቱን ልነግራቹ ነው እየምከርኩ ያለሁት?" ብሎ ሳይጨርስ የተረዳው የሚመስል ጓደኛው " አትረብን እናዳምጠው" ብሎ ናቲ እንዲቀጥል መንገድ ከፈተለት።

★ ሜሪ★

ሜሪ ከመበሳጨቷ የተነሳ እቤት ከተቀመጠውን የውስኪ ጠርሙስ አንስታ የተቃጠለ አንጀቷን በባዶ ሆዷ የውስኪ ናዳ ታወርድበት ጀመረ

.

.

ይቀጥላል

## ክፍል -14

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

★ናቲ★

.....የተረዳው የሚመስል ጓደኛው "አትረብሹን እናዳምጠው" ብሎ ናቲ እንዲቀጥል መንገድ ከፈተለት።

....."በቃ ሳቋ ጨዋታዋ ቀልዷ አንድ እንከን ማይወጣላት ንፁህ ልጅ ታዉቃለህ ምንም ክፋት የሌለባት ንፁህ ሴት ናት OMG በጣም ወድጃታለው ስልክ 2 ሰዐት ሙሉ አውርተን ካርድ ሲዘጋ እንዴት እንደሚበሳጭ አትጠይቁኝ ወሬዋ ቢደመጥ ቢደመጥ የማይሰለች ሙዚቃ ነው የሆነብኝ።" እያለ ሲያወራ አንዱ ወሬ አቆርፋጅ ጓደኛው "Next አርገው Next አድርገው ቀጥታ ወደ ሮማንሱ ብራዘር እንደ ህንድ ፊልም 3 cd ወሬ የማዳመጥ አቅሙ የለኝም።" ብሎ የናቲን የፍቅር ወግ መሪ አዞረው ...እሺ ብሎ ወሬወን ቀጠለ " ከመነሀሪያ ተቀብያት እየተሳሳምን ወደ room ገባን ብሎ ያደረጉትን በከፊሉ ነግራቸው ።

......" ከልቡ እንደሚወዳት በስሱም በቢሆን ተረዱት። እየመሸ ሲመጣ እራታቸውን ቀማምሰው ወደ ዶርም ተመለሱ።

★ ሜሪ★

...........ሜሪ ከመበሳጨቷ የተነሳ እቤት የተቀመጠውን የውስኪ ጠርሙስ አንስታ የተቃጠለ አንጀቷን በባዶ ሆዷ የውስኪ ናዳ ታወርድበት ጀመረ። ....አንድ ሁለት እያለች ሶስተኛ ብርጭቆዋን አቅም ባጡት እጆቿ ደግፋ ታንቆረቁረው ጀመር።

ስትናደድ የምግብ ፍላጎቷ ስለሚቀንስ መጠጥ ከቀመሰች ወደስካሩ ለመሄድ ጥቂት ደቂቃዎች ይበቋታል ስሰክር ደግሞ ያ 'የዋሁ ልቧ' ውሸምነት ገብቶ ባሏ ቢመጣስ ብሎ እንደጠረጠረ ወስላታ ጎረምሳ መርበትበት ይጀምራል። እንደጠረጠረውም ስካሩ እየተቆጣጠራት ሲመጣ ክፋት ና በቀልን የተሸከመው የስካር ልቧ 80ያውን እንደተማመነ አባወራ ቆፍጠን ብሎ በሯን ይደበድባል ያኔ ገራገሩ ልቧ በመስኮት ለማምለጥ የገደዳል... የዋህነቷ በበቀለኛነት , ገራገርነቷ በክፋት ይለወጣሉ። ፍፁም ሌላ ሴት ትሆናለች ስሰክር ቀና ቀናው በፍፁም አልታይሽ ይላታል።

ሜሪ በሰከረው ኮልታፋ አንደበቷ "ሌላ ሴት ጋር ሄደህ ስትመጣ በተቀበልኩህ ... ነይልኝ ብትለኝ እንደኔ በናፍቆት ብትሰክር መስሎኝ ስንቱን አገር አቋርጬ በመጣው ..." እያለች ሲቃ በተምላበት ድምፅ ከራሷ ጋር ንትርኩን ተያያዘችው ንትርኳ እየከረረ መጣ ።

" ገላዬን ከመቅመስህ ፈላጊ እንዳጣች ሴት ስልኬን አለማንሳት አይከብድም ወይ ....... ....." ብላ ንዴቷን ያበርድላት ይመስል በእጇ የያዘችውን ብርጭቆ ወለሉ ላይ ወርውራ ሰበረችው ...... ስልኳ ሲጠራ ምንም እንዳልተፈጠረ እየተወላገደች ሄዳ አነሳችው። ፊሊምን ነበር ...

(ፊሊምን አሜሪካ የሚሰራ ጎበዝ የ software engineer ሲሆን ሜሪን የሚያውቃት ከአሜሪካ ከመምጣቱ ከጥቂት አመታት በፊት የሜሪ አጎት በሚልክለት ፎቶዎች ነበር። አጎቷ ፊሊምን ጥሩ ፀባይ እንዳለው አምላቆ እንደሚያኖራት እና እሺ ካለችው አግብቷት ሊወስዳት መፈለጉንም በተደጋጋሚ ያወራላታል እንደማይሆን አስረግጣ ብትነግረውም ፊሊምን አ.አ ከመጣ በሃላ በተደጋጋሚ እንዲገናኙ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ወደሃላ አላለም።

ሲያገኛት የሚያወራላት የምርጥ መኪናዎች ዋጋ የኢትዮጲያን ሀላቀርነት እና ከራሱ ኑሮ ስለማይዘል ሰልችቷታል አይገልፀውም። እሱም አልበቃ ብሎት ቀን በቀን በስልክ በፍቅሯ ማበዱን ባለቤቱን በምት እንዳጣ ወሻ እያላዘነ ከመግለፅ ቦዝኖ ባያውቅም ልቧን ለማግኘት አልሆንለህ ብሎታል። ዛሬም እንደተለመደው እድሉን ለመሞከር ነበር የደወለው።)

ሜሪ :- "ሄሎ ሄሎ እንዴት ኖት የተከበሩ"

ፊሌ:- "ወዬ የኔ ልዕልት እንዴት ዋልሽልኝ "

ሜሪ:- "አለውልህ ውዴዴዴ የኔ እውነተኛ አፍቃሪ የኔ ሸበላ .... " አለች ስክር ብለው በተሳሰሩት ኮልታፋ ምላሶቿ። ፊሊምን ሰምቶት የማያውቀው መልሷ በደስታ አሰከረው።

ፊሊ:- "የት ሆነሽብኝ ነው የኔ ጣፋጭ ደግም በጣም ተናፍቀሻል?" አለ መስከሯን ስላወቀ በእጁ ለማስገባት ከዛሬ የተሻለ ቀን እንደማይኖር ገምቶ።

ሜሪ:- " እቤቴ የኔ ውድ ዛሬ ወደ አሜሪካ የዘኸኝ ሁላ ብጠፋ ስሜቴ ነው።" አለ ስካር የዘረው ጭንቅሏቷ ናቲን ለመበቀል እየወተወታት

ፊሊ:- "ታዛዥ ነኝ እመቤቴ ለባበሰሽ ጠብቂኝ ሰፈር መጥቼ pick አደርግሻለው" ሲላት እሺ ብላው ስልኩ ተዘጋ ።

ፊሊምን ሀሳቧን እንዳትቀይር ሰግቶ እየተክለፈለፈ ሰፈሯ ደረሰ። ደውሎ ሰፈሯ መድረሱን ሲነግራት ውልግድግድ እያለች በሩን ከፍታ ወጣች።

,

,

ይቀጥላል

# ክፍል -15

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

.......ፊሊምን ሀሳቧን እንዳትቀይር ሰግቶ እየተክለፈለፈ ሰፈሯ ደረሰ። ደውሎ ሰፈሯ መድረሱን ሲነግራት ውልግደድግድ እያለች በሩን ከፍታ ወጣች።

ልክ ሲያያት ወባ የያዘው ይመስል ሰውነቱ ይብረከረክበት ጀመረ ደስታ ይሁን ድንጋጤ ፍቅር ይሁን ችግር ባይገባውም የሚያደርገው ሁሉ በደመነፍስ ነበረ። ምላሱ አፉን እንዳልፈታ ህፃን መንተባተቡን ቀጠለ ።

"ሜሪዬ የኔ ውድ እንዴ..ት..ት ነሽ..ልኝ" ብሎ ሊያቅፋት ሲጠጋ "excuse me ሙዚቃህን ትተህ በሩን ክፈትልኝ" ስትለው ቆሌው ተገፎ እሮጦ በሩን ከፈተላት "10Q" ብላ ስካር ባዘረው አይኗ ጠቀስ አደረገችው።

ሜሪ የፊሊምን እንዲ መሽቆጥቆጥ ስታየው እሱ ሊያስደስታት እየሞከረ ቢሆነንም ለሷ ግን ወንድ አልመስልሽ ብሏታል። እንደው እሺ ብዬ ባገባው እንኳን እኔ ነኝ እሱ ባል አሀሀ... እያለች ስታብሰለስል ፊሊ መኪናውን ሲያስነሳው ከሀሳቧ ነቃች " የት እንደምንሄድ አውቀሀል አአ" አለችው በስካር ድንዝዝ ያሉ አይኖቿን

በግድ እየገለጠች። " የት እንሂድ የት ይሻላል የፈለግሽበት መሄድ እንችላለን ምረጪ ውዴ" አለ ሽቁጥቁጡ ፊሊ " ሀሀሀ አንተ ሰውዬዬ በቃ ቦሌ 1 አሪፍ club ውሰደኝ" ጭንቅላቱን ነቅነቅ አድርጎ እሺታውን ገለፀላት ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

ሜሪ ሲደርሱ ለመውረድ ብትታገልም ድካሙም ስካሩም ተደራርቦ አልሆንልሽ አላት "ፊሊ ቆመ ታየኛለህ እንዴ አሀሀ ናና አውርደኝ እንጂ"ስትለው ደስ እያለው እቅፍ አድርጎ አወረዳት እንዳቀፋት ተያይዘው ገቡ።

ውስጥ ከገቡ በሃላ ለስለስ ባለው ሙዚቃ ታጅበው የቀረበውን ውስኪ ይልፋት ጀመረ። ሜሪ መጠጡ በድንግዝግዙ ብርሃን ላይ ተደምሮ ስካሯን ከአቅሟ በላይ አድርጎባታል። ለሱ መደካከሟ ጥሩ አጋጣሚ ስለፈጠረለት በሆነ ባልሆነው አንዴ ጡቷ ላይ አንዴ መቀመጫዋ ላይ እጁን ጣል እያደረገ መደባበሱን ተያይዞታል ኢሄም አላረካህ ቢለው እከክ እንደያዘው በግ መተሻሸቱን ቀጠለ። ሜሪ ምን እየተካሄደ እንዳለ እንኳን በቅጡ ማወቅ ተስኗታል እንደምንም ትንፋሿን ሰብስባ ስክር ባለው ደካማ ድምፃ "እንቅልፌ መጣ እንሂድ" አለችው ትንሽ ምቅ ስላለው ከወትሮው በተለየ ቆፍጠን ብሎ " እዚው አከባቢ አልጋ እንይዛለን dont worry" አላት .."የትም ይሁን መተኛት ብቻ ነው ምፈልገው " አለች በስካር መንፈስ ተነድታ ያለመንም ግርግር የተዘጋጀላት ወጥመድ ውስ ለመግባት የተዘጋጀች

ይመስል።

ሂሳቡን ከፋፍሎ አልጋ ለመያዝ ለመውጣት በመዘጋጀት ላይ ሳሉ ሜሪ ስልኳ ይጠራ ጀመረ .....ኡፋ ያቺ ፌቨን ነው ምትሆነው ብላ እየተነጫነጭ ስልኳን ከትንሿ ቢርሳዋ ውስጥ ስታወጣው "ናቲ" ይላል በርግግ አለች ስካሯ ከላዩ ላይ ግፍፍ ሲል ታወቃት የከዳት አቅሟ አንዳች ተአምር የተፈጠረ ይመስል ጥሏት ጠፋ ቀጥ ብላ ቆመች። የሙዚቃው ድምፅ እንዳይረብሻት ለመውጣት ብትፈልግም ስለተርበተበተች መትሄድበት ጠፋት ስትደነባበር ጠርቶ እንዳይዘጋ ፈርታ እዛው ክለብ ውስጥ ሆና አነሳችው።

ሜሪ:- "ሄሎ ሄሎ ናቲዬ"

አለች ፈታ ባለ ድምፅ የጠፋው ብርታቷ ተመልሶላት። ናቲ ከሷ ድምፅ ይልቅ የሚሰማው ሙዚቃው ስለነበር በጣም ደነገጠ ሰዓት ሲያይ 4:17 ይላል በዚ ሰዓት ምን እየሰራች ነው ብሎ ግራ በገባው ድምፅ።

ናቲ:- "የት ነው ያለሽው" አላት

ቤቲ:- " አይደለም እኮ ፌቨን ልደቴ ነው ብላ ጠርታን ............ " እያለች የውሸት መዘባረቁን ተያያዘችው ። ናቲ የውሸት ማውራቷን

የነቃ ይመስል።

ናቲ:-" ምንመንም መስማት አልፈልግመደ 30 ደቂቃ ሰጥቼሻለው እቤት ገብተሽ በቤት ስልክ ደውይልኝ አለበለዛ እስከመጨረሻው ቻዉ ብሎ ዘጋባት"

ሜሪ ያስቀመጠችውን ቦርሳ አንስታ እሩጫዋን ተያያዘችው ፊሊምን ምን እንደተፈጠረ ግራ ገብቶት ድንዝዝ ብሎ ቆም ነበር።

በስካር ስትንገላጀጅ የነበረች ልጅ ምን ብታገኝ ነው እንደ እንዝርት ምትሽከረከረው በሎ በመገረም ተከተላት ሮጣ ላዳ ውስጥ ገባች "ሜሪ ሜሪ እኔ አደርስሻለው" እያለ ወደ ሲጠጋ ቦታ አልሰጠችውም ንዳው ንዳው አለችው ሹፌሩን 30 ደቂቃ አልቆባት ትዳሯን ታጣ ይመስል እየተጣደፈች።

እቤት እንደደረሰች እያለከለከች ደወለችለት ናቲም ትዛዙን በማክበሯ ቢደሰትም ዉጪ በማምሸቷ ግን ቅር ተሰኝቷል።

ናቲ:- "ሄሎ"

ሜሪ: "እሄው የኔ ጌታ እቤት ነኝ"

ናቲ:- "መግባትሽ ደስ ይላል ማምሸትሽ ግን ያስቀጣሻል"

ሜሪ:- "የፈለግከውን እቀጣለው የኔ ጌታ ደም ሁለተኛ አላመሽም"

አለችው ቀን ስልክ አለማንሳቱን ጭራሽ ዘንግታው።

ናቲ:- " የሚቀጥለው ሳምንት የፈለግሽውን ቀን መርጠሽ ግዴታ ትመጫለሽ"
አላት በዚ አጋጣሚ እሷን የተራበ ልቡን ፍቅር ሊያስጎነጨው በማሰብ።

ሜሪ:- "እሺ ቅዳሜ እመጣለው" አለችው ያለማቅማማት

እንደለመዱት እረጅም የፍቅር ወሬያቸውን ካወሩ በሃላ ተሰነባብተው ስልኩ ተዘጋ።

★ቅዳሜ★

ሜሪ ቀደም ብላ በጠዋት ተነስታ ልብሷን ለባብሳ ተኳኩላ እየተጣደፈች መነሃርያ ደረሰች ከተደረደሩት መኪኖች ወደ አንዱ ዘው ብላ ጋቢና ገባች። መኪናው መንቀሳቀስ ጀመረ የሹፌሩ አነዳድ እንኳን ሰው ጤፍ የጫነ እራሱ አይመስልም ከአነዳዱ ፍጥነት በላይ እረዳቱ እየሰጠው አፉ ውስጥ የሚሰነቅረው ጫት ጉንጩ ላይ

ተቆዝሮ ተራራ አክሏል።

ሜሪ ጋቢና እንደመሆኗ የምታየው ነገር እያስፈራት መሆኑን በተደጋጋሚ ለናቲ txt ታደርግለታለች። እሱም ጭንቀት ሆኖበት እንድትወርድ ቢነግራትም ያሉበት ቦታ ጭው ያለ ምድረበዳ መሆኑን txt አድርጋለት ቀና ስትል ከፊት እየተምዘገዘገ

.

,

ይቀጥላል

# ክፍል-16

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

..........ያለችበት ቦታ ምድረበዳ መሆኑን txt አድርጋለት ቀና ስትል እየተምዘከዘከ ደርቦ ከሚመጣው መኪና ፊት ተፋጠጡ። ቦታው ዳገታማ መሆኑ በዛ ላይ የመኪኖቹ ፍጥነት ሲታከልበት ሹፌሮቹ በሽርፍራፊ ሰከንዶች ውስጥ የሚያደርጓት እያንዳንዷ እርምጃ የተሳፋሪዎቹን የህይወት አቅጣጫ መወሰኑ ግድ ሆነ።

ሹፌሩ ከፊት የተጋረጠበትን አደጋ ለማለፍ ወደግራ ፊቱን ቢያዞር ቀስ ብሎ በመሄድ እየተደረበ ያለው መኪና መፈናፈኛ እንደማይሰጠው ተመልክቶ በብረሀን ፍጥነት ሲዞር ከፊት ለፊቱ ያለው መኪና አጠገቡ ደርሷል ምንም ማድረግ ባለመቻሉ ምላስ ምታህለውን አስፓልት በግራው ትቶ ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ ቁልቁል መምዘግዘጉን መረጠ።

ሁሉም ተሳፋሪዎች በጩኸት ከመጣባቸው አደጋ ያመልጡ ይመስል ኡኡታቸውን አቀለጡት። ሜሪ ለመምት ጥቂት ሰከንዶች የቀሯት ይመስል የምትጨብጠው የምታደርገው ነገር ሁሉ ግራ ስለገባት

ከሌሎቹ ተሳፋሪዎች በተለየ መልኩ አንድ ድምፅ ሳታሰማ ደረንዝዝ እንዳለች እንባዋ በግራ እና በቀኝ ጉንጯ እርግፍ እርግፍ ይላል።

የመኪናው ጎማ ትልልቅ ድንጋይ ትልልቅ ቁጥቋጦዎችን እየረገጠ ማለፍ ግድ ሲሆንበት በከፍተኛ ሁኔታ መንገጫገጩን ጀመረ ሜሪ ወንበሩን እንቅ አድርጋ የመትረፍ ትግላን ብትቀጥልም ከአቅማ በላይ ሆኖ እያነሳ ያፈርጣት ጀመረ።

ሹፌሩ ከዚህ በላይ ቁልቁለቱን የሚጓዝ ከሆነ መኪናው ሊገለበጥ ስለሚችል ከፊለፊት ከሚታየው ባህር ዛፍ ጋር አጋጭቶ ማቆም ግድ ሆነበት። አይኑ እያየ በራሱ በኩል ማጋጨት አልሆንልህ ቢለው ሜሪ በተቀመጠችበት በቀኝ በኩል አላትም ቀጥ አደረገው።

★ናቲ★

ናቲ ያደረገችው txt ጭንቀት ለቀቀበት ውረጂ ቢላትም ምድረ በዳ መሆኑን ስትነግረው "አነስ ያለች ከተማ ላይ ስትደርሺ ውረጂ እኔ ያለሽበት ድረስ እመጣለው" ብሎ txt ካደረገላት 20 ደቂቃ ቢያልፍም ከሜሪ ምንም አይነት ምላሽ አለማግኘቱ በጣም አስጨንቆት መደወል ጀመረ "ይቅርታ የደወሉላቸው ደንበኛ........" ደጋግም ቢሞክርም ያው ሆነበት።

ጭንቀቱ ከአቅሙ በላይ ሆነበት ልቡ ትር ትር ስትልበት ደመነብሱ የሜሪን አደጋ ያሳበቀው ይመስል እንባውን መቆጣጠር አቃተው "ምነው አምላኬ ምን አደረግኩህ ይህን ያህል ጨከንክብኝ ሁሌ የምወደውን እንደ ነብሴ ምሳሳለትን ሰው ከኔ መንጠቅ አላቆም አልክ። የምወደው አባቴን ወሰድክብኝ ሁሉም ለበጎ ነው ብዬ ዝም አልኩ ትንሿን እህቴን ደግመህብኝ ሀዘኔን በጣም የከፋ አደረግከው አሁን ደም ሜሪን አይሆንም አይሆንም" እያለ እንባ ታይቶበት የማያወቅ ልጅ በእንባ ፊቱ ራሰ ጉራው የማይቻል ልጅ ልቡ ኩምሽሽ ብላ አሳዛኝ ሆኖ ቢያዩት ጓደኞቹ ግራ ገባቸው።

"የእህቴ መፅናኛ የልጆቼ እናት ብዬ ያሰብኳትን በህይወቴ ለመጀመሪያ ግዜ ፍቅርን ያየሁባትን ሚስቴን........ እባክሀረን አታድርገው እባክህን" እያለ ሜሪ የምተች ይመስል እዬዬ ማለቱን ዶርም ውስጥ ተያያዘው። ጓደኞቹ ተደናግጠው ምን እንደሆነ ባይገባቸውም ሊያረጋጉት መጣራቸውን ቀጠሉ ናቲ ቦታ ሳይሰጣቸው ስልኩን ይምክራል አይሰራም ስለሷ መረጃ ሚሰጠው ሰው ለማግት ቢያወጣ ቢያወርድ አልመጣልህ አለው። "ምን ሆነህ ነው? ምንድነው የሆንከው?" እያሉ የሚነተርኩትን ጓደኞቹን ገፈታትሮ "አንድ ሰው እናዳይከተለኝ!!" ብሎ አስጠንቅቋቸው ትላንት ለብሶ ባደረበት ቱታ ከስር ዶርም ውስጥ የሚንሳቀሱባትን ሲሊፐር አድርጎ እንደ እበድ ብቻውን እየለፈለፈ ወደ ቤተክርስተያን ሲጓዝ የሚያውቁትም የማያውቁትም ተማሪዎች ምን ሆኖ ነው? በሚመስል እይታ

ቢመለከቱትም እሱ ግን ደንታው አልነበረም ከማንም በላይ የሚያፈቅራትን ሜሪን ሰላም ያደርግለት ዘንድ ብቻ ነበር ምኞቱ።

ቤተ ክርስትያን ደረሰ ወደ በሩ ተጠግቶ ፈጣሪውን ሰላም ያደርጋት ዘንድ ለምኖ እዛው ተቀመጠ .... ተቀምጦ ስልኳን እየምከረ ሰዐታት ቢያልፉም ጠብ የሚል ነገር ጠፋ ....

በባዶ ሆዱ ኩርምት ብሎ ከተቀመጠ ከ 5 ሰዓታት ቆይታ በሃላ ግን አንድ አንድ የማያውቀው ስልክ ሲደወል መርዶ ሊነግረው ይመስል ልቡ በፍርሀት ይርድ ጀመረ እጁ እየተንቀጠቀጠ ማንሻውን ተጭኖ ....

ናቲ :- "ሄሎ ... "

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል -17

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

★ሜሪ★

.........ሹፌሩ ከዚህ በላይ ቁልቁለቱን የሚጓዝ ከሆነ መኪናው ሊገለበጥ ስለሚችል ከፊለፊት ከሚታየው ባህር ዛፍ ጋር አጋጭቶ ማቆም ግድ ሆነበት። አይኑ እያየ በራሱ በኩል ማጋጨት አልሆንልህ ቢለው ሜሪ በተቀመጠችበት በቀኝ በኩል አላትም ቀጥ አደረገው።

ሜሪ ነብሷን ለማትረፍ ያላትን ጉልበት ሁሉ አሟጣ ሹፌሩ ላይ ዘላ ለመዉጣት ጥረት ብታደርግም ከመኪናው መስታወት ጋር ከመጋጨት ለመትረፍ ግን አልቻለችም።

የተጎዱት ተሳፋሪዎች እሪታ መኪናውን በአንድ እግሩ አቁምታል። ሁሉም በየፊናው ለራሱ ጉዳት እሪታውን ያቀልጠዋል። ከተሳፈሩት 16 ሰዎች 13ቱ ላይ ቀላል 2ቱ ላይ መለስተኛ የሚባል ጉዳት ሲደርስ አንድ ተሳፋሪ ግን የተሰበረ መስተዋት ጉሮሮው ስር ተሰንቅሮበት በሞት እና በሂወት መሀል እየዋለለ የሰውን እርዳታ

ይማፀናል።

ሜሪ ከመኪናው ከፊት መስታወት ጋር በደረሰባት ግጭት የተነሳ ከግንባሯ የሚፈሰው ደም ሙሉ ፊቷን ከመሸፈኑም በላይ አንዳች እንቅስቃሴ አለማድረጓ እንደበረኛ ተወርውራ የወደቀችበት ሹፌር መምቷን ያለ አንዳች ጥርጣሬ እንዲያምን ቢያደርገውም ተስፋ ቆርጦ ሊተዋት በፍፁም ስላልፈለገ የራሱን ቀላል ጉዳት ወደ ጎን ትቶ የሚፈሰው ደማን ሳይፀየፍ እንደ እህቱ እቅፍ አድርጎ ከመኪናው አወጣት።

የሰፈሩ ሰዎች ከየጎጆዋቸው ተሯሩጠው ወተው የተቻላቸውን ሁሉ ለተጎዱት ሰዎች ለማድረግ በመረባረብ ላይ ሳሉ ሜሪ በደም ተለውሳ በሹፌሩ እቅፍ ሆና ስትወጣ አንድ እናት የእናት አንጀታቸው አልችል ቢላቸው ተጠግተው ጣታቸውን አንገቷ ስር አድርገው ትንፋሿ አለመቋረጡን እንዳረጋገጡ ሜሪን ወደሳቸው ቤት እንዲወስዳት እሳቸውም የተቻላቸውን ሁሉ እንሚያደርጉላት በተማፅኖ ሹፌሩን ጠየቁት። የእናትነት ልመናቸው ቢከብደው የደረሰበትን ቀላል ጉዳት ተቋቁም ከቤታቸው አደረሳት።

እማማም እንደ ዶ/ር ደሟን ጠራርገው ግንባራ ላይ ያለችውን ቁስል በስስ ነጠላ አሸገውላት በደም የተጨማለቀ ልብሷን አውልቀው ከቤት ያለውን በአረንጓዴ መደብ ላይ አበባ ጣል ጣል ያለበትን

የልጃቸውን ሽንሽን ቀሚስ ሲያለብሷት ሁላ ሜሪ አልነቃችም ነበር።

ተኳኩላ ተተኩሳ የነበረው ፀጉሯ ለእማማ ቦታ አልነበረውም "አስካሉ ለጋ ቂቤ አምጭልኝ" አሉ ልጃቸውን የሜሪን ፀጉር ሶስት ቦታ እየጎነጎኑ። የመጣላቸውን ቅቤ በደንብ ውስጡን ቀብተዋት የገጠር ሙሽራ አስመስለው ጋደም አድርገዋት ወጡ።

ከሰዐታት ቆይታ በሃላ ሜሪ ብርግግ ብላ ተነስታ "ናቲዬ አልቀረሁም አልቀረሁም እየመጣው ነው" እያለች እዬዬዋን ለቀቀችው የተፈጠረውን ሁሉ ካስረዷት በሃላ እሷም ሁሉን ነግራቸው ለናቲ አረጋግተው እንዲጠሩት ካሉት ሰዎች ለአንዱ ቁጥሩን ሰጡት።

★ናቲ★

....

.ናቲ :- "ሄ..ሎ..ሎ" አለ እንደሰረቀ ሰው እየተርበተበተ

ሰውየው :- "ሄሎ ወንድሜ የሜሮን ፍቅረኛ ነህ አይደል?"

ናቲ:- "አዎ አላወኩህም ግን ወንድሜ ማን ልበል" አለ ድምፁ እርጅና እንደደቆሰው ሽማግሌ እየተንቀጠቀጠበት .....

ሰውየው ቀለል አድረጎ ሁሉንም አንድ በአንድ ካስረዳው በሃላ ቶሎ እንዲመጣ አስጠንቅቆት አድራሻውን ነገሮ ተሰናብቶ ስልኩን ዘጋው።

ናቲ ኩርምት ብሎ ከተቀመጠበት ተነስቶ ምላስ የምታህል ሲሊፐሩን እያንጣጣ ትንፋሽ እስኪያጥረው እየሮጠ ከ ቤተክርስትያን ግቢ ተፈትልኮ ወጣ። እንደዛው ኩትት እንዳለ መነሃሪያ ተሳፍሮ ወደ ተባለበት ጉዞውን ቀጠለ።

★ሜሪ★

ሜሪ ስልኳ ይጠራ ጀመረ ቁጡው ቆፍጣናው አባቷ ነበሩ። አ.አ እንዳልሆነች ለወንድ ብላ ሌላ አገር መሄዷን ሰምተው ክፉኛ ተናደዋል ......

ሜሪ:- "ሄሎ አባዬ"

አባቷ:- "ያባባሽና የት ነው ያለሽው" አሉ በልጃቸው ስራ እጅጉን ተናደው...

ሜሪ:- "እ..እ..

.

ይቀጥላል

# ክፍል -18

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

ሜሪ:- "ሄሎ አባዬ"

አባቷ:- "ያባባሽና የት ነው ያለሽው" አሉ በልጃቸው ስራ እጅጉን ተናደው .......

ሜሪ:- "እ...እ ምን ማለት ነው" አለች ቆምጨጭ ብላ በሱ ለማላከክ ማለት ያለባትን በሃሳባ እያውጠነጠነች።

አባቷ:- " ከ አ.አ ውጪ መሆንሽን አጎትሽ ነግሮኛል መዋሸቱን ተይና አሁን የት እንዳለሽ ንገሪኝ" አሉ አባቷ የሰሙት ወሬ ውሸት ሆኖ እንዳይዋረዱ ፈራ ተባ እያሉ ....

ሜሪ:- "አዎ አ.አ አይደለሁም!! አክስቴ ጋር ደብረዘይት ሄጃለው አጎቴን ደም ገና ለገና ለጓደኛዬ እድራታለው ብለህ ወሬ አታመላልስ በልልኝ። አባዬ በአንተ ግን በጣም አዝኛለው የሰው ወሬ ሰምተክ እኔን ያባባሽ ትለኛለህ አሁንም የማታምነኝ ከሆነ አክስቴን አዋራት ? ልስጣት? " አለችው በድፍረት ስጫት እንደማይላት ገምታ

አባት:- " እረ ተይ ይቅር ልጄ ... ይቅርታ የሰው ወሬ ሰምቼ ረበሽኩሽ .....ነገ በጊዜ ተመለሽ አክስትሽንም ሰላም በይልኝ " አሉ ባደረጉት ነገር እንደማር ብለው.....

ሜሪ እንዳኮረፈ ሰው ምንም ሳትናገር ስለኩን ዘጋችው እና ከገባችበት ወጥመድ በማምለጧ ተንፈስ አለች።

★ናቲ★

እንደዛው ኩትት ብሎ መነሀርያ ተሳፍሮ ወደተባለበት ቦታ ጉዞውን ቀጠለ። የተባለበት ቦታ ሲደርስ ወርዶ በተደወለለት ስልክ መድረሱን ሲያሳውቃቸው ከጥቂት ደቂቃ ቆይታ በሃላ ከስር ጥብቅ ያለች ቁምጣ ከላይ ቀይ በነጭ ሸንተረር ባለ ኮሌታ ቲሸርት የለበሰ ጎረምሳ ደምግባቷ እህቱን ከምመስል ኮረዳ ጋር ወደ እሱ ሲመጡ ተመለከተ ።

"አንተ ነህ አይደል የደወልከው" አለ ጎረምሳው የገጠር ለዛ በተላበሰው አንደበቱ "አዎ እናንተ ቤት ነው ያለችው ሜሪ" አለ ናቲ ቀበል አድርጎት ስላለችበት ሁኔታ ትንሽ ቢያወራልኝ ብሎ። "ዋ ሜሪ ነው ስማ አዎ ከኛ ዘንዳ ነው ያለችው .........." የተፈጠረውን ሁሉ አንድ በአንድ እያወጋለት ከ አሰፓልቱ ቁልቁል ወዳለችው ወደ እማማ ጎጆ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

★ሜሪ★

እማማ አንዳች ጥቁር እንግዳ ይመጣባቸው ይመስል በስተ ምስራቅ ባለችው የጎጆዋቸው መስኮት አንገታቸውን አውጥተው ማዶ ማዶ ሲመለከቱ ናቲ ከልጆቻቸው ጋር እያወጋ ወደ እሳቸው ቤት ሲገሰግስ ተመለከቱት። መደበቅ አልሆንሎት ቢላቸው አስሬ "መጣ አልደረሰም እንዴ እማማ!" እያለች ፊት ለፊት ካለችው የጠፍር አልጋ ላይ ተጋድማ ንዝንዝ ስታደርጋቸው ለቆየችው ሜሪ " ልጄ እየመጡ ነው የጋሽ ቦጋለን የእርሻ መሬት አልዋል" አሉ ሰፈር ውስጥ ለብዙ አመታት እንደቆየ ሰው ሰፈሩን ታውቀው ይመስል።

ሜሪ ነብሷ ተጨነቀች የእውነትም ናቲ ናፍቋት ነበረ የበለጠ ግን መቅረቡን ስታውቅ ናፍቆቱ ቢብስባት መተኛት አልሆንልሽ አላት " እማማ እኔም አየዋለው አየዋለው እንደርሶ በመስኮት" ብላ እንዳትነሳ ያስጠነቀቋትን የእማማ ምክር ወደ ጎን ትታ ለመነሳት ከጠፍሯ አልጋ ላይ ስትፍጨረጨር እማማ ከመስኮቱ መለስ ብለዉ " የከተማ ሰው እንደው ትግስት የላቹም አይሆንም መንቀሳስ የለበሽም ሲደርስ ታይዋለሽ" ብለው ተቆጥተው መለሷት።

የእማማ በር ላይ ሲደርሱ ናቲ "ቤቶች" አለ ገጠር ተወልዶ እንዳደገ ጎረምሳ የደንቡን ለማክበር እማማ "ግባ ልጄ" ሲሉት እላያቸው ላይ

ጥምጥም ሲል ያላሰቡት ነገር ስለነበር

※ " ምነው ልጄ ምን ሆነክ ነው" ....... አሉ በእናት አንደበታቸው

※"እርሶ ባይኖሩ ......." ብሎ በቃላት ወለታቸውን መናገር ቢያቅተው እንባው ዱብ ዱብ አለ

※ "እረ ምንም አይደል ልጄ ደም ወንድ ልጅ አያለቅስም " ብለው እንባውን አበስ አበስ አድርገው እሱ ለሷ እሷ ለሱ ያላቸውን ስሜት ሲረዱ ቱቱቱ ፈጣሪ ከአይን ያውጣችሁ አሉ በልባቸው። "በል ወደ ውስጥ ዝለቅ ልጅቷ ዘላ ሳትወጣልህ " ሲሉት ሳቅ ብሎ ተንደርድሮ ገባ።

ሲያያት የለበሰችው ልብስ የፀጉሯ አሰራር በላዬ ላይ የተቀባችው ቅቤ ቢያስቅም ለሱ ግን አንዳች ልዩነት አልነበረውም ከዘናጯ ሜሪ ጋር እሷም በቱታ በሲሊፐር መንከራተቱ ሲደመርበት አመድ ቢመስልም ለሷ ምኑም አልተቀየረም። እንቅ አድርጓ አቀፋት ትንፋሽ እስኪያጥራት ድረስ እሷም ጉንጩ ላይ ተጣብቃ አልላቀቅ ቢሉ እማማ ጠጋ ብለው "እህህህ " አሉ ሰው እንዳለ ለማሳወቅ በሚመስል ቅላፄ። እንደማፈር ብለው ሲላቀቁ "ልጄ ከመንገድም አይደል የመጣኸው እህል ቅመስ ሌላው በሃላ ይደርሳል" ብለው ጋሻ የሚያህል ትልቅ ቂጣ እርጎ ከያዘ ኩባያ ጋር አቀረቡለት።

አበላሉ ባዶ ሆዱን መዋሉን ቢያሳብቅላት ምን ያህል እንደሚያፈቅራት በጥቂቱም ቢሆን አመነች።

እስኪመሽ አጠገቧ ሆኖ ሲጫወቱ ሲያወሩ ወለው ሲመሻሽ እማማ ጎጆዋ ውስጥ እንደማምቂያም እንደ ብረሀንም የሚያገለግለውን ካንፋዬር መሳይ እሳታቸውን ጎጆዋ መሀል ላይ አያያዟት። ሁሉም የቤቱ ሰዎች ዙሪያውን ካለው መደብ ላይ ተደርድረው ቆሎዋቸውን እየቆረጠሙ ጠላቸውን እየላፉ የራሳቸውን ጨዋታ ያወጋሉ። ናቲ ና ሜሪ እንደ ክብር እንግዳ እራቅ ብለው ቁርበት ተነጥፎላቸው ተቃቅፈው ተቀምጠዋል። ናቲ ቀስ እያለ በጆሮዋ ሚያንቆረርላት ወሬ ብረሀኑ እየደበዘዘ በመጣው የእማማ ካንፋየር ላይ ተደምሮ አጉል ስሜት ይሰማት ጀመረ።

የበርሀኑን መደብዘዙን ተከትሎ ሁሉም ጥግ ጥጉን እያመቻቸ መተኛት መጀመሩ ሜሪ እያየለባት ለመጣው ስሜቷ መፍትሄ ያገኘች ያህል ደስ ብሏት ከአንገቱ ስር ቱር ብላ ወጥታ ከንፈሩን ትስመው ጀመረ ናቲ የእሳቱ ፍም እንደማሳያቸው ቢያውቅም የእማማ መገላበጥ እንቅልፍ እንዳልወሰዳቸው ያሰታውቃል ቢወስዳቸው እንኳን የሜሪ የሲቃ ድምፅ እንኳን አንድ ቤት ላለ ሰው ለጎረቤት አስጊ መሆኑን ስለሚያውቅ እረፊ አምሽ የለ ብሎ ሊያስቆማት ቢምክርም................ይቀጥላል

# ክፍል -19

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

..............ቢምክርም እንደ ትንሽ ልጅ አንድ ነገር ካማራት ካላገኘች መተው የማይሆንላት ሜሪ ቢያማትም የሱን ደስታ ለማየት ፈልጋ " አንዴ ብቻ የኔ ፍቅር እውነት አንድ ድምፅ አላወጣም ደም አምኝ የለ? ያመመው ሰው እምቢ ይባላል?" አለችው ጆሮው ስር ገብታ ስልል ባለ ስሜት በሚቀሰቅስ ዝቅተኛ ድምፅ እሺታውን ለማግኘት መቅለስለስ አክላበት።

ከሷ በላይ እሱ ደሙ ምቆ አካሉ በሷ ገላ እረሀብ ቢንገበገብበትም ከስሜቱ በላይ የፈሰሳት ደም ምን ያህል አቅሟን እንዳሳጣት ስለሚያውቅ በልጅነት ሽንገላዋ ተታሎ ቢያደርግ ነገ አጉል እንደምትሆን በማሰብ " እኔ ሳደርግ ዝም ማለት አልችልም በሀላ አጉል ነው ምንሆው ኡኡ ብዬ እዚ ሁሉ ሰው መሃል" አላት በስላቅ ጉትጎታዋን ብታቆም ብሎ።

"አኮርፋለው እምቢ እምቢ" አለች እንደለመደችው የስረኛ ከንፈራን አሳብጣ ከእቅፋ እየሸሸች። " ነይ ተመለሽ ጌታን ጮኬ ተጣርቼ ነው እማማ የምለው ከዛ የምትይውን እነግራቸዋለው" አላት ከእቅፋ ወጥታ ፊቷን ማዞሯ የውሸት መሆኑን ቢያውቅም።

"በቃ ሁሌ አንተ ያልከው ብቻ ነው የሚሆነው" ብላ እየተነጫነጨች የእማማ ስም መነሳቱን የፈራች አስመስላ ስሩ ውሸቅ አለች ተመለሳ። የሚያደረገው ሁሉ ለሷ አስቦ እንደሆነ በደንብ ቢገባትም እሷ ግን ለሱ ብላ ምንም አለማደረጓ አንገብግቧታል።

የባጥ የቆጡን እሹሹ እያሉ በቀስታ ሲያወረ እኩለ ለሊት ቢያልፍም አንዳቸውም የመተኛት ሀሳብ አይታይባቸውም። "በቃ እንተኛ ነገ ተጓዥ ነን" ቢላትም እንቢ ብላ ክችች አለች ከመተኛቱ በላይ እቅፉ ስር ሆና የሱን ጣፋጭ ንግግር ማዳመጡ ስቧት። ናቲም እምቢታዋን ተቀብሎ ስለወደፊት ሂወታቸው ምን እንደሚመስል ልስልስ ብሎ በተመጠነ ደምፅ ስዕል በሚከስቱ ቃላት ፀጉሯን በስሱ እየዳበሰ እያወራላት ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዳት። እዛው ደረቱ ላይ እቅፍ አድርጓት የቀን ድካሙን ለማስታገስ እሱም ጋደም አለ።

"ጠዋት"

ሜሪ እዛው ደረቱ ላይ እንደተጣቀች እማማ ላምቹን ለማለብ በሩን ሲከፍቱ የበሩ ጩኸት ናቲን ከእንቅልፉ አነቃው። ከጥቂት ቆይታ በሃላ በእንቅልፍ ድርድር የማታውቀው ሜሪ አይናን እያሻሸች የገጠር ኮረዳ ከመሰለው አለባበሷ ጋር ነቃች።

ለሁለቱም የገጠር ኑሮ አዲስ እንደመሆኑ ለስራ ያላቸው ትጋት ትህትናቸው የዋህነታቸው ሲታከልበት በወሬ የሚያውቋትን የጥንቷን ኢትዬጲያ ቁልጭ አድርጎ ቢያሳያቸው ከተሜነት ምን መሰልጠን ነው መሰይጠን ነው እንጂ ያሉ ይመስል ነበረ ሁኔታቸው።

ከተኙበት ቁርበት ላይ ሳይነሱ እማማ ትኩስ ወተት ጀግ በሚያስንቅ ኩባያ እና ጥይት አይበሳውም ብለው ቢደራደሩ ሊረቱ ከሚችሉበት ትልልቅ ሽልጦ ጋር አቀረቡላቸው።

ቁርሳቸውን ጥርቅም አድርገው በልተው ለአይን ምትማርከውን የገጠር መንደር የተቻላቸውን ያህል ዞር ዞር ብለው ከቃኙ በሃላ በተፈጥሮዋ በህዝቡ የዋህነት ተደንቀው ለመዝናናት የመጡ ያህል ትልቅ የመንፈስ እርካታን ሸምተው የደጓን እናት እጅ ስመው ስለውለታቸው ምስጋናቸውን ቸረዋቸው የገጠሯን መንገድ ለቀው ወደ አ.አ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

አ.አ እንደደረሱ በእማማ ህክምና ብታገግምም ሆስፒታል መታየቱ እንደሚሻል ስላሰበ ይዟት ሄደ። ዶክተሩ መልካም ጤነንነት ላይ መሆኗን ነገር ግን ፈሳሽ ነገር እንድትወስድ እና በደንም ማረፍ እንደሚኖርባት አስረግጦ ነግሯቸው ወጡ።

ሰፈሯ ድረስ ካደረሳት በሃላ ሁለቱም ትንሽ አብረው ለመቆየት ቢከጅሉም ናቲ የሚጠብቀውን ጉዞ በማሰብ በጊዜ ለመለያየት ተገደዱ።

ከሰአታት ቆይታ በሃላ ሜሪ አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ የክፍሏ በር ገርበብ እንዳለ ከምትወደው ባሏ ጋር ስልክ እያወራች ሳለ አባቷ ትላንት ላስቀየማት ልጁ ማካካሻ ይሆን ዘንድ የገዛላትን ስጦታ ኮቴውን አጥፍቶ ሳታስበው ሰርፕራይዝ ሊያደርጋት ሹክክ ብሎ ሊገባ ሲል ሜሪ ምታወራው ወሬ እንደተቆረጠ እንጭት አድርቆ አስቀረው።

"እረ ናቲዬ ትንሽ እኮ ነው የተጫርኩት ከሱ ይልቅ ካንተ ጋር ስላደርኩ የተሰማኝ ደስታ በቃላት የሚገለፅ አይምሰልህ......"

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-20

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

"እረ ናቲዬ ትንሽ እኮ ነው የተጫርኩት ከሱ ይልቅ ካንተ ጋር ስላደርኩ የተሰማኝ ደስታ በቃላት የሚገለፅ አይምሰልህ...... "።

ከዚህ በላይ የልጃቸውን ጉድ መስማት አልሆንልህ ያላቸው አባቷ ገርበብ ያለውን በር ርግደው ያዙትን ስጦታ እንደሳቸው ጉዳን ከተመለከተው ግድግዳ ላይ አጋጭተው ሲሰብሩት።

ሜሪ ድምፁ አስደንግጧት ፊቷን መለስ ብታደርግ ደርባባው ግዙፉ አባቷ የጦር ቀጠና ላይ እንዳለ ጀነራል ትከሻቸው ከወትሮው ሰፍቶ ፊታቸው ቀልቶ አይናቸው ፈጦ ከወዲህ ወዲያ ሲንከራተት ንዴታቸው ከመብዛቱ የተነሳ በህይወት የመትረፏን ነገር እንኳ አጠራጣሪ ሳያደርገው አልቀረም። እንኳን እንዲ ፊቱ ቀልቶ ትንሽ ሲበሳጭ ምን እንደሚያደርግ የምታውቀው ሜሪ ተርበትብታ "አሁን ደና ነኝ እሺ ቻው ቻው" ብላ ከናቲ ጋር የነበራትን የስልክ ግንኙነት አቋርጣ ዞር ስትል .........

★ናቲ★

የሜሪ ስልኳን ተቻኩላ መዝጋት ቢያስገርመውም ማታ ብዙ ስላልተኙ በተጨማሪ የመንገዱ ድካም በዛ ላይ ህመሟ ሲታከልበት በጣም ስለደከማት መተኛት ፈልጋ ይሆናል ስላሰበ ያን ያህል አላስጨነቀውም ነበር።

ከዛ ይልቅ ብቻውን ጋደም ብሎ ሜሪ ከሚያውቃቸው ሴቶች ምን የተለየ ነገር ቢኖራት እንዲ ሊንበረከክላት እንደቻለ እንደ ላብራቶሪ አይጥ እራሱ ላይ research ይሰራ ጀመረ። ሲያወጣ ሲያወርድ ከቆየ በሃላ ስለ 9ኙ ፍቅረኞቹ ሲያስብ በጣም የተቀራረበ አሰልቺ በሃሪዎች ነበራቸው ብሎ ደመደመ።

ሁሉንም አንድ ከሚያደርገው በሀሪያቸው አንዱ ከ ሴክስ በፊት በፍቅርህ ተሸንፈው እንኳ ኩራታቸው መከራ። ውሀ እንደነካው ሳሙና እየተሙለጨለጩ አልያዝ አልጨበጥ ይሉሀል። የትም ብትውል ደንታቸው አይደለም ላንተ ግድ እንደሌላቸው በማስመሰል ይጠመዳሉ። እየወደዱህ እራሱ የትም እንደማትሄድ ያላቸው እምነት የትም እንዳትሄድ ያደርግሀል ላንተ አለመደወላቸው አብዝተህ እንድደውል ያስገድድሀል ምን አለፋህ እሺታቸውን ለማግኘት ደፋ ቀና ማለትህ ግድ ይሆንብህ ይሆናል።

እንዲም እንዲያ ብለህ እጅህ ካስገባሀት በሃላ አብረሃት ታድራለህ ከዛ በሃላ የድሮ በራሷ ያላት መተማመን የትም አትሄድም ብላ ችላ ትልህ የነበረች ልጅ በራስ መተማመኗ እንደ ጉም በኖ ጠፍቶ የትም አትሄድም ብላ ደውላልህ የማታውቀው ልጅ በቀን 10 ጊዜ መደወል ትጀምራለች።

በቀን ያ ሁሉ ጊዜ እየደወለች መተንፈሻ አሳጥታህ እንደ ድሮው ማደውለው ለ sex ፈልገኸኝ ብላ ያላሰብከውን ታሳስብህ ትጀምራለች።

ምን አለፋህ ጭቅጭቋ እየበዛ ሄዶ እንደዛ ጠብ እርግፍ ብለህ ያገኘሀትን ልጅ እየወደድካት መለየት ግድ ይሆንብሀል። በወጣህ በገባህ ቁጥር ከሌላ ሴት ጋር መጠርጠሩ ሲመርህ ሳትወድ player ለመሆን ትገደዳለህ!! እያለ አሰልቺ የፍቅር ታሪኩን በሀሳብ ማህደሩ ገምግም ማጠቃለያ ከሰጠ በሃላ የሜሪን ጣፋጭ የፍቅር ታሪክ ለመገምገም ከእረፍት ተመለሰ።

ሜሪ ከሚያውቃቸው ሴቶች የሚለያት ብዙ ነገር ቢኖርም ዋና ዋናዎቹን ለማሰብ መሞከሩን ተያያዘው። የመጀመሪያው በጣም እንዳፈቀራት ብታውቅም ማፍቀሯን ደብቃ መኩራራትን አልመረጠችም ከ sex በፊት የሚያውቃት ሜሪ ከዛ በሃላም እራሳ ናት።

አስቡት እስቲ ከኪሱ እቃ የተሰረቀበት ሰውዬ እጅ ከፍንጅ ይዞህ ሌባ ብሎ አስደበደበኝ ስትል አትንኩት እርቦት እኮ ነው በከላከልለልህ ምን ይሰማሀል? ይህነን ሰው እንዴትስ አድርገህስ ደግመህ መስረቅ ይቻልሀል? የእድሜ ልኩ ባርያው መሆንህ ግድ ይሆናል።

የኔ ሜሪ እንዲህ ናት በቃ ከሌላ ሴት ጋር መወስለቴን አውቃ የኔ ጥፋት ነው መቅረቴ ነው ያሳሳተህ ብላ የምትከራከርልኝ ምርጥ ሚስቴ የእድሜ ልክ ባርያዋ ብሆን ቢያንስባት እንጂ አይበዛባትም። እያለ የሜሪ ስብሰባውን ቀጠለ ......

★ሜሪ★

.......... አቋርጣ ቀና ስትል የአባቷ ረዣዥም ወፍራም ጣቶች የተደረደረበት መዳፍ ፊቷ ላይ ሲያርፍ አይና ጭልም ልቧም ስልብ አለባት ከጥፊው ድምፅ ውጪ አንዳች ነገር አይሰማም ነበር ...... ከአፍንጫዋ ደማ ጠብ ጠብ ይል ጀመረ....

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-21

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

.......ከአፍንጫዋ ደማ ጠብ ጠብ ይል ጀመረ....

ይህን ያህል እጎዳታለው ብለው ያላሰቡት አባቷ የልጃቸውን ክፉኛ መጎዳት ባዩ ጊዜ ልባቸው ደንገጥ አለ መጀመሪያ የደረሰባትንም ጉዳት ልብ ያሉት ቀምሳ የማታውቀውን ጥፊያቸውን ካቀመሷት በሃላ ነበር። ግንባሯ ላይ ያለው የታሸገ ቁስሏን ከዚያም ሲያልፍ በሳቸው የተነሳ ከአፍንጫዋ እየፈሰሰ ያለውን ደም ሲመለከቱ ከከፍተኛ ንዴት ወደ ከፍተኛ ሀዘን ስሜታቸው ለመቀየር ደቂቃም አልፈጀም ነበር።

እንደዛ ተወንጭፎ የመታት እጃቸው ተልፈስፍሶ ሊያቅፏት ከጀለ ..... ሜሪ ምንም ሳትናገር ለማቀፍ የተዘረጋው እጃቸውን አልፋ ከአፍንጫዋ የሚፈሰውን ደማን እየጠራረገች ክፍሉን ለቃ ስትወጣ እናቷ ከስራ ደክማት እቤት ስትገባ ኮሪደሩ ላይ ተገጣጠሙ። የሆነችውን ስትመለከት በጣም ደነገጠች ሜሪ አረጋግታት ከጓደኛዋ በላይ ለምትቀርባት እናቷ የተፈጠረውን ሁሉ አንድ በአንድ አጫወተቻት።

እናቷም ናቲ ሆነልኝ ያለችውን በሰሙ ግዜ እንደሚያፈቅራት ቅንጣት ያህል ባይጠረጥሩም ልጆች በመሆናቸው ተቻኩለው ነገሮችን

እንዳያበላሹ መስጋታቸው ግን ከፊታቸው ይነበብ ነበር። ሜሪ የእናቷን ስጋት ለማስወገድ በሚመስል አኳሀን ለቁም ነገር እንደሚያስቡ በቅርቡ ሲመጣ ደግም እንደምታስተዋውቃት ቃል ገብታላት እናቷ በ ናቲ ላይ ያላትን እምነት ለማጠናከር ምከረች።

አባቷ በዚህ ሀሳቧ ሊስማሙ ስለማይችሉ ሁሉንም ነገር በሚስጥር እንድታደርግ ከአባቷ ጋር እንደምታስማማት እና አባቷን ይቅርታ እንድጠይቀው አስጠነቀቀቻት።

ሜሪም የተባለችውን አድርጋ የቤተሰቡን ሰላም ወደነበረበት ለመመለስ ቻለ።

★★★★★ናቲ★★★★★

.....እያለ የሜሪ ስብሰባውን ቀጠለ። እስከዛሬ የቀበጠ ሁሉ ምልቃቃ የቀበጠ ሁሉ ጨምላቃ ይመስለኝ ነበር የኔ ሜሪ ግን ቅብጠቷ ልጅነቷ የሚያምርባት የሁሉን ልክ የምታውቅ ኡፍፍፍፍፍፍ እያለ አለቆቹን አስቀምጦ የስራውን ሪሰርች ለማስረዳት እንደሚጥር ቅጥረኛ በሀሳብ ወዲያ ወዲህ እያለ ሳለ አንድ ኮቴ ደረቅ የዶርሙ ልጅ "ናቲ ናቲ " ብሎ ሲጠራው የምርምር ስራውን ከሚያቀርብበት መድረክ በቀጥታ ወደ ዶርም መለሰው።

እሱን ተከትለው የቀሩት የዶርሙ ልጆች ወደ ውስጥ ገቡ ትላንት ምን እንዳበሳጨው ሁሉም ለመስማት ጓጉተው ስለነበር " ምን ሆነህ ነው ትላት ደም ስንደውልም ስልክ አታነሳም " አለ እንደ ሀረር ፊየል አገጩ ላይ ያለች ፂሙን ያስረዘመ ቀጫጫ የዶርም ጓደኛው።

የተፈጠረው አንድ በአንድ ያስረዳቸው ጀመረ የናቲ የፍቅር ወሬ የማይዋጥለት አብሮ አደግ የሀገሩ ልጅ ዳኒ "በሉ እንግዲ እኔ ድድ ማስጫ እጠብቃችሃለው ፍቅር እና እሳት በሩቁ ነው ይል የነበረ ልጅ ደርሶ የፍቅር ሰባኪ ይሁን ሆሆሆ... ጀማሪ ዲያቆን ከቄስ ይበልጣል አሉ እውነታቸውን ነው" ብሎ ከዶርም ተፈተለከ። የተቀሩት ሀ... ብለው የናቲን ወሬ ካደመጡ በሃላ በሷ የተነሳ ከትምህርቱ አጉል እንዳይሆን ምክር ቢጤ ለግሰውት ተያይዘው ከዶርም ወጡ።

ሜሪ እንደ መርዶ ነጋሪ በጠዋት ደውላ ከአባቷ ጋር ምን እንደተፈጠረ እናቷ ያለቻትን በሙሉ ዘክዝካ ነገረችው ከዚ በሀላ አባቷ አጠገባ ሊኖር ስለሚችል እሷ ካልደወለች እንዳይደውል አስጠነቀቀችው telegram እንድሮው እንደሚያወሩም አክላ ነገረችው። እሱም ከሁለት ወር በሃላ ለ apparent እንደሚወጣ 8 ወር ገደማ አጠገባ እንደሚሆን ነገራት እሷም በጣም ደስ አላት .....

★★ከ 2 ወር በሃላ ★★

አንዳንዴ የፈለገ የምታፈቅረው ሰው ቢሆን ደጋግመህ ስታገኘው ትሰለቻለህ እንደድሮው አይሆንም ፍቅርህ ይቀንሳል ተብሎ ቢታሰብም የናቲ እና የሜሪ ግን በተገናኙ ቁጥር ፍቅራቸው እየጠነከረ መሄዱ አጀብ ያስብላል።

ሲገናኙ ገና ከርቀት ሲያያት በስስት አይን አይኗን እየተመለከታት ከወረደችበት taxi ከመሮጥ ባልተናነሰ እርምጃ አጠገቧ ይደርሳል እሷም ፊቷ ፍም ሆኖ ይፈጃታል ሙቀቱን መቋቋም ያቃታቸው የሚመስሉ ጉንጮቿ እንደ እንጆሪ ቀልተው ላያቸው ብሉኝ ብሉኝ ያሰኛሉ አይኖቿ ሙሉ ለሙሉ ሊያዩት አይቻላቸውም አንዴ ወደ አይኑ አንዴ ወደ መሬት የምሰብራቸው አይኖቿ ተጨማሪ ውበትን አጎናፅፏታል እርብትብት እያለች ከከፈተላት እጆቹ መሀል ገብታ ቀና ብላ ከንፈራን ትሰጠዋለች ሰው አየኝ አላየኝ የማያውቀው ፍቅራቸው ተመክቶ ጎንበስ ብሎ ከንፈራን በከንፈሩ በስሱ ሲስማት የተመለከተ መንገደኛ በሚያየው ነገር ጎምዥቶ ስጋ እንዳየ ውሻ አፋ በምራቅ ይመምላል ብል ማካበድ አይሆንብኝ።

በጣም በሚገርም ሁኔታ መንገድ እንኳ ለመሻገር መኪናው እንሱን ቆም ቢጠብቅ እንጂ እነሱ መኪና የማሳለፍ ትግስቱ የላቸውም ብዙ

ጊዜ የሚገናኙት በ15 ቀን አንዴ ስለነበር እሷ ሁለመናው እርቧት እሱም እሷን በመናፈቅ አልቆ ሲተያዩ ብዙ ነገራቸው ከቁጥጥር ውጪ ይሆንባቸዋል። በፍፁም እንደ ሰው ቢርባቸው እንኳ ምሳን አስቀድመው አያውቁም ሁሉም ነገር ናፍቆታቸውን ካስታገሱ በሃላ ይርሳል ባይ ናቸው።

እንደው እንደተገናኙ ሊበሉ ግድ ሆነባቸው ቢባል እንኳ ሰወር ያለች ቦታ ለመሰለል አይናቸው ይዳክራል እንዳገኙ ለመቀመጥ ሰዋራዋን ቦታ ተገን አድርገው መሳሳም ይጀምራሉ እንደ ፈንጂ አምካኝ በተሰጧት የማሳወቂያ በትር በመሰሉ እጆቿ ፈንጂ ወረዳውን ሳታስጠጣ ነካ ነካ ስታደርገው አንዳች ነገር ፈንቅሎ ሊወጣ ሲታገል ትመለከታለች ያኔ እዛው ሊበላ የታዘዘው ምግብ take away ይሁንልን ብለው አስተናጋጁን ያጣድፋታል። የያዙትን ምግብ ይዘው እየተመናቀሩ ክፍላቸው ይገባሉ እሱን እረስተው የናፍቆት ትግላቸውን ይቀጥላሉ። በአጭሩ እሷም ለሱ ሱሱ ናት እሱም ለሷ ሱስ ሆኖባታል።

ምናልባት በአንድ ሰሀን የሚበሉ በአንድ ብርጭቆ የሚጠጡ ጥንዶች ተመልክታቹ በፍቅራቸው ተደንቃቹ ይሆናል ነገር ግን በአንድ አፍ አኝከው በሁለት አፍ የሚውጡ ጥንዶች ብታይ ግን ናቲ ና ሜሪ መሆናቸውን በፍፁም አትጠራጠር።

እንደ እርግብ እሱ ያኘከውን እሷ እሷ ያኘከችውን እሱ ለመዋጥ ሲጣደፍ ያለ አንዳች መጠየፍ ነው እሱ የጠጣውን እሷ እሷ የጠጣችውን እሱ መጣታቸው የተለመደ ሆናል ምን አለፋቹ ናቲ እና ሜሪ ያለፉት 4 ወራትን በእንዲህ አይነት ሁኔታ ነበር ያሳለፉት ........

★★ሜሪ★★(ከ 4 ወር በሃላ)

ሜሪ ክፉኛ ታመመች ሀኪሞች ተስፋዋ በጣም የተመናመነ መሆኑን ሲነግሯት ናቲ ስቃይዋን እንዳይሰቃይ ጉዳቷን እንዳይጎዳ ከዚያም አልፎ በህይወት ብታልፍ የሚጎዳው ጉዳት ከህሊዋ በላይ ቢሆንባት ልትርቀው ብትምክርም ስልኳን መደወሉን አላቆም ማለቱ ቢየስጨንቃት እንዲቆርጥለት ሲደወል አንስታ ልታናግረው ወሰነች ..... ናቲ እንደተለመደው ሙከራወን ቀጠለ ስልኳ ይጠራ ጀመር ሜሪ እንባ እየተናነቃት ዋጥ አድርጋው ቆፍጠን ብላ አነሳችው።

ሜሪ:- "ሄሎ ምን ፈለክ".......ናቲ ያልጠበቀው ነገር ስለሆነበት ግራ ገባው

ናቲ:- " ሁና ምን የተረፈኝ መሰለክ ካንተ ማከክ ብቻ ነው ተማሪ መጥበስ ትርፋ እሄ ነው አባቴ ልክ ነበር መጀመሪያም ለማንኛውም አክስቴ የሆነ ሀብታም አግብቼ አሜሪካ እንድሄድ አመቻችታልኝ እኔም

ተስማምቼ ከአንድ ወር በሃላ ለመሄድ ሁሉንም ነገር ጨርሻለው አንተም አብራህ ጊታር የምትመታ ሴት ፈልግ" ብላ ጆሮው ላይ ዘግታበት ለቅሶዋን ቀጠለች .........

.

.

.ይቀጥላል

# ክፍል -22

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

......ናቲ መብረቅ እንደመታው ሰው ድንዝዝ ብሎ አንድ ቃል ሳያወጣ የወረደበትን የቃላት ጋጋታ ካዳመጠ በሃላ የራሱን ጆሮ ማመን እስኪያቅተው ድረስ የሱ ሜሪ መሆኗን ተጠራጠረ። በሆነ ነገር ተበሳጭታ ይሆናል ብሎ እራሱን አረጋግቶ መደወሉን ቀጠለ።

ሜሪ:- " ቆይ አንተ እስከዛሬ ምን አደረክልኝ??" ብላ ስትጮህበት ልቡ ስንጥቅ ሲል ተሰማው የሚስበው አየር እንደ ድመት ጉሮሮው ስር ኩርር ኩርር ይልበት ጀመረ አንዳች መልስ መመለስ ቢያቅተው ስልኩን ዘግቶ እራሱን ለማረጋጋት ሞከረ።

"ቆይ ለሰው ልጅ ማድረግ የሚባለው ምንድነው? ውድ ስጦታዎችን መስጠት ወይስ ምርጥ ቦታ ወስዶ ማዝናናት ወይስ እኔ በፍፁም አልገባኝም .... እሄስ ከነበረ ማድረግ ማለት ለሷ እኔ አስመጪ እና ላኪ ነኝ ብዬ አልጠበስኳት ለምን ይሄ ሁሉ መንገድ አብራኝ ተጓዘች??" እያለ በንግግር ያቀሰለችው ልቡን በሃሳብ ጋጋታ እየጎረጎረ ማድማቱን ተያያዘው።

"እኔ በበኩሌ አባትም እናትም ጥሩ ባልም ለመሆን መምከር ከማድረግም በላይ ነው ብዬ አስቤ ነበር ይሄ ሁሉ መንገድ መጓዜ

ለምሳሌ .....

እንደልጄ ሳስባት:- የምትናገረውን ክፉ ነገር በሙሉ ልጅ ስለሆነች እኮ ነው ስሜቷን መደበቅ ስለማትችል ክፉ እና ደጉን ባትለይ አትፍረድባት ብዬ እራሴን ጎሸም አደርጋለሁ። ሲብስም ብታጠፋ ልጅህ ናት አልኩህ አይደል እንዴ? ልጄ አጠፋች ብለህ የምትተው ክፋ አባት አትሁን በል ደውለህ ታረቃት ብዬ እራሴን በቁጣ እገስፀዋለሁ በራሷ ጥፋት ተለማምጬ እታረቃታለው።

እንደ አባት:- ሳስብ የምትወጣበትን የምትገባበትን ሰዐት ተቆጣጥሬ በፊት አደረኩት አደረኩት ካለችኝ ይጎዳታል ብትቀጥልበት ብዬ ያሰብኩትን ላስተዋት እምክራለሁ።

እንደ ባል:- ሳስብ ደግም ሁሉንም ነገሯን ከኔ ውጪ ማንም ባያይብኝ ብዬ እመኛለሁ። ጡቷን ጭኗን ሰው ያየው ከመሰለኝ የወሰደው ያህል ያንገበግበኛል ኡኡ ብዬ እጮሀለው ልብስ መቀየሯ ግድ ይሆናል። በአጭሩ እጅግ በጣም እሳሳላታለሁ ለ አንድ ደቂቃ ከአይኔ ስር ባጠፋ ምኞቴ ነው በየደቂቃው የምታደርገው ነገር ያሳስበኛል ለኔ 24 ሰዐቴ እሷ ናት።

እንደ እናት:- በፍፁም በየትኛውም ሁኔታ ላጣት አልፈልግም ጥፋት በታጠፋም እኔ ባጠፋም ክብሬን ጣል አድርጌ የማይሰራውን ሰርቼ ልመልሳት ግድ ይሆንብኛል። የከረረ ፀብ ውስጥ እንኳን ገብተን አንዳች አጉል ነገር ላደርግ ነው ካለች ሁሉን እረስቼ ከምታደርገው ነገር ላድናት ስበር እቤቷ እደርሳለሁ። እናት ክብሬን ብላ ልጇን ትተዋለች እንዴ? እናት ተሰደብኩ ብላ ክፉ ነገር ልታደርግ ልጇ ስትጣደፍ ዝም ትላለች እንዴ?? እያልኩ ሁሉን እረሳለው።

እንግዲህ እኔ እንዲህ ነበርኩ እንኳን አስከፍቻት አስከፍታኝ እጨነቅለታለሁ እንኳን አጉል ነገር ላደርግ ነው ብላኝ ስላስከፋዋት አጉል ነገር ብታደርግስ ብዬ እንቅልፌን አጣለሁ። ቆይ እናትነት ስንት ብር ነው?? የቱ መኪና እሄን እናትነት ይቀይረዋል። ይህን ሁሉ ነገር ከአንድ ሰው ማግኘትስ ቀላል ነው እንዴ? ምን አደረክልኝ ማለት ይህን ሰው አይከብድም??"
እያለ እያንዳንዱ ነገር በህሊናው እየተገለባበጠ ስቃዩን ያበዛው ተያያዘ።

አልፈለኩም እኔ አስገድደውኝ እንዲ ላደርግ ነው አግዘኝ የሚል ወሬ እንኳን ቢሰማ ከገባችበት ችግር ፈልቅቆ ለማውጣት ጥረት ባደረገ ነበር ነገር ግን እሷ እራሷ ፈልጋ እንደምታደርገው እየሰማ ማንን ነው ከማን ውስጥ ፈልቅቆ የሚያወጣው ሁሉም ነገር ተስፋ

ቢያስቆረጠው "ብዙ ጊዜ ዋጋ ሊወጣላቸው የማይችሉ ነገሮች እርካሽ ናቸው። ወንድሜ የምተነፍሰው አየር ቢከፈልበት ስንት የሚያወጣ ይመስልሀል? በየቀኑ አፍንጫህ ስር ብታገኘው እርካሽ ይመስልሃል እንጂ ለ 2 ደቂቃ ብታጣው ዋጋው ይገባሀል...." እያለ ለራሱ ድጋፍ በመስጠት ከህሊናው ዱላ እራሱን ገሸሽ ለማደረግ ምከረ።

ፍፁም ነኝ ብዬም አላስብም አጥፍቼም ይሆናል ነገር ግን እህቴ ትልቅ ወረቀት ላይ ትንሽ ነጥብ አድርገው ምን ይታይሻል ሲሉሽ ነጥብ የምትይ ከሆነ እመኝኝ እውር ነሽ? ሰፊው ወረቀትን መመልከት ያልቻለ አይን እንዴት ነጥቧን መመልከት ሆነለት? ሰፊው ጥሩነቴን ማየት ተስኖት ለእይታ ትንሽ የሆነችውን ችግሬን አጉልቶ ሊተወኝ የሚምክር ሰው ምንኛ ምኝ ነው። ብሎ የተለመደ ወቀሳውን በዚ መልኩ እያቀረበ ሳምንታት ቢያልፋም አንድም ተስፋ የሚሰጠው ነገር ማግኘት አልሆንልህ አለው።

ሀሳቡም ተደራርቦ እንቅልፍ ይነሳው ጀመረ ሂወቱ በማይስተካከል ጭንቀት ወዲያ ወዲህ ሲወዛወዝ ለያብድ ትንሽ የቀረው ያህል ይሰማው ጀመረ ያኔ ነበር ክፉውን ውሳኔ ለመወሰን የተገደደው

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-23

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

★ሜሪ★

ሜሪ እያደረገች ያለቸው ነገር ልቧን ቢሰብረውም ከዚህ የተሻለ ነገር ለናቲ ማሰብ ተስኗታል። አብሯት ሆኖ ህመማን ከሚካፈል ከዚያም ካለፈ በምቷ ምቱን ከሚመኝ በጊዜ በሷ ተስፋ ቆርጦ የውሃ አጣጬን እንዲፈልግ ጭንቅላቷ ያላትን ብታደርግም ልቧ ግን የሚወድሽ ከሆነ ምንም ብታደርጊ ታግሎ ይመልስሻል እያለ የምኝ ምክሩን ይለግሳታል።

መልሳ ደግሞ ፈጣሪ ያድናል ብሎ የማያምን አለ? የለም እአ..? ግን ፈጣሪ ያድናል ብሎ ከ ፎቅ መዝለል ፈጣሪን መፈታተን ካልሆነ ምን ይባላል? እኔም እንደሚወደኝ እያወኩ ይህን ያህል መፈተን ፈጣሪ ያድናል ብሎ ከመዝለል አይተናነስም። ብሎ ልቧ መልሶ በመመለሱ ተስፋ ይቆርጥባት እና ሁሉንም ነገር ዝርግፍ አድርጋ ልትነግረው ትከጅል ጀመረ።

በሁለት ሀሳቦች መሃል እየዋለለች ነው።

★ናቲ★

.........ያኔ ነበር ክፉውን ውሳኔ ለመወሰን የተገደደው ናቲ ተስፋ ቢቆርጥባትም መልካም ነገር ከሰማው በሚል መንፈስ የመጨረሻ የስልክ ጥሪውን ሲያደርግ ሜሪ ከሀሳቧ በርግጋ ነቃች ተክለፍልፋ አነሳችው።

ሜሪ:- "ሄሎ ..." በተረጋጋ ድምፅ ስትለው

ናቲ:- "ሄሎ ሜሪዬ ዛሬ የተረጋጋሽ ትመስያለሽ" .... ብሎ ሃሳቧን የቀየረች ያህል ደስ አለው።

ሜሪ:- "ቆይ አንተ ከኔ ሌላ ሴት አታውቅም እንዴ?" ካለችው በሃላ ደንገጥ አለች።

ናቲ እስከመጨረሻው አይኗን ላለማየት ማለ መለማመጡን ረገመው አፍቅሮ ከኖረበት ጊዜ ሴት ሲያገላብጥ የኖረበት ጊዜ ጣፋጭ መስሎ ይታየው ጀመረ።

ነገር ግን ንዴቱን ለማብረድ እንደ ኢትየጲያ የፊልም አክተሮች ክለብ ለክለብ መሮጡ ስላልፈለገው fb ላይ ጓደኛው ከሆነችው ከሜላት

ጋር አልጋው ላይ ጋደም ብሎም እያወራ ሳለ ከጓደኞቿ ጋር የተነሳችውን ፎቶ ትልክለታለች።

★ አናምርም?

-ደስ ትላላቹ ማናት 3ኛ ላይ ያለችው ቆንጆዬ ነገሯ?

★ጄሪ ነው ስሟ ምነው ተከይፈህባት ከሆነ ተስፋ ቁረጥ የሌለ አካብዴ ናት በዛ ላይ ባል አላት ባይሆን ሌላ ላጣብስህ?

-እረ እራሷን ነው ምፈለገው ? fb ስሟን ስጭኝ?

★ ባል አላት እያልኩህ? አትጠብሳትም የፈለከውን እናሲዝ? "jerry Ak" ነው ስሟ

- እሺ አሲዘናል በቃ

ናቲ የምታካብድ ቆንጆዬ ሴት እንደማሳመን የሚያዝናናው ነገር ኖሮ አያውቅም ከአንዷ በስተቀር ሁሉም ሚስቶቹ ከዛው ምድብ በመሆናቸው ነው ትኩረቱን የሳቡት ሜሪንም ጨምሮ። ከሜሪ ጋር ከጀመረ በሃላ ግን በፍቅሯ ሰክሮ የድሮ በሀሪውን እርግፍ አድርጎ የነበረ ቢሆንም ድጋሚ በእሷው በደረሰበት በደል የተነሳ የድሮው በሃሪው ተቀሰቀሰበት።

ጄሪን ባልተለመዱ ደሳስ በሚሉ ወሬዎች ልባ ላይ እምነት ማሳደሩን ቀጠለ የሚያወራቸው ወሬዎች እለት ከእለት ብታነባቸው አለሰለችሽ አሏት ከዛም አልፋ ከጥንት ጀምሮ ያለው ታሪኳን ትዘረግፍለት ጀመር ።

ናቲም እሷን በእጁ ለማስገባት ይጠቅመኛል ያላቸውን ሲመዝ ሲጥል ቆይቶ በድንገት ባሏ አብሯት ሆኖ እንደወሰለተባት እሷም ልደግመው እንደምትፈልግ በግልፅ ነገረችው እሱም የሆነውን ሁሉ አጫወታት ሁለቱም አብረው ለማደር ተስማሙ ነገር ግን እሷም ባሏን ለመበቀል እሱም የሜሪን ክህደት ለመርሳት እንጂ ከዛ የዘለለ ምንም አይነት ነገር እንደማይኖር ተማምነው ለመገናኘት ተቀጣጠሩ።

★ከሳምንት★

የሚገናኙበት ቀን ደርሶ ጄሪ ደወለችለት

※ ሄሎ

※ ሄሎ ናቲዬ የት ብዬ ነው ምወርደው " ከዚ በፊት ሄዳበት የማታውቀው ሀገር ስለሆነ ቦታውን ቢጠቁመኝ ብላ

※ "B.M ብለሽ ውረጂ " አላት ነብሱ በሚያፈቅራት ሜሪ እንደተቃጣለ

※ "እሺ ውዴ"

ከ 4 ሰዓታት በሃላ

--ደወለች

ጄሪ:- "ደርሻለው"

.

.

.

.

#ይቀጥላል

# ክፍል-24

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

"እሺ እኔም እዛው አከባቢ ነኝ አስፓልቱን ተሻግረሽ ጠብቂኝ"

እሺ እንዳትቆይ

ብላ ስልኳን ዘጋችው በስሱ ቢሆን ጥርጣሬ ጎሽም ያደርጋት ጀመሯል።

ካወቀችው 15 ቀን እንኳ በስረአት ያልምላውን ልጅ አምና ስንት አገር አቋርጣ መምጣቷን ለሰማ ልጅቷ አለሌ ዱርዬ ብትመስለው አይገርምም። ነገር ግን ጄሪ አለሌም ዱርዬም አልነበረችም ከወሰለተባት ጓደኛዋ ውጪ ገላዋን የቀመሰው ኖሮ አያውቅም ነገር ግን ከናቲ ጋር ለቀልድ እንኳን ወሬ መጀመር ካላሰቡት አዘቀት ለመግባት ከመሞከር አይተናነስም።

hi ምናምን ብሎ ሙሉ ቀን እንደሚያሰለቹሽ ወንዶች ተንዛዝቶ ወሬውን ይጀምራል ብለሽ ካሰብሽ እመኝኝ ምኝ ነሽ ከዚያ ይልቅ ኮስተር ብሎ እንደሚያቅሽ ሰው ስለአንድ ነገር በቁም ነገር ማውራቱን ይቀጥላል። ጉዳዩ ፈገግ ስለሚያደርግሽ ከ 113ቱ "hi" የሚሉ መልእክቶች የናቲን መርጠው ለማንበብ አይኖችሽ ቢጣደፉ

ጣቶችሽ እንደ ደ.ኮሪያ ሚሳኤል ደጋግመው ስልክሽ ላይ ድብደባ ቢያደርሱ ኔትወርክ ከወትሮ በተለየ መልኩ ቀርፋፋ መስሎ ከተሰማሽ እመኝኝ ናቲ ነው። አቅሙ ካለሽ ሳታነቢ ብሎክ አድርጊው ብሎክ የማድረግ አቅሙ ከሌለሽ ግን መልእክቱን አትመልሺ።

መልእክቱን ከመለሽ ግን አለቀልሽ በሀሳብ ከሚገርመው ተራራ ያወጣሻል በፅሁፍ አቅፈሺው ለመብረር ትገደጃለሽ ካለ እሱ ወሬ ወሬ አይመስልሽም አፍጠሽ fb ላይ መዋል ስራሽ ያደርገዋል ሳታገኚው ያገኘሽው ይመስልሻል ሳታውቂው ያወቅሺው ያህል ይሰማሻል በፍፁም ከሌላ ወንድ አይተሽው በማታውቂበት መንገድ ይዞሽ ይነጉዳል በሃሳብ ትዳርሽን ለመመስረት ትጣደፊያለሽ ሳታስቢው እራስሽን ለሱ ድረሽ ታገኚዋለሽ።

ልክ እዚህ ደረጃ ላይ ስደርሱ በስልክ እንድታወሩ እንድሉን ያመቻችልሻል ማውራት ስትጀምሩ ከአንደኛው ሰማይ ከፍ አድርጎሽ ወደ ቀጣዩ ሰማይ ከመጀመሪያው በተለየ ፍጥነት ይዞሽ መንጎዱን ይቀጥላል እህቴ ከላይ ወደስር በምታይው ነገር በሃሴት ትሰክርያለሽ ከአንቺ በላይ ደስተኛ ሰው አለ ብትባይ አታምኝም ነገር ግን ከፍታውን ስትመለከቺ እንደ ቅልጥም ሰባሪ ንስር ከሰማይ ወደ ምድር ለቆኝ ድንጋይ ላይ ፈጥፍጦ እንዳይስብረኝ ብለሽ መፍራት ትጀምሪያለሽ። በሁለት ሀሳብ መሀል ትዋዥቂያለሽ እንዳትወርጂ የምታይው ነገር ማራኪ ነው ካለ እሱ ደግሞ ይህን ማየት

የማይታሰብ መሆኑ ስትረጂ ላለመውደቅ ትጣበቂበታለሽ።

መጣበቅሽን ሲያውቅ ደግም ወደ ሶስተኛው ሰማይ ሊወስድሽ በአካል ይመጣል ላግኝሽ ሲልሽ አትከራከሪውም በበረራ ቀድመሽ ተዳክመሻል ከሁለተኛው ሰማይ መልሰኝ ብለው ቢለቀኝስ ብለሽ ትፈርያለሽ ሳታንገራግሪ ጉዞ ወደ ሶስተኛው ሰማይ .........

=ደወላት

※ " እያየሁሽ ነው ተሻገሪ"

ከርቀት ሆኖ በእጁ ምልክት ሲሰጣት ተመለከተችው እና ራመድ ራመድ ብላ ተሻገራ አጠገቡ ደረሰች።

Entrance ተፈትና ለእረፍት ክፍለ ሀገር ዘመዶቿ ከርማ በምትመለስበት ሰአት ነበር እንደ ቡና ቀሻቢ መሀል ላይ አምታታ የመጣችው ለዛም ሳይሆን አይቀርም በልብስ የተሞላ ቦርሳ በጀርባዋ ይዛለች።

※ "ደክምሻል አይደል ላግዝሽ"

※ "ኖ እኔ እይዘዋለው እሩቅ ነው እንዴ አልጋ የያዝከው"

※ "እረ አይደለም ያው እዛ ግቢ ነው"

አላት ከፊት ለፊት ያለውን ፔንሲዬን በእጁ እየጠቆማት። ነገር ግን ብዙ ማውራት የማይሆንላት ጄሪ ስትጠይቅ ከምትመልሳቸው አጭር መልሶች ውጪ ለጨዋታ የሚጋብዝ ወሬ ማውራት አለመቻሏ ለናቲ ብዙም አልተመቸውም ነገር ግን በቁንጅናዋ ተፅናንቶ ወደ ክፍሉ ይዟት ገባ።

ጄሪ መካከለኛ ቁመት ሸንቀጥ ያለ ሰውነት ሲኖራት የፊቷ ገፅታ ደግም በጣም የልጅ ነው። ጥሩ ተደርገው የተቀረፁት ከንፈሮቿ በሚያምሩት ጥርሶቿ ሲታጀቡ ቆንጆዬ ልጃገረድ ያሰኛታል። ሜካፕ ባታዘወትርም ቆንጆዬ መሆናን ሁሉም ነገሯ ይመሰክርላታል። ሻንጣዋን ወንበር ላይ አስቀምጣ እየተጣደፈች ወደ ሻውር ስትገባ በአይኖቹ ሸኛት።

አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ተጣጥባ እስክትመጣ ስልኩን እየጎረጎረ መጠበቁን ተያያዘው። ሙሉ መረጃውን ሲያሳያት  ቀኑን ሙሉ ተሸንፌያለው እባክህን እህቴን ተዋት እያለች የምትጨቀጭቀው ሜላት ሀሳቡን መንታ መንገድ ላይ ብትጥልበትም ያኔ በጄሪ በጣም ከመተማመኗ የተነሳ ምንም ቢፈጠር ላለመደወል በእናቷ የገባችው ቃል ጠፍሮ ስለያዛት አሁንም ናቲን እንጂ ጄሪን መግራት አልሆን ቢላት ትደውልልለት ጀመር?

ጄሪ የተባባሉትን እንዳትሰማ  ወጥቶ ያናግራት ጀመረ።

※  "ናቲዬ ስምትልህ እህቴን ተዋት " እያለች ታሰቃየው ጀመር

※ "እሺ አልኩሽ አይደል ከዚ በላይ ከጨቀጨቅሽኝ አትራጠሪ አደርገዋለሁ" ብሎ ስልኩን ዘግቶባት ወደ room ሲመለስ ጄሪ ተጣጥባ እንደ ድፎ ዳቦ ከላይም ከታችም በፎጣ ተጠቀልላ ስትወጣ ለሜላት ቃል መግባቱን ሁላ ዘነጋው ክው ብሎ ቀረ  ሜሪን ለመበቀል ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ እንደማያገኝ በማሰቡ "ነይልኝ የኔ ጣፋጭ" ብሎ እቅፍ አድርጎ አጠገቡ አስቀመጣት።

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-25

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

★ሜሪ★

ሜሪ ህመሟ አልጋ ላይ ካዋላት 20 ቀናቶች ቢያልፏትም ይህ ነው የሚባል የመዳን ተስፋ በአካሏ ላይ አይታይም። ናቲ በአይነ ህሊናዋ እየተመላለሰ በናፍቆት ቢያሰቃያትም አንዴ የተናገረችውን ላለማጠፍ በሚመስል አኳሀን እውነቱን ከመናገር ተቆጥባለች። ሜሪ ለመደወል ያላት ፍላጎት ከቀን ወደቀን እየጨመረ ቢመጣም አንድ ነገር አንዴ ካወራች ስህተት መሆኑን ብታውቅ እንኳን ክችች ብላ መፅናቱ ክብሯን የሚጠብቅላት መስሎ ስለሚሰማት ከደረቀች መመለሻ የላትም።

በአጭሩ ያንን ከመሰለ ፍቅር ነገ በእጇ የሚገባው ክብሯ በእጅጉን ያሳስባታል ያወራችውን አጥፋ አብራው ከምትኖር አንድ የሚወደኝ የምደው ልጅ ነበረ.... እያለች እንደድሮ የተረት አባት እድሜ ልኳን ብታወራ ይቀላታል። ከናቲ ጋር ፍፁም ተቃራኒ ከሚያደርጋቸው በሃሪዎች አንዱ ይሄ ነው። እሱ #ከነበረኝ #አለኝ ማለትን ስለሚመርጥ ክብሩን ምኑን አዋርዶ ሊመልሳት ይጥር ነበር!!

★ናቲ★

"ነይልኝ የኔ ጣፋጭ" ብሎ አጠገቡ አስቀመጣት።

እውነት የዚን ያህል ልብ የሚሰብር ነገር ከየት ይመጣል እዩልኝ ሁለት የተሰበሩ ልቦች አንዳች ክፉ ነገር ለማድረግ ስንቱን ዶልተው ስንቱን አውርተው ጉዳታቸውን ይጠገንላቸው ይመስል የተደረገባቸውን ሊደግሙት ሲታገሉ። ቢሆንላቸው ሁለቱም ይህን ማድረግ ፍላጎታቸው አልነበረም ቢሳካላቸው ጥሩ አፍቃሪዎች ነበሩ አንዳንዴ ባፈቀርከው ሰው ተስፋ ስትቆርጥ ብትከበር ብትረክስ ጉዳይህ አይደለም የምታከብረው ገላህ ዋጋ ያጣብሃል ዋ.... ያፈቀረ ሰው አይጎዳ ያሰኛል.....

"ወንድሜ የአንድ አፍቃሪህን ልብ ስትሰብር ያንተ ማጥፋት ሳያንስ እንደ አንተው አይነት ወንድምህን መጫወቻ ለማድረግ የምትታገል ሴት እየፈጠርክ መሆኑን አትርሳ። አንተ ባጠፋኸው የሷ የእውነተኛ አፍቃሪ የሆነው ያንተ የዋሁ ወንድምህ ይገረፍባታል። እሱ ላይ ቢያበቃ መልካም ነበር እሱም የሷ ግርፋት ሲመረው እሷን ትቶ የምታፈቅረው ሴት ላይ ይጣበቃል። የዛች በቀል ለዚች ምስኪን ሴት ይተርፋል እሷም በተመሳሳይ ትቀጥላለች...... አንተ እንደቀልድ የሰራሃት ስህተት አንዱን ሁለት ሁለቱን አራት እያደረገች ሚሊየኖችን ታበላሻለች። ከዛም ወንድ እኮ? እንዲህ ነው .......ሴት እኮ እንዲያ

ናት? እየተባባሉ መወቃቀሱ ይሰፋል፡፡

እህቴ አንቺም አመመኝ ብለሽ የምትወጂው ፍቅረኛሽን አውጥተሽ መጣል ማለት ድመት ልጆቿን ቅርጥፍ አድርጋ የምትበላው በጣም ከማፍቀሯ የተነሳ ነው የሚባለውን አይነት ቀልድ እየቀለድሽ መሆኑን አስተውይ!! ምትን ከፈራሽ ማንንም አትቅረቢ? የኔ እህት ስንቱ ትን ብሎት ድፍት እንዳለ ቢገባሽ ስንቱ 1000 አመት የሚኖር መስሎት ደረቱን ነፍቶ ሲወጣ የመኪና እራት ሆኖ መምቱ ካወቅሽ የታመመ ሁሉ #አይምትም የቆመ ሁሉ #አይኖርም የሚለው ተረት በገባሽ ነበር ... እንኳን ዶ/ር ፈጣሪ ቀንሽን ቢነግርሽ ......፡፡" ተፋጠው ለመርከስ የሚዘጋጁ ያዘኑ ልቦችን ስመለከት እንዲህ ብዬ በዳዬቹን በመከርኳቸው አሰኘኝ ፡፡

......በግድ እናድርግ የተባለች ይመስል አይኖቿ ቀልተው ሻውር ሆና ማልቀሷን ያሳብቁባታል ልቧ ከዚህ አፀያፊ ስራ ለማምለጥ ይመስል እንደታረደ በሬ ሲንፈራገጥባት ፈንቅሎ እንዳይወጣባት በሚመስል መልኩ በእጇ ደረቷን ያዝ አድርጋዋለች!!

ናቲም ተመሳሳይ ስሜት እየተሰማው ቢሆንም ሜሪ ቤተሰቦቿ ያመጡላት ባሏ ይሄኔ ምን እያደረጋት እንደሆነ በህሊናው ይታየው ጀመረ፡፡

ሲስማት .....እራቁቷን ሆና በቃ ሁሉም ግልፅ ሆኖ ሲታየው በጣም ሲበሳጭ ዝም ብላ በትለየውስ ምናለ ወንድ ጋር ልሄድ ነው እንኳን ባትለው ብዬ አስባለው ...... በህሊናው የሚታየው ሰውዬ ሜሪን እንደሚያደርጋት እሱም ጄሪን ለማድረግ ከጀለ።

አይኖቿን ጠረግረግ አድርጎላት ሳም አደረጋት። በህሊናው የሚታየው ሰውዬ የሜሪ ልብስ ሲያወልቅባት ሲመለከት ነብሱ ተጨነቀች የጄሪ ፎጣ ጎትቶ ፈታባት በስሱ ገፋ ሲያደርጋት ሳይበላ እንደከረመ ሰው አቅም ያጣች ይመስል አካብዳ በጀርባዋ ተኛች .......ሊስማት ሲጠጋት ስልኩ እናቱ ጥላው ገበያ እንደሄደችበት ህፃን ማለዘኑን ጀመረ

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-26

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

የሚያደርገውን አቁም እላይዋ ላይ እንዳለ እጁን ዘርግቶ ከተቀመጠበት ትንሽዬ ኮመዲኖ ላይ አንፏቆ አነሳው ሲያየው ሜላት ናት። ደግማ መደወሏ በጣም እንዳበሳጨው እንደ ጣሳ የተጨማደደው ፊቱ ምስክር ነው ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘግቶት ወደ ጀመረው የጄሪን ገላ የማጣጣም ስሜቱ ከቀድምው በጋለ መንፈስ ተመለሰ።

※ናቲዬ ምነው ችግር አለ እንዴ

※እረ የለም ዝም ብሎ ነገር ነው

ብሎ እሷ ከስር እሱም ከላይ እንዳሉ ከንፈሮቿን ይስማቸው ጀመረ እሷም ስትስመው የዋዛ አለመሆኗን ከንፈሩ ላይ የተጣበቁት ከንፈሮቿ አሳበቁለት ሁለቱም ለጊዜውም ቢሆን ከደረሰባቸው ነገር እፎይታ ለማግኘት ይጣደፉ ጀመረ ናቲ ከስር ያደረገውን ግልገል ሱሪ ደግም አያደርገው ይመስል መንጭቆ አወለቀው።

የጄሪንም የተጠቀለለችበትን ፎጣ ሙሉ ለሙሉ ከላይዋ ላይ አነሳው ትልልቅ ጡቶቿ ትንንሽ ከንፈሮቿ ሙሉ ሰውነቱን ሲያግሉበት ታወቀው

በቃ የሜሪ ውሸት ናቲን ሌላ ገላ ላይ ጣለው ሁሉም ነገር በፍጥነት መከናወኑን ቀጠለ ናቲ በጄሪ ገላ ውስጥ ለመጀመርያ ግዜ የሚገባበት ሰአት ናፈቀው ጄሪም የናቲ እቅፍ ውስጥ እራቁቷን ተጣብቃ እንደ ጡት ከንፈሮችን ትመጠምጠው ጀመረ ሁለቱም አንድ ለመሆን ከመጓጓታቸው የተነሳ በመሀላቸው ክፍተት የለም በሚባልበት ደረጃ ተጣብቀዋል።

ናቲ ተቆላልፈው የተዘረጉትን እግሮቿን ከፈተዉ እሷም ተመቻችታ ተኛችለት ገላውን ከገላዋ አዋሀደው ያ ሁሉ ፍቅር ያሁሉ ለሜሪ የነበረው ነገር በዚች አልጋ ላይ እረከሰ ናቲ ከገባውበት አይቀር በሚመመስለ መልኩ ጄሪ ላይ እልሁን ይወጣ ጀመረ እሷም የሆነችውን በማሰብ እንቅ አድርጋው አድርጋው ከገቡበት ሰመመን ጨርሰው ነቁ።
ሻውር ለመውሰድ ወደ ውስጥ ሲገቡ ጄሪ ለቀሶዋን አቀለጠችው።

※እንዴ ምን ሆነሽ ነው

※እንዴት እንዲ አደርጋለሁ

ጭራሽ መንቀጥቀጥ ጀመረች ናቲ ሁኔታዋ ግራ ግብት አለው እቅፍ አድርጎ ያባብላት ጀመረ በፍፁም እንዲ አትሁኚ በቃ እኔ አለሁልሽ

ጃሪዬ እያለ ምን ያህል መጎዳቷን የተረዳ ይመስል ሊያረጋጋት ምከረ ።

እሱም ከመጀመሪያው ይልቅ አሁን የፀፀት ስሜቱ እያየለበት መጣ ወይኔ ምንድነው ያደረኩ? በቃ ፍቅሬን አርጄ በላሁት ማለት ነው? እያለ የሚበላው አጥቶ የሚያርስበት በሬውን እርቦት አርዶ ስጋውን ቅርጥፍ አድጎ እንደበላው ገበሬ ከበላ በሃላ ልክ ሆዱ ሲሞላ ቦርጩን አሳብጦ በእጆቹ እያሻሸ ለዚች ብዬ ነው በሬዬን ያረድኩት የሚል ነው ሚመስለው ስንቱን ካደረገ በሃላ ሲያዝን ለተመለከተው።

ተጣጥበው ወደነበሩበት አልጋ ተመለሱ ጃሪ ስላሳለፈችው ጊዜ ብዙ ነገር ታወራለት ጀመረ ናቲ የምታወራውን ሁሉ በተመስጦ ያዳምጣት ነበረ ባሏ ባደረገባት ነገር ከልቡ ተናደደ።

በነገራችን ላይ ናቲ በፍፁም አብሯቸው በነበሩት ሴቶች ላይ ደርቦም ሆነ cheat አድርጎ አያውቅም የፈለገ ቢጠላት እንኳ ያንን ማድረግ ከነውርም ነውር መስሎ ስለሚሰማው እንድትጠላው የቻለውን ሁሉ ያደርጋል ካልሆነም መለያየታቸውን በግልፅ ሲያረጋግጥ ሌላ ሚስት ይጠብሳል እንጂ አሁን አለው አለው እንደሚሉት ወጠጤ ወንዶች አንዷን ይዞ ሌላኛዋ ላይ መስፈር አራዳነት ነው ብሎ አያምንም።

በሜሪም ባወራችው ነገር የመጨረሻ ተስፋ በመቁረጡ መለያየታቸውን በይፋ ስላወጀችበት እንጂ በፍፁም ይህንን ማድረግ ምኞቱ አልነበረም።
ጄሪ የምታወራቸው ነገሮች በጣም ይስቡት ጀመረ ምርጥ ሴት መሆኗን ነገር ግን የማይጠገን ስብራት እንደዳለባት ከምታወራው ነገር በቀላሉ መረዳት ቻለ።

እንክብካቤዋ ልታስደስተው የምታደርጋቸው ነገሮች ስሜቱን ለመረዳት የምትጠይቀው ጥያቄ ብዛት ሲመልስላት መልሱን ተቀብላ እሱን ለማስደሰት የምታደርጋቸው ነገሮች ሲመለከት እናት የሆነች ሚስት ሊወጣት እንደሚችል ልቡ ጠቆም አደረገው። ነገር ግን እሱም እሷም ለመወስለት እንጂ ለትዳር እንዳልተገናኙ ስላሰበ ምንም ባያወራም ከሜሪ ጋር በመገናኘቱ ተስፋ ስለቆረጠ አብሯት ቢሆን ደስ እንደሚለው ሁኔታው ያስታውቃል።

ጄሪም ግራ ገብቷታል በድጋሚ እንዴት ከባሏ ጋር መመለስ እንደምትችል ማሰብ አቅቷታል ልቧ በፍፁም ማድረግ ያለባትን ቁርጡን አልነግርሽ ብሏት ተጨንቃለች።

ጄሪ እንደ ባለምያ ሚስት በጠዋት ተነስታ ወደቤቷ ለመመለስ

ተጣጥባ እራሷን እያሰማመረች ሳለ ናቲ ከእንቅልፉ ነቃ የአልጋ

መውረጀም መሰነባበቻም ይሆነው ይመስለ ሳብ አድርጓት እንዴ ሰፈረባት!! ጨርሰው ስለሚሆኑት ነገር ምንም ሳያወሩ ተያይዘው ወጡ።

መነሀሪያ አስገብቷት እንደ ልጅ እየቦረቀች መኪና ውስጥ ገባች የምታወቃቸው ያገሯ ሰወች አዮኝ አላዩኝ እያለች እየተሳቀቀች ይስማታል እሷም ዞር ዞር ብላ ሰው አለማያቱን አረጋግጣ ሳም ታደርገዋለች። ምንም ስለመጨረሻቸው ሳያወሩ ቻው ተባብለው ተለያዩ። ሁለቱም ግራ ገብቷቸዋል ምንድነው ምንሆነው በቃ ቻው ልንባባል ነው ወይስ ....?
እቤቷ መድረሷን ደውላ አሳወቀችው እንደተለመደው በ fb ማወራታቸውን ቀጠሉ።

※ለምን ባል እና ሚስት አንሆንም

※ እንዴ ባሌን ምን ልለው ነው

※ ያደረግሽውን ንገሪው እና ከዚህ በሃላ አብረሽው እንደማትሆኚ አስረጂው እሱን ፋይል ዝጊ እና አብረን እንሆናለን

※ግን እንዴት ምንገናኘው እሺ አንተ ያለኸው እዛ እኔ ያለሁት እዚ

※እሱን እኔ አመቻቸዋለሁ አንቺ ብቻ ፋይልሽን ዝጊና እናወራለን ስለሌላው እመኝኝ ጥሩ ጥንዶች ይወጣናል

※ እሺ ግን ትንሽ ጊዜ ስጠኝ ?

※ችግር የለውም እሺ

★ከ20 ቀን በሃላ★

ጄሪ እና ናቲ የጦፈ አለም ውስጥ ገብተዋል እሷም ባሏን ሁሉን አሳውቃው ከ ናቲ ጋር ቀጣይ ሂወቷን ለማሳመር ሽር ጉድ ማለት ከጀመረች ቀናት አልፈዋል።

ናቲም በእናትነት ፍቅሯ መሳቡ ፈጣሪ የ ሜሪን ጭካኔ በጄሪ የካሰለት ያህል ደስታን አጎናፅፎታል ሜሪ ጋር የመደወል ሀሳቡ 100% አክትምለታል ነገር ግን ጄሪን ከሜሪ ጋር ያደረገውን ሁሉ አብራው እንደድታደርግ አሳምኗታል እሷም ጉዳቷን አረስታው መልካም የሚባል ትዳር ከፊት እንደሚጠብቃት ጭላንጭል ተስፋ ይታያት ጀምሯል።

የጄሪ የ Entrance ውጤት መጣ እሷም 4ቱ ጓደኞቿም ማለፏን በማረጋገጡ በጣም ደስተኛ ሆኗል የምትምላቸው ግቢዎች እንዳይርቁ ማድረግ ያለባቸውን ያስቡ ጀመረ።

ጄሪ ከ አራቱም ጎደኞቿ ጋር አንድ ግቢ ደረሳት ናቲ ከሚማርበት ግቢም ብዙም ስለማይርቅ በደስታ ሰከረ ግቢ ሲገቡ ለመገናኘት ሁለቱም ቋምጠዋል። ትዳራቸውን አንዴ በስልክ ሲያሻቸው በfb እያወሩ ተነቅሎ እንደበቀለ ጥርስ አጠነከሯት። ★

## ከ 2 ወር በሃላ★

ጄሪ ወደ ግቢ ለመግባት fresh እንደመሆኗ ልብሱን ሻንጣ ሸመታው አድክሟት ወደ ቤቷ ገብታ አረፍ አለች ለ ናቲ ደወለችለት።

※ ሄሌ ጄሪዬ

※ ወዬ ናቲዬ ዛሬ ......ብላ ስሰራ የዋለችውን ነገረችው።

※ አይዞሽ አረፍ በይ በቃ ሳምንት ነው ግቢ የምትገቡት

※ አዎ

※ በቃ ከሳምንት በሃላ ትመጫለሻ ግቢ

※ አዎ ጓደኞቼ ግን አንተን መጥበሴን ከሰሙ ይገሉኛል? እነሱን እቤት ደርሼ ልምጣ ብዬ ነው ሸውጃቸው ምመጣው

※ እሺ ፍቅር ከሜላት ውጪ እስካሁን አልሰሙም አይደል?........ ( ሜላት ቀድማ መሄዷን ብታውቅም ተወራርዳባት ስለነበር ማወቋን መናገር አፍራ ትዳር መጀመራቸውን ያላወቀች አስመስላ ጄሪ በቅርቡ ነበር የነገረቻት ናቲም እንዳላወቀች አስመስላ ስሰማ እንድትደነገጥ አስጠንቅቆ ነግሯት ስለነበር ማስመሰሉን ችላበታለች ሌሎቹ ሶስቱ ግን አያውቁም)

※ አዎ!

※እሺ በሰላም ለመገናኘት ያብቃን!!

※ አሜን የኔ ፍቅር!! ባይ .

# ★ከሁለት ሳምንት በሃላ★

ጄሪ ናቲ ጋር መጣች ሄዶ ከመነሃርያ ተቀበላት ዋው ከወራት በሃሏ ሲያገኛት የሌለ ቆንጅዬ ሆናለች ትንሽነቷ ልጅነቷ ተበልታ የማትጠገብ ምርጥ ሴት ያደርጋታል ልክ ሲያገኛት እቅፍ አድርጎ ሳማት በጣም አይናፋር ከመሆና የተነሳ ሲስማት "ና..ቲቲ ወይኔ አሀሀ ሰው ሲያስፈራ" ምናም ስትል በሳቅ ድክም አለ። እየሳቁ ተያይዘው ወደ ክፍላቸው ገቡ።

እሷም እንደ ሜሪ እንድትሆንለት ስለሚፈልግ ሁሉንም ከሜሪ ጋር የሚያደርገውን ማደረግ ጀመረ። አብሯት ሻውር የወስዳል እቅፍ አድርጎ ይስማታል እቅፍ አድርጎት ነው ሚተኛው በጣም የሚገርም ፍቅር ይሰጣታል። እሷም ከልቧ የሚገርም ፍቅር ትለግሰዋለች ለሱ ደስታ ገደል የምትገባ እናትነቷ በእጅጉ የበዛ ምርጥ ሴት ሆነችለት።

ለመወስለት የተገናኙ ሰዎች የሚያምሩ ጥንዶች ሆኑ ጄሪ ሴክስ ካደረጉ ሃላ ሁሌ በሆዱ አስተኝታው በስሱ በሚያምሩ ለስላሳ ጣቶቿ የምታደርግለት ማሳጅ በእውነቱ ለናቲ ሱስ ሆኖበታል ሙሉ ሎሽኗን እሱን በማሸት ነው የጨረሰችው ቢባል እወነትነቱ የበዛ ነው።

ናቲ እፈልጋለው ብሏት የምችለው ነገር ኖሮ የማታደርግለት ነገር የለም ፍፁም መልካምነቷ አውርቶ መጥገብ አይቻለውም ነገሮችን አታካብድም ቀለል አድርጋ ማየት ልማዷ ነው።

ከዛ በላይ ግን የተቸገረ ሰው ስታይ አንጀቷ ፍፁም አይችልም አንድ እናት መድሀኒት መግዣ አጥተው ሲንከራተቱ ተመልክታ በተላከችበት ብር ለሳቸው መዳኒት ገዝታ እሳቸውን እቤት አድርሳ የምትመለስ አስመሳይ ሳትሆን እውነተኛ መልካም ሴት መሆኗ ናቲ ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ እንዲኖራት እያስቻላት መጥቷል። ናቲ ግቢ ለበአል ሲቀር እንኳ ከዶሮውም ከሚጠጣውም ሸክፋ ይዛለት መምጣቷ ናቲንም በአል በአል እንዲያሰኘው እሄን ማድረጓ ሳይሆን ማሰቧ እንኳ ያስገርመው ከጀመር ቆየት ብሏል።

★ሜሪ★

ናቲ ለልደቷ ከላከላት HBD መልእክት በሃላ አልፎ አልፎ በስልክ ማውራት ጀመረዋል ናቲ ሁሉንም ያለበትን ሁኔታ ስለነገራት ተስፋ ብትቆርጥም ከህመሟ ስላገገመች ግን እውነቱን ነግራው ከሚያሰቃያት ጭንቀት ለመገላገል ወስና ደወለችለት።

※ ናቲ ታምሜ ተስፋ ቆርጬ እኮ ነው የውሸት ያ ሁሉ ወሬ ያወራሁት .......ናቲ fb ላይ የላኩልህን ታምሜ የነበረ ሰአት የተነሳዋቸውን ፎቶዎችእያቸው ካላመንክ .......

ናቲ ድንዝዝ ብሎ ቀረ እያንዳንደዱን ያሳለፈችውን ነገር ስትነግረው እንባውን መቆጣጠር አቃተው ልቡ በሁለት ስሜቶች መሃል ተወጠረች .. ፍቅሯ እንደ አዲስ በጣም በከባድ ሁኔታ አገረሸበት ለሱ ስትል በቻዋን መምት የመረጠችውን ሴት ትቶ መወስለቱ አሳፈረው.......

.

ይቀጥላል

# ክፍል-27

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

ለሱ ስትል ብቻዋን መምት የመረጠችውን ሴት ትቶ መወስለቱ አሳፈረው ነገር ግን ይሄ ሁሉ የመፈጠሩ ምክንያት አለመናገሯ ነበር እና ለምን እንዳልነገረችው እሳት እንደነካው ወተት በንዴት ገንፍሎ ጠየቃት እሷም ለምት የሚያሰጋት ህመም አሟት እንደነበረ አሁን ግን ሙሉ ለሙሉ እንኳ ባይሻላት መልካም ሆኔታ ላይ መሆኗ እውነቱን ለመንገሯ ምክንያት እንደሆናት ስትነግረው ጭራሽ ማሰብ ተሳነው።

እሱም በመደበቋ የተነሳ የተፈጠረውን በምላ አንድ በአንድ ዘክዝኮ ነገራት ነገር ግን እንዳይከፋት በማሰብ ከጄሪ ጋር የጠነከረ ነገር እንሌላቸው ነገር ግን አንድ ሁለቴ አብረው ማደረቸውን ከአሁኗ ሰአት ጀምሮ ግን በፍፁም አጠገባ እንደማይደርስ አበክሮ ነገራት። እሷም ያደረገችው ነገር ምንኛ ከባድ እንደነበረ ስለገባት ሳታቅማማ እሺታዋን ገለፀችለት።

የስልክ ወጋቸውን ካበቁ በሃላ ናቲ በፍፁም ከራሱ ጋር መሆን ተሳነው ተልከዋል ያለችውን ምስሎች ለመመልከት ስልኩን ለማወጣት እጁን ኪሱ ቢከትም እዛው እረስቶት በሃሳቡ ነጎደ "እሷ

ታማ ለዛውም ለምት የሚያሰጋት ህመም እኔ ግን ከየቱ ወንድ ጋር አልጋ ላይ ተኛች ብዬ አስባለሁ  እሷ ሆስፒታል አልጋ ላይ ከጉልኮስ ተጣብቃ በህመም ስትሰቃይብኝ ነበር.. " እያለ እራሱን ወቀሳ ላይ ሳለ አንዱ ጓደኛው ደብተር ይዞ ከዶርም ሲወጣ አይቶት

※ ናቲ..ናቲ..class አገባም እንዴ ..

※ አቦ አልገባም ...

አለ በንዴት ከሀሳቡ እየባነነ ... ፎቶው ትዝ ሲለው ስልኩን አውጥቶ መጎርጎር ጀመረ መልዕክቱ ላይ ያሉትን ፎቶዎች ሲመለከት እሷ አልመስል አለችው። በጣም ከመደንገጡ የተነሳ ፎቶዎቹን ባላየዋቸው አስባለው። ጭራሽ ሌላ ትልቅ ፀፀት ውስጥ ወደቀ እሷ እዛ አልጋ ላይ ሆና ስትሰቃይ እሱ እዚ ምን ሲሰራ እንደነበረ ሲያስበው ከማበድ ያልተናነሰ ጭንቀት ውስጥ ተዘፈቀ። አቀርቅሮ መሬት ሲጭር ለተመለከተው የሚወደው ቤተሰቡን ያጣ እንጂ በሰራው ሀጥያት እራሱን የሚቀጣ ምስኪን አይመስልም።

"ለምን ሜሪዬ ለምን?መስዋትነት እኮ እንዲህ አይደለም የኔ ፍቅር? እኔ እኮ ታመምሽ ቢዬ የምጠላሽ ሰው አይደለሁም? ያኘክሽውን የምካፈልሽ ያኘኩትን የምትካፈይኝን ሴት እንዴት ይጠየፈኛል ብለሽ ማሰብ ቻልሽ?

መስዋት የሆንሽልኝ መስሎሽ ለሁለተኛ ጊዜ እኔኑ መስዋት አደረግሽኝ ሜሪዬ በቁሜ ገደልሽኝ። እንዴት ጤነኛ መሆን ይቻለኛል ከዚህ በሃላ? አንቺን መጥላት ያስችለኝ ይመስል በምላሴም በገላዬም ገደልኩሽ እኮ እንዴት ነው ሚስተካከለው ያ ሁሉ ስህተት በምን ላጺስስ ይደመሰስ ይሆን?

ሜሪዬ እኔ እኮ ክፉ አይደለሁም ለምን እንደ ክፉ ባል ደበቅሽኝ ብሰማ እኮ ከስርሽ አልጠፋም ነበር? ሜሪዬ ሌላ ባል ብለሽ እኮ ነው ናላዬን ያዞርሽው በተማሪነቴ ቀልደሽ እኮ ነው ሁሉን እውነት ያስመሰልሽብኝ ሜሪዬ ገደልሽኝ? " አሟት የተነሳችውን ፎቶዎች እየተመለከተ ትመልስለት ይመስል በጥያቄ ማጣደፉን ቀጠለ።

"በዚህ በኩል ደግሞ በተጨነቀ ጊዜ አብራው ተጨንቃ በከፋው ጊዜ ከስሩ ሳትለየው የሚፈልገውን የምትችለውን ሁሉ የምታደርግለት። ጓደኞቿ ያላቸውን ግንኙነት ከሰሙ በሃላ player ነው ይቅርብሽ ብለው ሲምግቷት እነሱን ትታ ከሱ ጎን በመቆሟ ከነሱ ጋር ያላት ነገር ለሱ ስትል መሻከሩን ያውቃል።

ከዚያም በላይ ግን ለ ሜሪ ያለውን ስሜት ስለምታውቅ እንደማይጎዳት እና ምንም ነገር ቢፈጠር ትቷት ሜሪ ጋር

እንደማይመለስ በሚወደው ሰው ቃል ገብቶላት ነበረ። የፈለገ ነገር ቢሆን እችን እናት የሆነች ሴት እንደ እርካሽ እቃ አውጥህ የመጣል ምራሉ ይኖርሃል?

እንዴትስ የመጀመሪያ ጉዳቷን እያወቅክ ሳለ አንተም እንደቀድምው ባሏ ልቧን ለመስበር አቅሙ ሊኖርህ ይቻልሀል? እንዴት የምትወዳቸው ጓደኞቿ ባንተው የተነሳ ጥርሳቸውን ነክሰውባት አንተን ተማምናብክ ቆማ እሷን አሽቀንጥረህ በሀፍረት ጓደኞቿ መጀመሪያመደ ብለንሽ ነበረ እያሉ እንዲዘባበቱባት ትፈቅዳለህ?" እያለ አንዴ የጄሪ አንዴ የሜሪ ጠበቃ እየሆነ በሁለት በኩል እንደሚጎተት ላስቲክ ህሊናው ተወጥሮ ሊበጠስ ጥቂት ቀርቶታል።

ናቲ ከመቃዠት አልፎ ለትምህርቱ ይሰጠው የነበረውን ትኩረት እያጣ መጣ ፀፀት እና ጭንቀቱ አቆረቆዘው እንኳን እንደ ሜሪ በጣም የሚያፈቅራት እንደ ጄሪ የሚወዳትን ሴትን አይደለም ለማይወዳት ለሰለቸችው ሴት እንኳ ማስቀየም ፍላጎቱ ያልሆነ ሰው ሜሪ ላይ መወሰን በፍፁም አቃተው።

በጣም ቢመረው እንድትጠላው ሌላ ነገር ነው ያሰብከኝ አልፈልግህም ብላ እንደድትተው በማሰብ ከወትሮው በተለየ መልኩ ሊያበሳጫት ሊያናዳት ወሰነ።

በቅርቡ መጥታ ስለሄደች ብር እንደሌላት እያወቀ ካልመጣች ከሌላ ሴት ጋር እንደሚሄድ ሲነግራት እሷም በንዴት ገንፍላ እንዴት ሌላ ሴት ጋር ትሄዳለህ ብላ ኡኡ ብላ እርግፍ አድርጋ እንደምትተወው አስቦ መደወሉን ቀጠለ።

※ ሄሎ ናቲዬ

※ እንዴት ነሽ ነገ መምጣት ትችያለሽ?

※ ምን አለ

※ night እንወጣለን ከጀለሶች ጋር

※ እንዴ ናቲዬ ብር እኮ የለኝም ?

※ የኔ እህት በቃ ከሌላ ሴት ጋር ባድር እንደዳይደብርሽ

※ ማርያምን ብር ስለሌለኝ እኮ ነው

※ ገባኝ እኮ እኔም ማታ ብቻዬን ማደር ስለሚደብረኝ ነው

sorry በቃ ቻው ከቻልሽ ብዬ ነበር የደወልኩት

ብሎ ጆሮዋ ላይ ጠረቀመው። ጄሪ እያለቀሰች ደወለችት።

※ሄሎ

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-28

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

...........

※ ሄሎ

※ ሄሎ ናቲዬ

※ ወዬ ጄሪዬ

※ በቃ ነገ እመጣለሁ አንዷ ጓደኛዬ አበድርሻለሁ ብላኛለች

※ እሺ በቃ በጠዋት ነይ!!

ብሎ ዘጋው.... ናቲ ይህን ያህል የሚፈትን ነገር በሂወቱ አጋጥሞት አያውቅም። ሚስቱ ሆና ሳለ ብር እንደሌላት እያወቀ ከቀረች እንደሚወሰልትባት በግልፅ ተነግሯት እሱን ላለማጣት በ campus ኑሮዋ ላይ በብድር ተጠብሳ ለመምጣት የምትጣደፍ ምርጥ ሴት። ጭራሽ ሊያሸሻት በምከረ ቁጥር የምታደርጋቸው ነገሮች ግፉን እንዳያበዙት ሰጋ!!

" በነገራችን ላይ ስለ ፍቅር ከኔ በላይ ሊያወቅ የሚችል ይኖራል ብዬ በፍፁም አላስብም። ሜሪ ተብሎ ሲጠራ እንኳ ልቤ ውስጥ አንዳች ነገር ሲሰራጭ ይሰማኛል ሜሪ የምታደርጋቸው እያንዳንዷ ነገር እንደ ድሮ ቲቪ ቢዥዥ እያለ ይታየኛል ቀስ እያለ ጠርቶ አይኔ ስር ትመጣለች ናቲዬ ብላ እየሮጠች የተሰቀለ የቡቲክ ጫማ ካልነካሁ ብላ ስትንጠራራ የሰው እቃ ሰብራ ጉድ እንዳታደርገኝ እሷን ለመያዝ ስሯሯጥ...... ጫማዋ ውሃ ነክቶባት አውልቄልህ ባዶ እግሬን ነው ምሄድልህ ስትለኝ የኔ እግር ይላጥ ይመስል በፍፁም አይሆንም እያልኩ ስምግታት ሌላውም ሌላውም ቁልጭ ብሎ ይታየኝ እና አይኔን ስገልጥ ሳጣት እቁነጠነጣለሁ ወለም ዘለም ሳልል እደውልላታለው። ብታምኑም ባታምኑም ሲያማት ሁላ ይታወቀኝ ነበር።

በሀሳብ እናወጋለን በስረአት አጫውታታለሁ እሷም የኔን ስሜት ትጋራለች በአጭሩ ስሟ ብቻ ይህን ያህል ይዞኝ ይነጉዳል። በሀሳብ ይህን ያህል ከሆንኩ በአካል ደግም እራሳችሁ ገምቱት። ነገር ግን የሰራችው ከባድ ስህተት ሀዲዱን እንደሳተ ባቡር እውነተኛነቴን አንገጫግጮ ሊገለብጥብኝ ጥቂት ቀርቶኛል።

በነገራችን ላይ መዋሸት ማለት ለኔ እራስን መስደብ ነው። እራሴን

ለመስደብ ደግሞ እስካሁን ዝግጁ አልነበርኩም ምክንያቱም በራሴ አላፍርም ነበረ ። አሁን ግን እራሴን መስደብ ምጀርበት ሰዐት ላይ ሳልደርስ አልቀረሁም? ውሸታም ያልነበርኩ ልጅ በግድ ውሸታም ለመሆን ዝግጅቴን በመጨረሴ ከልቤ አዝኛለሁ!!

ክፉ ባለ ጋሪ በችግር ጊዜ ሂወቱን ያቀናለት ፈረሱን የሚወደው አዲሱ በመጣለት ጊዜ የድሮ ውለታውን ዘንግቶ አውጥቶ ይጥለዋል በየሜዳው ሲንከራተት የጅብ አራት ይሆናል። እኔ ግን የክፉ ግዜ ባለውለታዬን ውጪ ብዬ ከማባረት እራሷ አልፈልግም ብላ አስክትወጣ እራሴን በውሸት መስደቡን መርጫለሁ።

ለጄሪ ምን ያህል እንደማዝንላት ለሜሪ ነግሪያት እውነተኛው የፍቅር ክምሬን ከምንድ በምሰራው ስራ በማፈሬ እራሴን በውሸት ለመስደብ ወስኛለሁ።" እያለ የምስኪን ህሊናውን አፍ ጭርምት አድርጎ ይዞ መራራ ሃሳቡን እንደ ኮሶ መድሀኒት ይግተዋል።

" አንተ እኮ እንዲህ አልነበርክም ብር እወዳለሁ ብላ የመጣች ሴትን ብር እንደሌለህ ነግረሀት መጥበስ የማይቸግርህ። player ወንድ አለወድም ላለችህ ሴት 10 ሚስት ነበረኝ ብለህ ጅንጀናህን የምትጀምር ሰውዬ ምን ነካህ በራስህ አፈርክሳ? ለምታፈቅራት ሜሪ ሹክ በላት ትረዳሀለች?" ይለዋል ከከፍታ ወድቆ እንደተሰበረ ብርጭቆ 10 ቦታ ከተከፈለው ህሊናው አንዱ።

ናቲ ከዶርሙ ፊት ለፊት ካለችው ጎርባጣ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ በደመቀችው ጨረቃ ፊት ከ 10 አይነት የህሊናው ሀሳቦች ጋር ሙግት ገጥም ጭቅጭቃቸው ወደ እብደት መንገድ እያንደረድረው ሳለ የሜሪ ስልክ ከሀሳቡ አነቃው።

※ ሄሎ

※ ወዬ ሜሪዬ

※ እንዴት አመሸህ

※ አለው እ/ር ይመስገን ....እያለ ከ ወራቶች በፊት ያቆሙትን የረጅም ሰአት የስልክ ወጋቸውን በይፋ ጀመሩት

★ጄሪ★

ደመነብሳ አንድ ነገር እየተፈጠረ እንዳለ ሳይነግራት አልቀረም መደወሏን ተያያዘችው ...

ተይዛል ...አሁንም ደገመች

ተይዟል ..

ተይዟል

ካልመጣሽ ከሌላ ሴት ጋር አድራለሁ ማለቱን አስታውሳ ልታብድ ጥቂት ቀራት ......

.

.

.ይቀጥላል

# ክፍል-29

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

...........ከምከረች ከብዙ ደቂቃዎች በሃላ መስመር ላይ መግባቷን ተመልክቶ ደወለላት።

※ ሄሎ ናቲ

※ ወዬ ጄሪዬ

※ ስልክህ እኮ እረጅም ሰአት ተይዞ ነበር

※ ወንድሜ ደውሎ ...........

መናምን ብሎ የመጀመሪያ አፍ ማሟሻ ውሸቱን ሀ ብሎ ጀመረ። እሷም ተሸናፊ እንደመሆኗ ላለመገፋት ብዙም ሳትከራከረው ስለነገው መገናታቸው አውርተው ተሰነባበቱ።

ናቲ የቆርጥላታል ብሎ ያዘጋጀላት ወጥመድ እራሱን ቢይዘውም አይሆንም ተመለሸ ብሎ ሊያሸማቅቃት ግን አልፈለገም። ከዚያ ይልቅ ሜሪን በአካል እስኪያገኛት ድረስ የጄሪን ነገር መላ ለማለት ወሰነ።

## "ጠዋት"

ሜሪ የተበደረችውን ብሯን ሸክፋ ሲጀምሩ እንደ ሮሚዬ ፍቅርን የለገሳት አሁን ግን እግሩም ልቡም ፍቅር እንደሚሰሩ ባለትዳሮች ወጣ ገባ እያለ ካስቸገራት ወዳጇ ናቲ ጋር በጠዋት ደረሰች።

ያው እንደተለመደው ልበሺ የተባለችውን ለብሳ ተቀቢ የተባለችውን ተቀብታ የሚፈልገውን ገፅታ ተላብሳለች። በነገራችን ላይ የናቲ ሚስት መሆን ለአንድ የደርግ ወታደር እራስን ከመዳር አይተናነስም የሚፈልገውን እንጂ የፈለገ ቢያምርብሽ የምትፈልጊውን አያስለብስሽም የምትፈልጊበት አትሄጂ የምታደርጊው ነገር ሁሉ በሱ ፍቃድ ቢሆንብሽም እመኝኝ ደስ እያለሽ ማድረጉን ትለምጂዋለች። የሚገርመው ምክንያቱን አንቺም አታውቂውም!!

ከመኪናው ወርዳ ከወትሮው በተለየ መልኩ ፊቷ የበሰለ ቲማቲም መስሎ እሱን ጥበቃ ቆማለች። ከጥቂት ደቂቃዎች በሃላ ከፊት ለፊቷ ሲመጣ ተመለከተችው። ናቲ ሰላምታውን ከጥንቱ ምንም ሳያጎል ሰጥቷት ተያይዘው ወደሚይዙት ክፍል አመሩ።

እንደተለመደው ሁሉምነገር ተጠናቀቀ። ጄሪ የትላንት ፍርሀቷን ለማብረድ ይመስል

※ ናቲዬ ዛሬ በመኪና ወደዚህ ስመጣ በመስኮቱ አሻግሬ ስመለከት ትንንሽ ደሳሳ ጎጆዎችን ተመለከትኩ መብራት የላቸው ሱቅ በአከባቢው የለ .....

※ እሺ

※ እዛ ወስደህ እንኳን አግብቼሽ ልኑር ብትለኝ ያለ አንድ ማቅማማት እከተልሀለው

ግራ ገባው እቺ ልጅ ግፋን እንደ ምድር አሸዋ እያበዛችው መሆኑን ሲረዳ መጨከን አማራጭ የሌለው አማራጭ ሆኖ ተሰማው። ያደረገችለትን የዋለችለትን ውለታ ሁሉ እንኪ ብሎ መልሶላት ወደ ድሮ ሰላሙ ቢመለስ ምኞቱ ነበር ግን እንዴት?

የማለው መሀላ እየቆረቆረው ያደረገችለት ነገር እየነዳው አይሆኑ ገደል ውስጥ ገፍትሮት ተሰባብሮ እንዳይምት ቢፈራም መጨከን እንዳለበት ወስኖ ምንም ሳይመልስላት ወሬ ቀየረ።

በነጋታው ጠዋት ላይ ጄሪ ወደምትማርበት ግቢ ጉዞዋን ቀጠለች። በትንሹም ቢሆን ትላንት ከነበረችበት ውጥረት ማገገሟ ፊቷ

ያመላክታል። ነገር ግን ናቲ እየዶለተባት ያለው ሴራ ምኑም አልገባትም ነበር።

★ሜሪ★

ትላንት ስልኩን ዘግቶ ስለነበር በሰላም እንደሆነ ልታረጋግጥ ደወለችለት።

※ ሄሎ ሜሪዬ

※ እንዴት ዋልክልኝ

※ አለሁልሽ እ/ር ይመስገን.... ብሎ የጠፋበትን ምክንያት ትላንት ለጄሪ መዋሸት በጀመረበት አንደበቱ የባጥ የቆጡን ዘላበደ። ከ ሜሪ ጋር ያለው ነገር ሙሉ ለሙሉ እንደድሮው ተመልሷል ማለት በሚቻልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

እንደ ድሮው ምንም እንዳለተፈጠረ ማውጋታቸውን ቢቀጥሉም በተመሳሳይ ሰአት ከጄሪ ጋር የሚደውሉት ነገር 50 አይነት ውሸት እንዲያወራ ምክንያት ሆኖታል።

ከሜሪ ጋር በዚህ ወር መጨረሻ ለመገናኘት ቀጠሮ በመያዛቸው

የጄሪን ነገር ከመቼውም በላይ ማጦዝ ግድ ሆኖበታል።

**#ከሳምንት በሃላ**

ናቲ ከሜሪም ከጄሪም ጋር እየተጓዘ ያለው ጉዞ ሁለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ዛፍ ላይ የመውጣት ያህል ከብዶታል። ለዚያም ይመስላል አይሆኑ ነገር እየጠየቃት ይረብሻት የጀመረው።

※ አቦ ሱፋን ብር አጠፋሁት  ለመጽሄት ፕሮግራም ቶሎ ካልገዛው ደግሞ የሌለ አዛ ነው ምሆነው

※ ለምን እቤት አትነግራቸውም

※ እንዴ ድጋሚ የሱፍ ብየ ነው የምጠይቀው ተቀብዬ ነበር እያልኩሽ እኮ ነው

※ እና ምን ይሻላል እረ ናቲ በፈጣሪ

※ ካልደበረሽ ከሜሪ ልቀበላት በጣም ያስፈልገኛል

※ እረ ናቲ ተው በጌታ

※ ምንም ማድረግ አልችልም......ብሎ ዘጋው

ናቲ ሜሪን ልጠይቃት ነው ያላት አንደኛ ሜሪ እራሷ የምፈልገውን አይነት ሱፍ በራሴ ምርጫ አሰፋልሀለው ብላ የገባችለት ቃል ትዝ ብሎት ሲሆን ዋናው ነገር ግን ከ ሜሪ ጋር ማውራት መጀመራቸውን ፍንጭ ሰጥቷት ተናዳ እንድተወው ቢሆንም ይሄም አልተሳካም።

ትንሽ ተዘጋግተው ከሳምንት በሃላ

※ ሄሎ ናቲ

※ በጣም ልቤን ታምሚያለው ብዙ ብር ያስፈልግሀል ተብያለሁ። አሁን እንደ ሱፋ ምቀልድበት ጊዜ ላይ አይደለሁም አማራጭ ስላጣው እንዳይደብርሽ ምንም ባደርግ?

※ እረ እቤት ለምን አጠይቃቸውም

※ በጣም ከባድ ደረጃ ላይ ደርሷል ስለተባልኩ ይደነገጥሉ እሱ በፍፁም አይሆንም እንካ ብላ አትሰጠው ነገር እጇ ላይ ምንም የለም ዝም አትለው ነገር ትወደዋለች ግራ የገባው ነገር ውስጥ ገባች። በጠዋት ተነስታ አሪፍ የተባለ ሆስፒታል መች እንደሚሰሩ ያለውን ነገር አጣርታ ተመለሰች።

ናቲ ይሄ ብር ወዳድ ሰው ለብር ሲል ገደል ይገባል ብላ ተወችኝ ብሎ አስቦ ሳይጨርስ ስልኩ ጠራ ጄሪ ነበረች ።

※ ሄሎ

※ ወዬ ጄሪ

※ ዛሬ ኮሪያዎች የሚሰሩበት የልብ ብቻ ሆስፒታል ሄጄ ሁሉንም ነገር አጣርቼ ነው የመጣሁት ማክሰኞ እና ሀሙስ ብቻ ነው ሚሰሩት ብር ሳገኝ መተህ ትታከማለህ እሺ በቅርብ አገኛለሁ?

ናቲ ኡኡ ብሎ ቢጮህ ምኞቱ ነው። ያልታመመ ልቡን አመመኝ ብሏት ልታስታምመው ፈልጋ ብር አጥታ ደፋ ቀና ስትል ማየት ከማበድም በላይ ሆነበት።

አሁን ግን የመጨረሻ ጥግ ላይ ደርሷል ምክንያቱም ከሚያፈቅራት ሜሪ ጋር ሊገናኝ ሳምንት ብቻ ቀርቶታል።

እሱ ባሰበበት መንገድ በፍፁም ሊሆን ስላልቻለ ከሜሪ ጋር ሊመለስ መሆኑን እውነቱን አፍርጦት እሱ የተሸከመውን ጭንቀት

እሷ ላይ አራግፎ እራሱን ነፃ ለማውጣት ወሰነ!!

መሪ ልትመጣ 1# ቀን ቀራት ናቲ የበፊት እውነተኛ ፍቅሩን እንደገና የሚያጥምበት ሰአት በመድረሱ የእዳ ሸክሙን ለምስኪና ጄሪ አሸክሟት ከሷ አለም እስከወድያኛው ሊወጣ ከመጨረሻው ውሳኔው ላይ በመድረሱ ስልኩን አውጥቶ ጄሪ ጋር መደወል ጀመረ ..

※ ሄሎ ናቲ

.

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-30

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

※ ሄሎ ናቲ

※ ወዬ ጄሪ ሰላም ነው

※ አለሁ እ/ር ይመስገን እንዴት ነህ

※ አለሁልሽ ከሜሪ ጋር ስለታረቅን ነገ ላገኛት ነው በፍፁም እንዳትደውልኝ txt እንዳልኪልኝ ከዚህ በሃላ

※ ምን

※ ሰምተሻል

※ ናቲ እየቀለድኩ ነው በለኝ

※ ጌታን እውነቴን ነው

የሰማቸውን በፍፁም ማመን ተሳናት ምንም ስላልጠበቀችው ቢያበሳጫትም መልሳ ከመደወል ዋጥ አድርጋ ለትችለው ምከረች። ወዲያው profile ላይ "20$ ነበረኝ ያለኝን ሙሉ 20$ ሰጠሁህ እሷ

500$ ነበራት 100$ ካላት ቀንሳ ሰጠችህ ከኔ የተሻለ ስለሰጠችህ ከኔ በላይ የምትወድህ መስሎክ ተውከኝ" የሚል ሀሳብ የያዘ ፅሁፍ አሰፈረች።

ፅሁፉን ሲመለከት የሌለ ደበረው ለፍቅር ብሎ እንጂ ለብር አለመሆኑን ሊያስረዳት ፈልጎ ሌላ እዳ ውስጥ እንዳይገባ በማሰብ ባላየ ችላ ብሎ ተዋት።

#**ጠዋት**

☎ሜሪ ደወለችለት

※ ሄሎ ሜሪዬ

※ ወዬ ናቲዬ

※ እንዴት አደርሽልኝ

※ አለሁልህ እየመጣው ነው በቃ አንተም ተነስ

※ እሺ ከትንሽ ደቂቃ በሃላ እወጣለሁ

※ እሺ ቻው

※ ቻው

የመጀመሪያ ቀን የአዳር ትውስታቸውን ለመመለስ ይመስል ሜሪ እዛው ክፍል እንዲያድሩ በጠየቀችው መሰረት ናቲ ያ ክፍል እንዳይዝ በጠዋቱ ከበራቸው ውሏል። ወደ ውስጥ ገብቶ ክፍሉ እንዳልተያዘ ለማረጋገጥ የክፍል አከራዩዋን ቢጠይቃት ለሶስት ቀናት ቀድም መያዙን ሲሰማ ቢበሳጭም ምንም ማድረግ ስላልሆነለት ከጎን ያለውን ክፍል ለመያዝ ተገደደ።

ናቲ ክፍሉን ከያዘ በሃላ እስክትመጣ ወጣ ብሎ ዞር ዞር ለማለት ቢያስብም እግር ልቡን ተከትሎ ስጦታ መስጠት እንደለመደ ሰው ወደ ስጦታ ሱቅ ቢያመራበት ግርምትን ጫረበት። በነገራችን ላይ ናቲ በሂወቱ ለየቷም ሴት ስጦታ አበርክቶላት አያውቅም መገረሙም ለዛ ሳይሆን አልቀረም።

ሲመለከት ካያቸው ስጦታዎች ሁሉ የፍቅር ሂወታቸው ሰምሮላቸው የትዳር ህይወታቸውን ለማጣጣም ከሚጣደፉት በልብ ቅርፅ በተዘጋው መስታወት ውስጥ ቁልጭ ቁልጭ ከሚሉት ሙሽሮች ላይ አይኑን መንቀል ተሳነው። ከሜሪም ጋር ያለው ህይወቱ በትዳር

የሚታሰርበት ቀን ቢናፍቀው ይህን ስጦታ የመጀመሪያው አድርጎ አበርክቶላት ስጦታ ያለመስጠት ድንግልናውን ለማጣት ወሰነ።

የተጠቀለለውን ስጦታ ይዞ ወደ ያዘው ክፍል አመራ። ሜሪ በጣም ብትቆይበት ጊዜ ደጋግም እየደወለ የደረሰችበትን እንድታሳውቀው ይነዘንዛታል እሷም አጠገቧ የተቀመጡትን ትልቅ ሰውዬ እየጠየቀች ማሳወቋን ቀጠለች።

ከ 4 ሰአታት ቆይታ በሃላ መድረሷን ስታሳውቀው እንደሰከረ ሰው እግሩን እያማታ መነሀሪያ ደረሰ። ልክ ሲያያት አመል እንዳለው በግ ሲንደረደር ሊወጋት እንጂ ሊስማት በፍፁም አይመስልም ነበር። አጠገቧ ሲደርስ ግን መንርደሩን ገታ አድርጎ እንደፋርማሲ እባብ ጥምጥም ብሎባት ከንፈሮቿን ያ ሁሉ ህዝብ መሃል ሲስማት ለተመለከተ ፖሪስ እንጂ ሳሪስ አልመስልህ ቢለው አትፍረዱበት። ሰውን ከጤፍ እንኳ ሳይቆጥሩ እየተመናቀሩ ወደ ክፍላቸው አመሩ።

እውነቱን ለመናገር ወደፊትም ወደሃላም በሜሪ የሚደሰተውን ያሀህል በየቷም ሴት ሊደሰት አለመቻሉን ልቡ ይነግረዋል። በቃ ትክክለኛ ግጣሙ እሷ እና እሷ ብቻ ናት።

ይኸው አላልኳችሁም በሩን ከፍቶት ገባ ማን ይቆልፈው ተጣብቀው

መላላሳቸውን ቀጠሉ። ሜሪን እየሳመ ሲታገላት በሩን ስትታከክ ጓጓ ብሎ ተዘጋ። ከንፈሯን ክፉኛ ይመጠምጠው ይዟል ፊቷ ፍም ገላዋ በሱ ተረበው ልብሷን ታወላልቅ ጀመር። ልብሷን አውልቃ ስጨርስ አልጋው ላይ በጀርባዋ ተንጋላ ተኛችለት ደስ በሚል ሁኔታ ሁሉም ተጠናቀቀ።

ብዙ አመት ከsex እንደራቀ ሰው ከሜሪ ብቻ የሚያገኘውን የደስታ ጫፍ ከብዙ ወራት በሃላ ዛሬ አጣጣመው በፍፁም ከሷ ሌላ ሰው ይህን ማደረግ አይቻለውም ለምን እንደሆነ ግን እሱም አያውቀውም። እሷም ጨርሳ ተቃቅፈው ጋደም አሉ።

ስጦታውን ካበረከተላት በሃላ ሜሪ መጋረጃውን ጋርዳ ጭልምልመም አድርጋው በሻማ ብረሀን ወይናቸውን እየተጎነጩ መሳሳማቸውን ቀጠሉ። በዛ ደብዛዛ ብረሃን ሲመለከታት ቁጭ አድርጎት መጠጣቱ በፍፁም አልሆንልህ አለው ደገሙ ...አሁንም ....አሁንም ... ከወይኑ ድካሙ አስክሯቸው ድፍት ብለው ተኙ።

ጠዋት ሁሌ እንደተለመደው አከራዬቹ ሲደበድቡ ልብሳቸውን ለባብሰው እየተጣደፉ ወጡ።

ቁርሳቸውን አዘው ከአንዷ ምግብ ቤት ቁጭ እንዳሉ ሜሪ ስላለፈው

ጊዜ ታወጋለት ጀመር። ስራ ከጀመረች ወዲህ ብዙ ብር አጠራቅማ እንደነበር ነገር ግን አሁን በማየረባ ነገር ጨርሳው ጥቂት ብር እጇ ላይ እንደቀራት ስትነግረው ናቲ  የታዘዘውን ምግብ እንኳ ለመጠበቅ አቅም አጣ እሷም እንዲህ አዝኖ ስታየው የመጀመሪያዋ ስለነበር ደነገጠች።

የታዘዘውን ምግብ ጥሎ ትቷት ወጣ እንዲ ያስከፋዋል ብላ ባለማሰቧ በመገረም ተከተለችው።  ለዚህ ንዴቱ ምክንያቱ ደግሞ ከ 7 ወር በፊት ያሳለፋት ከባድ ጊዜ ነበረች።

**#ከ7_ወር_በፊት**

ሜሪ ስራ የሚባል አልነበራትም እሱም እንዳሁኑ ተማሪ ነው። ያኔ ታገኘው የነበረው ብር ናቲ በማያውቀው መንገድ ተቋረጠ። እንደዛ አገር አቋርጣ እንዳልመጣች አሁን ግን ለ apparent መጥቶ አፍንጫዋ ስር ሆኖ መገናኘት አቃታቸው።

የ apparent ብር ሲገባለት ሮጦ አግኝቷት ይመለሳለ በተረፈ ቅርብ ለቅርብ ሆነው መተያየቱ አልሆንላቹ አላቸው።

ሜሪ ከቤት መውጣት ካቆመች ወዲህ ናቲም ጓደኞቹን እንኳን

ማግኘት አቁም የሚስቱን ፈለግ ተከትሎ እቤት መዋል ሆኗል ስራው።

ምክንያቱ ደግም ከሁለት አንዱ በጠዋት የተነሳው የተኛውን ሰው ደውሎ ይቀሰቅሳል። በስልክ እረጅም ወሬ ማውራት ግን ፈፅም የተከለከለ ነው ምክንያቱም ነገን ካርድ ጠፍቶ ላለመዘጋጋት ሁለቱም ምኞታቸው ስለነበረ በዛ ላይ ሁለቱም እቤት መጠየቅ አይወዱም።

ቀድም የተነሳው ልክ ስልኩ ሲነሳ

※ FB ግባ ግባ .....

※ Fb ግቢ ግቢ ...ከዛ ጥርቅም

ሄሎ ሄሎ ብሎ ወሬ ማንዛዛት በሁለቱም ወገን ፈፅም የተከለከለ ነው።

የመቀደስ ተራ እንደወጣበት ቄስ በጠዋት ተነስተው የጀመሩትን ወሬ ማታ ሜሪ እንቅልፍ ሲጥላት ነው የሚያቆሙት።

**ቁርስ – በ FB**

※ ናቲዬ ቁርስ እንብላ

※ እሺ ቆይ ትንሽ ጠብቂኝ አልደረሰም

※ እሺ እጠብቅሀለው ልክደነው አአ
※ አዎ የኔ ቡችላ

※ ደርሷል ቡቹ ታጠቢና ነይ

※ እሺ 30 sec

※ አልመጣሽም , አንቺ ሜሪ , ማንን እየጀነጀንሽ ነው ,ዋዋ ግን

※ አለሁ አለሁ

※ እሺ ቶሎ በይ እንጀምር

※ ጀምር እሺ

※ የተባረከ ይሆን..... ቀድም ያለ የዛሬ የቁርስ አሸናፊ ነው። ቁርስ በስረአት መብላቷን ሲቀርብላት ፎቶ አንስታ የምግቡን ብዛት ስጨርስ ባዶ ሳህኑን አንስታ መጨረሷን ማረጋገጥ የእለት እለት ተግባሩ ነበር።

ቁርስ:ምሳ እና እራት ሁሌ በዚህ መልኩ ይበላሉ። የተረፈውን ሰአት ያለ ምንም ማቋረጥ በማውራት ያሳልፋሉ ለተመለከታቸው ወሬ አያልቅባችውም እንዴ ያሰኛል። ሁለቱም በስልክ መጎርጎር ብዛት አይናቸውን እስከመታመም ደርሶ ነበር።

3 ወር ሙሉ ማጣትን እንዲህ ተሻግረው ሳለ ሜሪ ከዛ ጊዜ ባለመማሯ ነበር በጣም የተናደደው።

ናቲ ናቲ ብትለውም ፊቱን ሳይመልስ

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-31

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

.......የሷ ብር ላይ ሼር ያለው ይመስል ብሯን ያለአግባቡ ለምን አጠፋች ብሎ መልጎምጎም ምን ይሉታል። እሷ ፈቅዳ ባጠፋችውስ ብር ምን ያበሳጨዋል? እጭ አሁንስ በዛ እወቁልኝ እወቁልኝ አበዛ ፍቅራቸው ያሰኛል ለተመለከታቸው።

ሮጣ ተከትላ አስቆመችው አይኑ በርበሬ መስሏል በንዴት ጨሶ።

※ እንዴ ምን ሆነክ ነው

※ አንቺ ግን ጤነኛ ነሽ

※ ምነው ምን አደረኩ?

※ ያኔ የሆንሺው ጠፍቶሽ ነው

※ አይደለም እሺ ይቅርታ

※ አሁን ዝም በይ ከዚህ በሃላ ግን በስረአት ታስቀምጫለሽ ስታስገቢ txt'ን ትልኪልኛለሽ

※ እሺ የኔ ፍቅር ከዚህ በሃላ በስረአት አስቀምጣለሁ ጌታን!!

በነገራችን ላይ በተገናኙ ቁጥር ብዙውን ወጪ ምታወጣው ሜሪ ነበረች። ምክንያቱ ደግም እሷ ስራ መያዝዋ እሱ ተማሪ መሆኑ ነበር። የሷን ብር ማውጣት ከምንም አይቆጥረውም እንደራሱ ነው የሚያያት ቢኖረው ለሷ የሚያደርገው ነገር ስለሆነ ስላላት ማድረጓ አያስደንቀውም። እሷም ልካለት አመሰግናለሁ ሲላት እንኳን በጣም ነው የምትበሳጨው። 1000 ብር በቀኝ ኪስህ ቢኖርህ እና 500ውን በቀኝ 500ውን በግራ ኪስህ ብታስቀምጥ ምን የተለየ ስሜት ይሰማሀል? ለናቲም የ ሜሪ ብር መላክ ከቀኝ ኪሱ አውጥቶ ወደ ግራ ኪሱ እንደመክተት ነው ስሜቱ ምክንያቱም እሷ ማለት እሱ ማለት እሷ ነን ብለው ያስቡ ስለነበር።

በነገራችን ላይ የኔ ሜሪ ሀብታም ለማግባት አሳራቸውን ከሚበሉ ሴቶች መሃል አለመሆኗ በጣም ያኮራኛል። ለምን ሀብታም አታገቢም ብሎ ለጠየቃት ግን ...

"አስቲ አስቡት ወሬው የሚያደርገው ነገር በሙሉ ግራ የገባው ሰውዬ ለብሩ ብለሽ የምታፈቀሪውን ትተሽ አግብተሽው ገባሽ እንበል። ከገባሽ ከሳምንት በሃላ ሶፋሽ ላይ ተጋድመሽ tv ትጎረጉርያለሽ እሱ ከያዛት ላፕ ቶፕ ጋር በስራ ተጠምዶ ፍቅሩን

ይሰራል። እሱነን አፍጦ

መመልከቱ ቢመርሽ አትጨርስም እንዷ ኤጭ ብለሽ ወደመኝታ ክፍል እየተመናቀርሽ ትገቢያለሽ። የጋለ ሰውነቱን ሲመለከት እሱን ለማብረድ ከተኛሽ መቀስቀሱ መከራ ስለሚሆንበት ተከትሎሽ ይመጣል።

ካንቺ ጋር መሳሳም መላፋቱ ሰአት መግደል መስሎ ስለሚሰማው እንደ ጁስ መምቻ ማሽን ሶኬቱን አውጥቶ ይሰካብሻል ተሽከርክሮብሽ ሲያበቃ ያንቺ መጨረስ ግድ ሳይሰጠው ትቶሽ ወደ ስራው ይመለሳል።

እህቴ አንቺ ማለት ለሱ ከቆመው ፍሪጅ በምንም አትሻይም። ፍሪጁ የምቀ ውሃውን አንቺ ደግሞ የጋለ ስሜቱን ማቀዝቀዝ ብቻ ይሆናል ስራቹ። ክፍልሽ እንዳለገባች ሴት ትራስሽን ታቅፈሽ የጎረቤቶችሽን የፍቅር ጫጫታ እየኮመኮምሽ ስታነቢ ታድርያለሽ የድሮ ባሌ ቢሆን የጎረቤቶቼን ሳቅ እኔ በሳቅኩት ነበር ያሰኝሻል።

ጠዋት ደልቶት እንዳደረ ሰው መኪናሽን እያሽከረከርሽ ወደ ስራ ለሚያይሽ ደስተኛ ብትመስይም ለራስሽ ግን ደንኳን ጥለሽ ብታለቅሺ ስሜትሽ ነው። በአመቱ የምትኮሪበት እቤት እና መኪና በባንክ እዳ መወረሱን ያረዱሻል። የመጣሽለት ብር ጥሎሽ ሲበር ጥለሽ

የመጣሽው ፍቅር ያንገበግብሻል ተስፋ ስትቆርጪ ከአዲሷ ደሳሳዋ

ቤትሽ የቆርቆሮ ማገር ላይ ገመድሽን ጣል አድርገሽ አንገትሽን ልታጣብቂባት ትጣደፊያለሽ። ስትንጠለጠይባት ስትታገይ አልችል ብላ የቆርቆሮ ክምር ዝርግፍ ብሎ ይደፋሻል። እመኚኝ እህቴ ቆርቆሮዋን መኪና ተከትለሽ ከቆርቆሮ ስር ትቀሪያለሽ" ብላ መምከር ልማዷ ነበረ። በዚህ ሀሳብ ሁለቱም ስለሚስማሙ ለጊዜው ትኩረታቸው ውዱ ፍቅር ላይ ነው።

★★★★★★★★★★★★

የሚጓዙበት መንገድ እሩቅ በመሆኑ ናቲ እራሱን አረጋግቶ ምግባቸውን በልተው አ.አ አድርሷት ሊመለስ መኪና ተሳፍረው ጉዞዋቸውን ቀጠሉ። ከረጅም የመኪና ጉዞ በሃላ ማታ 1 ሰአት አከባቢ አ.አ ደረሱ። ከድካማቸው የተነሳ እንደማይነካኩ ሲለፈልፉ ቢመጡም ክፍል ውስጥ ሲገቡ ናቲ እኔ በበኩሌ አልደከመኝም ብሎ ሀሳቡን አነሳ እሷም እኔም ልልህ ስል አላለችም ... እነዚህ ሰዎች ሳምንት አብረው ቢቆዩ መተላለቃቸው አይቀርም ያሰኛል እንደ አዲስ ተባባሉት ተባባሉት ድቅቅ ብለው ተኙ።

ጠዋት እንደለመዱት አረፋፍደው ወጡ ቁርሳቸውን በላ በላ አድርገው ናቲን ወደ ግቢ አሳፍራው ወደ ቤቷ ተመለሰች።

ናቲ ና ሜሪ እየተገናኙ ጊዜ ማሳለፍ ቢጀምሩም የድሮው በናቲ ላይ የነበራት እምነት ግን ፍፁም ከሷ ጋር አልነበረም። እንደ white board ዳስተር የያዘ ሁሉ ሀሳቧን ያጠፋዋል parker የያዘ ሁሉ ያሰፈረባትን ሀሳብ ማመን ጀምራለች። በአንድ ሀሳብ ላይ ቡዙ አቋም መያዝ መጀመሯ ናቲን ከወትሮው በተለየ ያወዛገበው ጀምሯል።

እየቆዩ ስለሚገናኙ በጣም በተደጋጋሚ sex አድርገው አሟት ስትመለስ። ለአንድ ሰው የሆነችውን ስትናገር

※ አየሽ ከአንቺ ሌላ ሴት ጋር አይሄድም ማለት ለዛ እኮ ነው የወሩን በአንዴ ሚወጣብሽ ምርጥ ባል ነው ያለሽ ያሏት ቀን አቤት ፍቅራችን ደስ የሚል ወሬ አውርተን በሰላም እናድራለን።

አንዱ ጠማማ መቶ ደግሞ ሌላ ነገር ያሳስባታል

※ ቢያፈቅርሽ እኮ አቻኩሎ ክፍል አያስገባሽም በዛ ላይ ይሄ ሁሉ ጊዜ ማድረግ ምን ይሉታል ኢሄ ለ sex ብቻ ነው ሚፈልግሽ በፍፁም አያፈቅርሽም ይሏታል። ትላንት ያስደሰታት ነገር ምኑም ሳይለወጥ ዛሬ ደም ተከፍታበት ትመጣለች። በቃ የዚን ቀን ፍቅራችን ደፍርሶ ተኮራርፈን ቀናት ያልፋሉ። ልመናዬ ሁሉ ጥሩ መካሪ

ያጋጥማት ከሆነ ቀናት አልፈዋል።

እረዳታለሁ የኔ ሜሪ እንዲህ አልነበረችም እንዲህ ያደረኳት እኔው እራሴ ነኝ የሚከፈለውን መስዋትነት ሁሉ ከፍዬ ወደ ድሮው እምነቷ ልመልሳት ጉዞዬን ብጀምርም ነገሮች እየከረሩ በመሄዳቸው ፍፁም ማስተካከል ተስኖኛል።

ለቀልድ እንኳ የተናገርኳት ነገር 80 ቦታ ተሰንጥቆ መዘዝ ይዞብኝ ይመጣ ጀመር። የሷም የኔም ፍቅር ከመጠን በላይ መሆኑን ያየን ሁሉ ቢያወቅም ድሮ ያለመደብንን 2 ቀን ሰላም 3 ቀን መዘጋጋት ልማዳችን ሆኗል ።

ጄሪን ያደረኳት ነገር የማልኩት መሃላ አስሮ እየገረፈኝ መሆኑን ካመንኩ ቀናት ቢያልፉም ስላደረኳት ነገር ይቅር በይኝ ብሎ ከዚህ ሁሉ ጊዜ በሀላ መደወሉ ፈጣጣነት መስሎኝ ስለተሰማኝ ትቼው ነበር። አሁን ግን ምንም ከባድ ቢሆንም ይቅርታ መጠየቅ ቢያንስባት እንጂ አይበዛባትም ብዬ በማሰቤ ስልኬን አንስቼ መደወሉን ተያያዝኩት።

※ ሄሎ

.

ይቀጥላል

# ክፍል-32

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

※ ሄሎ ናቲ

※ እንዴት ነሽ ጄሪዬ

※ አለው እ/ር ይመስገን ምን እሆናለሁ

※ ምንም አትሁኝብኝ። እኔ ግን life በጣም አይሆኑ ነገር እየሆነብኝ ነው። በጣም ከምታስቢው በላይ እየተረበሽኩ ነው። አንቺን ማስከፋቴ ምዬ መካዴ ሁሉ ተደርቦብኝ በጣም ተረብሻለሁ!! እባክሽን ስለ ሁሉም ነገር ይቅርታ አድርጊልኝ

※ ናቲ እኔ ይቅርታ አርጌልሀለሁ ብዬ ልዋሽህ እችላለሁ ግን እመነኝ ከልቤ በፍፁም ይቅር ልልህ አልችልም!! 3 አመት አብሮኝ ከኖረው ባሌ አንተ በ5 ወር ወስጥ ያደረከኝ ይብሳል። ናቲ አንተን በፍፁም ይቀር ልልህ አልችልም!!

※ ሰው የ እናቱን ገዳይ እንኳ ይቅር ይል የለ እንዴ?

※ ናቲ ዛሬ ይምታል የቅር ካላልሸው ብባል እንኳን አላደርገውም!!

※ ቢያንስ በደንብ አስቢበት

※ ምንም የማስበው ነገር የለም በፍፁም ይቅር ልልህ አልችልም አትደውል ከቻልክ?

ናቲ የጄሪ መልስ ካደረጋት ነገር አንፃር ቢያንስበት እንጂ አይበዛባትም እንደውም ያንን ሁሉ አድርጓት አንድም ክፉ ነገር አለመናገሯን እጅግ በጣም እንዲያከብራት አድርጎታል። ይቅርታዋን ባለማግኘቱ ግን መከፋቱ አልቀረም።

ሆሆ ሰው የዘራውን ያጭዳል ሲባል ሽንት እንዳሸተተ በግ እኝ ብዬ እንዳልሳቅኩ ዛሬ … የናቅኩት ክፋቴ እንደ ዳዊት ግንባሬን ብሎ ሊጥለኝ መሆኑን ሳስበው እውነትም የዘሩትን..... አሰኝቶኛል።

★ሜሪ★

ከሜሪ ጋር ያለን ነገር እንደተለመደው አወዛጋቢ ሆኖ ቀጥሏል። የምትፈልገውን ሁሉ በኩርፊያ ለማግኘት መምከሯ የእለት እለት

ተግባሯ መሆን ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል።

※ ናቲ ካፌ እንቀመጥ

※ እረ እኔ እኮ በጣም ነው ሚደብረኝ

※ ለነገሩ አንተ እኮ ከኔ ጋር ......

ሳትጨርሰው "እሺ እንቀመጥ" ይላታል አለበለዚያ የሚጀመረው ጦርነት እንኳን በናቲ አቅም በመከላከያ ጣልቃ ገብነት እንኳ መብረድ የሚቻለው እንዳልሆነ ልቡ ያውቀዋል። ምን አለፋቹ ናቲሻ ድሮ ደረቱን ነፍቶ ከጠዋት እስከማታ የራሱን ፍላጎት ብቻ ሲከተል እንዳልኖረ ዛሬ ባጠፋው ከባድ ጥፋት የተነሳ የተባለውን ሁሉ ለማድረግ " ለነገሩ ...." ማለት ብቻ በቂ ነው።

ይኸው ካፌ መቀመጥ የማይወደው ልጅ በአለቃው ምክንያት መዋያቸው ከሆነ ቆይቷል። በፍፁም እንዲከፋት ስለማይፈልግ እንደወሰለተባት እንዳታስብ የሚኖርለትን ክብሩን ጭምር ጣል አድርጎ የምትፈልገውን ሁሉ በማድረግ ተጠምዷል።

ይህን ያህልም ተቀይሬላት እንደምወዳት ለማሳመን በቂ አልነበረም። አሁንም ጄሪ ጋር የሄድኩት መወስለት አምሮኝ እንደሆነ በማሰብ

የጥያቄ ናዳ ታወርድብኛለች።

※ የምትወደኝ ቢሆን 10 አመት ቢፈጅም ትጠብቀኝ ነበር

※ ሜሪዬ ለስራ አሜሪካ ልሄድ ነው እኮ አይደለም ያልሽኝ? ላገባ ነው ተወኝ ብለሺኝ ምን ተስፋ አርጌ ነው ልጠብቅሽ የምችለው?

※ ቢሆንም ..........

በሂወቴ እንደ ጭቅጭቅ እና ልምምጥ የምጠላው ነገር በፍፁም ኖሮ አያውቅም። ሜሪን እንዳፈቀርኳት በጣም የሚገባኝም ጭቅጭቋን ከመቻሌ ባሻገር ስታኮርፍ እስከ ጥግ ድረስ የምለማመጣት ነገር ኦኦኦ.... እውነትም ላፈቀሩት ሰው እያስባለኝ መጥቷል።

በዚህ ሳመልጥ በዚያ በዚህ ስሮጥ በወዲያ እየመለሰችኝ እሷም ማኩረፏ ላይ እኔም አዲሱ በሀሪዬ መለማመጤ ላይ ተጣብቄ እዚህ ደርሰናል። በጣም እንደምትወደኝ የእውነት ሁሉም ነገሯ ምስክር ነው ቅንጣት እንኳ በፍቅሯ ጥርጣሬ የለኝም ግን ምን ዋጋ አለው የዋህነቷ የመከራትን ሁላ መስማቷ እኔን ለመከራ ሰጥቶኝ እሷንም በጥርጣሬ እንድትቃጠል አድርጓታል።

ነገ በአካል ለመገናኘት ተቀጣጥረን ሁለታችንም ለመገናኘት ልባችን ቆሟል።

☎ሜሪ.....

※ ሄሎ ሜሪዬ

※ ወዬ ናቲዬ

※ ነገ ስንት ሰአት ነው የምትመጣው?

※ በጠዋት ነዋ

※ እሺ የኔ ፍቅር ፀጉር ቤት ልሂድ በቃ ቻው ቻው...

እጅግ በጣም ደስ ብሏታል ለነገሩ በስልክ ከምናወራው ይልቅ በአካል ለማስረዳቱም ለምኑም ይሻላል።

# ★ጠዋት★

ናቲ ከመድረሱ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ደውሎ አሳውቋት ስለነበር ብዙም ሳትዘገይ ያለበት ቦታ ደረሰች። የሌለ እምር ብሎባታል ልክ ናቲን ስታየው የምትሆነው የሆነ ነገር አለ እሱ ብቻ የሚረዳው። መርበትበት አይሉት መደናገር መበርገግ አይሉት..... ብቻ ናቲ ይሄን ስሜቷን ይወደዋል ሳይሆን ያመልከዋል ቢባል ይቀላል። አይን አይኗን እያያት እንቅ አርጎ ከንፈሯን ግምጥ አደርጓ ሳማት እየተላፉ የባጥ የቆጡን እያወሩ ወደሚይዙት ክፍል አመሩ።

ከመንገድ እንደመምጣቱ ሻውር ለመውሰድ እየተጣደፈ ገባ። ተጣጥቦ ሲመለስ ሜሪ አልጋ ላይ ተቀምጣ ሲያያት ትግስቱን አጣ ዘሎ እንደመዥገር እላይዋ ላይ ተጣበቀባት። እንደተለመደው ሁሉንም ነገር ካደረጉ በሃላ ተያይዘው ከክፍሉ ወጡ።

ጠዋት የወጡ በሚገርም ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ውለው ማታ እያሽካኩ ወደያዝዋት ክፍል ተመለሱ። እየተቃለዱ ሳለ ሜሪ አጠገቧ ያለውን እቃ አቀብለኝ ትለዋለች አጠገብሽ አይደል እንዴ አንስተሽ አትወስጂም ሲፎካከሩ እንደቀልድ ነገሩ እየከረረ መጣ

※ ቆይ ለኔ በብትሰጠኝ ምንህ ይቀንስብሃል

※ አጠገብሽ አይደል እንዴ ያለው ምን ሆነሻል አንቺ ልጅ?

※ ጭራሽ

※ እንደዛ የሚያምር ውሎ ውለን ባለቀ ሰአት የማይሆን ነገር ውስጥ እንዳንገባ

※ እንግባ ታድያ

※ እሺ በቃ አታኩርፊ ነይ ብሎ ሊያባብላት ሲል

※ አንተ እኮ ለኔ ......

※ አቦ ኤጭ እንግዲ ለዚህ ኑሮ ነው እንዲ ስጓጓለት የነበረው

※ ምን? እኔ እኮ ይሄን ሂወት ነው ስናፍቀው የነበረው አንተ ጭራሽ .....

እንደቀልድ የተናገረውን ነገር ከቁም ነገር ይዛ አምርራ ታለቅስ ጀመረ ናቲ ግራ ግብት አለው እንደምንም አድርጎ አባብሎ ሊያሳድራት

ምከረ። ጠዋት በጊዜ ተነስታ ያለመደባትን ወደ ቤት ካልሄድኩ አለችው ናቲም ኩርፊያው እንዳለቀቃት ቢገባውም አሺ አላት እና ተያይዘው ወጡ።

※ ታክሲ የት ነው የምይዘው ወደ መነሀሪያ

※ እዛ ጋር ተሻግረህ ጠይቃቸው

ብላ ስትመልስለት የለሌ ተናዶ በቆመችበት ቻው እንኳ ሳይላት ጥሏት ሄደ።

እቤት ከገባ በሃላም በንዴት ገንፍሎ ሳይደውልላት አደረ።

....... " ምንም ብታደርግህ አይፈረድባትም እኮ ካአንተም ብሶ በእሷ ትጮሀለህ አታፍርም ስንት ነገርህን ችላ በኖረች" አያለ ህሊናው ሲጮህበት ግን ከሁለት ቀናት ቆይታ በሃላ እንደተለመደው ቢደውልም ከወትሮው በተለየ ተናዳ ስለነበር ስልኩን አላነሳ አለችው።

የሚቀርባት ጓደኛዋ ጋርም ቢደውልላትም እሷም አላነሳ አለችው በጣም ደነገጠ። ሳምንቱን ሙሉ ቢደውልም ሜሪ ስልኳን አላነሳ ብላው በጭንቀት ጭንቅላቱ ሊፈነዳበት ጥቂት ቀረው። ሁሉም ነገር ተበላሽቶ ሜሪን ላለማጣት በሂወቱ ሊያደርገው አይደለም ሊያስበው

የማይፈልገውን ነገር ለማድረግ ተገደደ

.

.

.

ይቀጥላል

## ክፍል-33

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

......................ምን ማድረግ እንዳለበት በህሊናው ያብለስል ጀመረ። ያለችበት ሄዶ ሊያገኛት አሰበ ነገር ግን እሷም ጓደኞቿም ስልኩን የማይመልሱ ከሆነ የት ብሎ ሊያገኛት ይቻለዋል። ትልቅ ባህር ውስጥ ጠጠር የመፈለግ ያህል ከባድ ሆኖ ተሰማው።

"ሌላ ምን አለ ምን አለ ቢያንስ አንዴ እንኳ ሊያገናኘን የሚችል ...." ሲል ህሊናውን ቢምግትም አንዳች መልካም ነገር ጠብ አልልህ አለው።

ሲያወጣ ሲያወርድ ውሎ ማታ ከእንቅልፉ እየታገለ አንዳች ክፉ ሀሳብ ድቅን አለበት። የሰጣት ስጦታ ነበር ...አሀሀ እሱን አምጪ ብላት እኮ ምን አይነት ሰው ነው ብላ ኡኡ ስትል። ቢያንስ ማውራት እንጀምራለን ካወራን ደግሞ ሁሉንም ወደነበረበት መመለስ በጣም ቀላል ይሆንልኛል ብሎ ያለችውን አንድ ጠባብ መንገድ ለመምከር ወሰነ።

txt--"የሰጠሁሽ ስጦታ አንቺ ጋር እንዲቆይ ስለማልፈልግ ከቻልሽ አሁኑኑ መልሺልኝ።"

ሜሪ ካፌ ውስጥ ከጓደኞቿ ጋር ተቀምጣ txt ሲገባላት ስልኳን አውጥታ ስትመለከት ክው ብላ ቀረች። መደንገጧን የተመለከቱት ጓደኞቿ ስልኳን ነጥቀው እየተቀባበሉ  መልእክቱን አነበቡት። በናቲ እጅግ በጣም ተናደዱበት " ምን አይነት ህፃን ልጅ ነው ቱ..ቱ... እንዲህም አይነት ሰው አለ እንዴ" አለች ከተሰበሰትኑ አንዷ ጓደኛዋ የናቲን ስራ እንደመጠየፍ ብላ።

ናቲ txt ከላከ በሃላ ያደረገው ነገር ቢከብደው ለምን እንዳደረገ ለራሱ በማስረዳት ተጠመደ። " ወንድሜ እናትህ እና አባትህ እንኳ እድሜህ ሲገፋ ቆመህ እንዳትቀር በሚል ሰበብ አግብተህ እንድትወጣላቸው እንጂ አብረሃቸው እንድትኖር አይፈልጉም።የወለድካቸው ልጆችህም ቢሆኑ እድሜያቸው ሲደርስ ከአንዷ ተጣብቀው ጥለውክ ውልቅ ማለታቸው አይቀሬ ነው።

እመነኝ አንተም ከሚስትህ አንቺም ከባልሽ ውጪ አብሮሽ እስኪምት የሚኖር አንድም ሰው የለም። ሙሉ ዘመንህን ላለማበላሸት ከፈለግክ ደግሞ የምታፈቅራትን ለማግኘት ምንም ብታደርግ ክፋት የለውም።

ታድያ የእድሜ ዘመኔን እንቁ ሴት የሚመልስልኝ ከሆነ ለምን ባልዲ ሙሉ ምራቃቸውን አይተፉም። ለምንስ ጅልም ልጅም ሲሉ ውለው አያድሩም። የነሱ ወሬ ለኔ በእጄ ጨፍልቄ ከምገላት ትንኳሽ ያነሰ

ነው። በፍቅር ሲኖሩ አንድ ቀን ቱቱ ከ አይን ያውጣቹ ያላለ ሁላ ትንሽ ሲጣሉ ሲመለከት .........አይ ሀበሻ።

አሁን ለጊዜው ለፍቅሬ እንጂ ለክብሬ ቦታ የለኝም" ብሎ ለተከፋው ህሊናው ማብራሪያውን አቅርቦ ጨረሰ።

**★ሜሪ★**

ሜሪ ድንዝዝ ብላ ተርበትብታ ለናቲ በወንድ አስደወለችለት።

※ ሄሎ

※ ለማን ልስጥልህ እያለችህ ነው ሜሪ

※ በሃላ እኔው ደውዬ እነግርሻለሁ በላት

ናቲም ትንሽ ቆይቶ በሴት ጓደኛው አስደውለላት

※ የት መጥቼ ልቀበልሽ

※ የት ነው ያለሽው እኔው መጥቼ እሰጥሻለሁ የኔ ቆንጆ

ቦታ ተቀያየሩና ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉም ነር ዝም አለ። እዚህ ጋር እዛ ጋር በሰው እያስባለ የሌለ ነገሩን አወሳሰበው ለማንም አግኝታ መመለስ እንዳትችል አደረጋት። ሁሉም ነገር ውዝግብግቡ ሲወጣ ናቲ ይደውልላት ጀመረ። እየተነጫነጬች ታዋራው ጀመረ የማይሆን ነገር አድርጎም ቢሆን እንድታወራው ማስቻሉ ደስታን ሰጠው.... እያወሩ እያወሩ ከትንሽ ቀናት በሃላ ወደነበሩበት ቦታ ተመለሰች ልታገኘው በጣም ጓጓች እሱም ከሚታሰበው በላይ መናፈቁን ገለፀላት ነገ በጠዋት ለመገናኘት ያለ አንድ ማቅማማት ተስማሙ።

☎ ደወለላት

※ ሄሎ የኔ ፍቅር

※ ወዬ ደርሻለው እዛው የተለመደበት እንገናኝ አአ

※ እሺ የኔ ፍቅር ከቤት እየወጣሁ ነው

እንደተለመደው ተገናኝተው ወደያዙት ክፍል ገቡ። ሜሪ የተናገራትን

አምርራ ይዛው ኖሯል ለካ የሰጣትን ስጦታ ጠቅልላ ይዛው መታለች።

※ አመሰግናለሁ

ብላ እጇን ዘርጋች ስጦታውን እንዲቀበላት። ናቲ የምር ደነገጠ በፍፁም ያልጠበቀው ነገር ነበር።

※ ሜሪ እንደዛ ያልኩሽ እኮ እንደዛሬ የምንገናኝባትን ቀን ፍለጋ አማራጭ ባጣ እንጂ ከልቤ እኮ አልነበረም

※ አመሰግናለሁ

አይኖቿ እንባ አቅርረዋል። ናቲ የ እውነት ቢከፋውም ከመመለሷ በላይ የሚያስደስተው ነገር ስላልነበር ሁሉን ነገር አሳምናት ይዛው እንድትመለስ አደረገ።

#ከ_አንድ_አመት_በሃላ

ናቲ ና ሜሪ እንደ መጀመሪያቸው ሆነው በጣም ደስ የሚሉ ግዜያቶችን ያሳለፉ ጀምረዋል። እሷም ጥርጣሬዋ ቀንሶ እሱም

ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ቤት በመመለሱ ተቀራርበዋል። ከበፊቱ

አንፃር በቶሎ ቶሎ መገናኘት ጀምረዋል በቃ በጣም በሚባለ ደረጃ በምቀ ፍቅር ታጅበዋል። በመሀል በሀል ግን ግጭቶች መፈጠራቸው አልቀረም ልክ ግጭቶች ሲፈጠሩ ናቲ ንፁ ይቅርታዋን እንድትሰጠው መሃላው እጅግ በጣም እያስጨነቀው መሆኑን ለጄሪ እየደወለ ቢነግራትም ተራራ የመግፋት ያህል ከቦታዋ ንቅንቅ አልል ብላለች።

ናቲ ከመቼውም በላይ የማለው መሃላ እጅግ ያሰቃየው ጀመረ። ደጋግም ቢደውልላት ጊዜ ጄሪ ስልክ ትዘጋበት ጀመረ።

የተፈጠውን ሁሉ መናገር ስላልፈለገ ለጄሪ ጓደኛ የከፋ ነገር ተፈጥሮበት እንጂ ጄሪን ተጫውቶባት ሊተዋት ፈልጎ ይህን እንዳላደረገ። ሁሉንም ነገር ደግም በአካል ያለችበት ግቢ ድረስ መጥቶ አስረድትቷት ጄሪን ካመነችበተረ ብቻ ንፁህ ይቅርታዋን እንድትሰጠው እንደሚፈልግ ልትረዳው ለምከረችው የጄሪ ጓደኛ ነገራት። እሷም እውነትም ምክንያት ካለው የቻለችውን ሁሉ አድርጋ እውነቱን ለሷ የሚነግርበትን መንገድ ለማመቻቸት ቃሏን ሰጥታው የስልክ ወጋቸውን ጨረሱ።

#**ሜሪ**

ሜሪ ከ ናቲ ጋር ትንሽ በተኮራረፉ ቁጥር ከወትሮ በተለየ ጄሪን ለማግኘት ጥረት ማድረግ ጀምራለች። ሁሉንም ያሳለፈውን ሁኔታ ስሟን ሁሉ ነገሯት ስለነበር ጄሪን Fb ላይ የማግኘት ጉዞዋን አልጋ በአልጋ አደረገላት። ለሷ ብሎ እንደተዋት ምን ያህል እንደምትጠላው እያወቀች

" ላዋራሽ ስለምፈልግ ስልክሽን ላኪልኝ" .....ብላ ለ ጄሪ txt ላከችላት።

ጄሪም ከዚህ የተሻለ ናቲን መበቀያ ልታገኝ እንደማትችል በማመኗ በደስታ ስልኳን ላከችላት።

.

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል -34

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

☎ሜሪ ለ ጄሪ

※ ሄሎ ጄሪ

※ ሄሎ ማን ልበል

※ ሜሪ ነኝ ጄሪዬ

※ ወዬ ሜሪዬ እንዴት ነሽልኝ

※ አለሁልሽ ማሬ

※ ሁሉም ሰላም

※ ሁሉም ሰላም ነው

※ እንዴት መልካም ልጅ ነሽ አነጋገርሽ ስረአት አለው እንዲህ መልካም ሴት ሆነሽ ነው ናቲ ሊወሰልትብሽ እኔ ጋር የመጣው

※ ማለት?

※ አይገርምሽም መጀመሪያ እኮ አብራቹ ሆናቹ ነው ሚስቴ ላይ መወሰለት እፈልጋለሁ ብሎ እኔም ባሌ ላይ ብየው የተገናኘነው

※ ምን ? እኔ እኮ ይቅርታ ልጠይቅሽ ነበር ካንቺ ጋር ሆኖ ወደኔ እንዲመጣ በማድረጌ

※ ኖ ሜሪዬ አታሎናል ባክሽ

※ በዛ ላይ ደግሞ አንቺን ለብር ነው የሚፈልግሽ አብረን ሆነን የሱፍ ብር ከሷ ነው ምቀበለው እያለ ሲፎክርብኝ ነበር

※ እኔን ብር ፍለጋ ነበር የቀረበው

※ አዎ ብታይ ምን ያልምከረው ነገር አለ መሰለሽ እኔ እራሱ ብዙ ብሬን እሱ ጋር በመመላለስ ነው የጨረስኩት

※ በፈጣሪ ልክ ነሽ አንዴ ብርላኪልኝ ብሎ የለኝም ስለው እንዴት እንደሆነብኝ ብታይ አይ ናቲ

※ ተጠንቀቂ በፍፁም የሚሆንሽ ሰው አይደለም ስለ ፍቅር

በፍፁም የሚያውቅ ሰው አይመስለኝም በኔ ብትማሪ መልካም ነው እህቴ።

ሜሪ እጅግ በጣም የዋህ ሴት ናት እንኳን ትንሽ በእውነት ያሸበረቀች ውሸት ቀርቶ ልሙጥ ውሸት በማደናገር ለውሰው ካቀረቡላት እንደፈጣሪ ቃል መቀበሏ ሀቅ ነው። በትንሹ ወደ ሃላ መመልከት እንኳ አይቀናትም። ይህን ማድረጎ የዋህ ቀና ነች የሚያስብላት መስሎ እንደሚሰማት በተደጋጋሚ ለ ናቲ ብትነግረውም ይህን ያህል ሁሉን ነገር ጣል አድርጋ የምትባለውን ታምናለች ብሎ ግን በፍፁም አስቦት አያወቅም።

ናቲም ቢሆን ስለ ሱፉ ማውራቱ ከሜሪ ብር እቀበላታለሁ ለማለት ፈልጎ ሳይሆን ለጄሪ ማሰቡ ነበር።
ጄሪን እርግፍ አድርጎ ቢተዋት ....እኔ ማለት ተራ ሴት ነኝ? እኔ ማለት የወረድኩ ሴት በመሆኔ ነው ሚስቱን ሲያገኝ የተወኝ? ብላ እንድታስብ .......... እኔ ናቲን የተውኩት ለብር ያለውን አመለካከት ተመልክቼ ለብር ያለው ፍቅር አንገሽግሾኝ የምትልበትን ምራል እንድታገኝ ቢሆንም ........።

☎ ጄሪ ለ ሜሪ

※ ካንቺ ጋር መች ነው ቆይ በድጋሚ የጀመረው

※ ቀኑን ነገረቻት

※ ከዛ በሃላ እኮ ካልመጣሽ ከእሷ ጋር አድራለሁ ብሎኝ ግቢ ሄጄ አብረን አድረናል

※ ምን?

※ ለካ ሁለታችንንም ሲጫወትብን ነበር?

ይህንንም ቢሆን ከ ሜሪ ጋር ታርቀው ነገር ግን ሳያገኛት ያደረገው ነገር ሲሆን። አንደኛ ብር እንደሌላት ስለሚያውቅ ባለመምጣቷ ተማምኖ። ሁለተኛው ግን ናቲ ወስላታ ስለሆነ ተውኩት የምትልበትን ምራል ሊሰጣት ፈልጎ ነበር። እመኑኝ የትኛውም ወንድ ሌላ ሴት ጋር እሄዳለው የሚላት ተናዳ እንድተወው አስቦ እንጂ እሄዳለው ስላልኳት አብራኝ ልታድር ትመጣለች ብሎ የሚያስብ ጅል ወንድ በፍፁም ይኖራል ብዬ አላምንም።

ናቲ መወስለት ቢፈልግ ለ ሜሪ ምንም ሳይነግራት ሁሉንም በሚስጥር ማድረጉን በመረጠ ነበር። በየትኛውም መንገድ እንኳን መገናኘት መተያየት የሚችሉበት አጋጣሚ ሊኖር አለመቻሉን እንኳን እሱ እነሱም ጠንቅቀው ያውቃሉ ግን ያንን አልመረጠም።

☎ ጄሪ ለ ሜሪ

※ ሄሎ ሜሪዬ

※ ወዬ ጄሪ

※ ሳልነግርሽ ጉድሽን

※ ምንድነው ደም

※ እረ ይሄ ናቲሽ ጓደኞቼ ጋር እየደወለ አስታርቂኝ ብሎ እያለ ነው በቅርብ ደም ግቢ ድረስ ሊመጣ መሆኑን ነገረችኝ ጓደኛዬ

※ ምን

※ አይገርምም ደም እኮ ምክንያት የሚደረድረው ነገር ነው

የሚያስቀኝ አሁን ብትነግሪው 1000000 ምክንያት ደርድሮ ሊያሳምንሽ መምከሩ አይቀሬ ነው አይ የምክንያት ሰው ናቲ ....haha

ናቲ ምሎ መካዱ ህሊናውን ቢያጎብጠው ምንም ሳትበድለው ስለበደላት ይቅርታዋን መማፀኑ ልቧ እያወቀ ይህንንም ዞር አድርጋ ሜሪን ለማሳመን ተጠቀመችበት።

ሜሪ ናቲ ለ ብር እንደማይፈልጋት ለማወቅ ሁለት እርምጃ ወደ ሃላ መመልከት በቂዋ ቢሆንም አላደረገችውም። ባዶ ኪሷን ስትቀመጥ አብሯት ኩርምት ማለቱ እንዴት ማስታወስ ተሳናት። ብሯ አለቀ ብሎ የነደደው ልቡ እንዴት ከአይነ ህሊናዋ ጠፋ። እንካ ውሰድ ስትለው እንኳ ከእሷ አብሮ ማሳለፉን መርጦ የካርድ እንኳ ሳይተርፈው እቤቱ መግባቱን እንዴት መዘንጋት ይቻላታል።

እንዴት ከአይኗ ጆሮዋን ማመኑን ልቧ ፈቀደ?

እንዴትስ እንደጎዳት ከነገራት ልጅ መልካም ምክር አገኛለሁ ብላ አሰበች?

እንዴት ስለምታውቀው ናቲ የማታቃትን ጄሪን ማመኑ ሆነላት? ትንሽ እውነት በትልቅ ውሸት ተጠቅልሎ ሲሰጣት ጫፍ ጫፉን ተመልክታ

እንደት መዋጡስ ሆነላት?

ወንድሜ እኔ ከ ሚስትህ ላጣላህ ብፈልግ

ባሏ :- " ሚስቴ ቂጣ ስለምትወድ ቁርስ ከቂጣ በቀር አትበላም" ብትለኝ
እኔ:- "ባልሽ እሷ ቂጣ የምትበላው ስለቸገራት ነው አለኝ "......... ብዬ ለፀብ እንድትሆን አሰማምሬ ነው የምነግራት

ምኝ ከሆነች ሚስትህ በትንሽ እውነት የተጠቀለለውን ውሸቱን አምና እንዴት ችጋራም ትለኛለህ ብላ ጉሮሮህ ላይ መቆሟ አይቀሬ ነው። አላወራሁም እንዳትል ስለ ቂጣ መብላቷ ካንተ በቀር የሚያውቅ የለም አውርቻለሁ እንዳትል ስለመውደዷ እንጂ ስለ ችጋራምነቷ በፍፁም ትንፍስ አላልክም።

ልታስረዳት ስትምክር ወሬውን ከማመኗ በላይ እንዳወራህ እርግጠኛ ሆና የምጮኸው ጩኸት ያደክምሀል ...የምትችለውን ያህል ትጥር እና ስታስበው ጭራሽ የማታውቀውን ሰው ይህን ያህል አምና ትዳሯን የምትበትን ከሆነ ነገ እህቷ ጠልታህ ታጥቦ የተቀሸረ ምርጥ ወሬ ብታወራላት በተኛህበት ጉሮሮህን በጥሳ እንደምትጥልልህ ሴይጣን ሹክ ሲልህ ማስረዳቱንም ማሳመኑንም ትተህ እርግፍ አደርገህ መተወህ ግድ ይሆናል.........ታድያ ወንድሜ ትዳርህን

በተንኩት ማለት አአ

 ....... ይህን ለመመልከት ሜሪ ጊዜ አልነበራትም? ማን ስለሆነች ነው ይህን የምትመክረኝ? ሴት ጋር ልሄድ ነው ብሏት እሱን ፍለጋ የሮጠች ልጅ እንዴት እንዴት ማዳመጡ ቀለላት?
የሜሪም ብስጭቷ የምታብሰለስለው ሁሉ ናቲ ክፉ እንደነበር ለብር እንደፈለጋት የሱ መጫወቻ ሆና እንደነበር። ከዚያም በላይ ፈጣሪን እሱን የመሰለ እናት ባል ስለሰጣት ልታመሰግነው ሲገባ ጄሪን ከሰማች ወዲህ ፈጣሪ ከክፉ ነገር ሊጠብቃት የላከላት መላአክ ሆና ትታያት ጀምራለች። ነገር ግን ለናቲ ምኑንም አልነገረችውም። ጭራሽ ነገ ለመገናኘት ተቀጣጥረዋል።

 ያሰበችው ለማድረግ የምታቅደው ሁሉ ግራ ግብት ብሏታል። ነገር ግን የትኛዋም ሴት ትሸወዳለች ተብሎ በማይታሰብበት ጨዋታ ያ ሁሉ ፍቅሯ ድርምስምሱ ጠፍቶ ጭራሽ ለሷ መኖር ፍላጎቱ የነበረውን ባሏን በጄሪ የማር ልውስ ወሬ የሷን በቀል ልትበቀልላት በሱ ላይ የማያዳግም ዘመቻዋን በገሀድ ለመጀመር ዝግጅቷን ጨርሳለች።

.

.

.

ይቀጥላል

## ክፍል-35

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

ናቲ ሊያገኘት በጣም ከመቸኮሉ የተነሳ በጠዋት የሚገናኙበትን ኘሮግራም ለማመቻቸት ገመድ አልባ ስልኩን ከጉያው አውጥቶ የሜሪን ስልክ በምሽቱ ያስለቅሰው ተያይዟል።

※ ሄሎ ናቲዬ

※ ወዬ የኔ ፍቅር ነገ ስንት ሰአት ነው የምንገናኘው

※ ከ 9 ሰአት በሃላ ቢሆን ደስ ይለኛል

※ ምን ሆነሻል ዛሬ እስከዛሬ በለሊት ለመገናኘት እንዳልተሯሯጥን ዛሬ....

※ ፀጉሬን ጠዋት ለመሰራት አስቤ ነበር እንደውም ለምን ማታ አንገናኝም

※ ሰላም ነው ግን የኔ ፍቅር ሀሳብሽ በፍፁም ባይገባኝም በዘጠኝ ሰአቱ ተስማምቻለው!!

※ እሺ ቻው

※ ቻው

የሜሪ ልብ በሁለት ሀሳቦች መሀል መዋዠቁን ቀጥሏል አንዱ ለምን ስልክሽን ቀይረሽ አጠፊበትም ይህን ሁሉ ጉድ በየትኛው አቅምሽ ተሸክመሽ ትኖሪያለሽ እያለ የግራ ልቧን እንደ ክፉ ውጋት ጠቅ ያደርግባታል። አንደኛው ደግሞ አግኝተሽው ሁሉንም አፍረጥርጠሽ ነገረሺው ጥፋቱን በደንብ አውቆት በፀፀት ዘላለሙን እንዲኖር ፍረጅበት እያለ ቢወተውታትም ሁለቱንም ለማድረግ መንቀዥቀዡን አልፈለገችም ሰከን ብላ ንዴቷን ለመቆጣጠር ትታገል ጀመር ነገር ግን ንዴቷ አይሎ በንዴት ናቲ ጋር መደወል ጀመረች።

※ ሄሎ

※ ወዬ የኔ ቆንጆ ሚስት

※ ናቲዬ ከጓደኞቼ ጋር ቀጠሮ ነበረኝ እረስቸው ብታይ አሁን ትዝ አላለኝም መሰለህ ለምን ከነገ ወዲያ አንገናኝም

※ ምን አይነት ቀልድ ነው የምትቀልጅው ያምሻል እንዴ .....

ናቲ ንዴት ያንዘፈዝፈው ጀመረ የሆነ ችግር እንዳለ ቢገባውም መገመት ግን ፍፁም አልሆንልህ አለው!!

※ እረ የቀልዴን ነው አረጋጋው.... ብላ ንዴቱን ስታይ በረድ ብላ አረጋጋችው

※ እንደዚህ አይነት ቀልድ.............

ናቲ ሲያወጣ ሲያወርድ ቢያድርም አንድም ችግር ሊፈጥር የሚችል ነገር ጠብ አልልህ አለው። ጠዋት በጊዜ ደውላ ፀጉር ቤት ልትሄድ መሆኑን እያወሩ ሳለ በአል በመሆኑ ባንክ እንደሚዘጋ ትውስ አላቸው። ውይ ዛሬ ለካ ዝግ ነው በቃ ከነገወዲያ እንገናኝ ፈጣሪ አላለልንም ማለት ነው አለችው ፈጠን ብላ!! ናቲ ይሄ ከነገ ወዲያ አልጥምህ ስላለው እንዴትም አምታቶ እንደሚመጣ አሳምኗት ስልኩ ተዘጋ።

ከ 2 ሰአታት የ መኪና ጉዞ በሀሏ ሰፈሯ ደርሶ ደለላት

※ ደረስክ ናቲዬ

※ አዎ ውጪ ሜሪዬ

※ እሺ መጣው

ልክ ስታገኘው ሁሉን እረስታ ምንም ክፉ ነገር ልታሳየው ባለመምከሯ ጥርጣሬው ልክ አለመሆኑን እራሱን በማሳመን የተለመደ ፍቀራቸውን ያጣጥሙት ተያያዙ። የያዙት ክፍል ከገቡ በሃላ ናቲ መንገዱ ስላደከመው ከተዘረጋው አልጋ ላይ እጁን እና እግሩን ዘረጋግቶ ጋደም አለ። ባልተለመደ ሁኔታ ጉሮሮው ስር በሁለት እጇ ጠፍራ ያዘችው እንድላፋት ፈልጋ ነው ብሎ ችላ ቢላትም እጇ እየጠነከረ መጣ ናቲ በጣም ትንፋሽ ሲያጥረው እጇን መንጭቆ አስለቀቃት።

※ እንዴ ምን ሆነሻል

※ ገድዬክ እኔም ብምት ስሜቴ ነው

※ እረ ተይ የኔ ፍቅር እኔ ምገባው ገነት
የራስሽን ታውቂዋለሽ እዛ ምንገናኝ መስሎሽ ጉድ እንዳትሆኚ
※ ለምን የ አምፖሉን ሽቦ በጥሰን አንይዘውም ጌታን
በጣም ደስ ይለኛል

※ ሜሪ እየማልሽ ነው ይታወቅሻል አይደል

※ ጌታን ከልቤ ነው ከዛ ሁሉን እርስት በቃ....

ናቲ ውዝግብግቡ ወጣ ቀልድ እና ምሯ እውነት እና ውሸቱ ተምታቶበታል። ምን ሆና ነው ብሎ የምክንያቷን ጫፍ ለማግኘት ታች ላይ ቢልም በፍፁም ሊሆንለት ግን አልቻለም።

ማታ ባልተለመደ መልኩ በጊዜ ተኛች ናቲ በጣም ግራ ተጋብቶ እዛው ክፍሉ ውስጥ ይጠጣ ጀመረ። ስክር ብሎ ሲደካክመው ፍንግል ብሎ ተኛ።

ጠዋት እንደ አዲስ በፍቅር ቢነሱም ሜሪ በመሀል በመሀል የሰማችው ነገር ሲያበግናት ወደ ቤት ካልሄድኩ ብላ ስትሮጥ እሱም ምክንያቷ ባይገባውም በሩጫ ሲከተላት ለተመለከተ ሻርኘ እና ተራራው ጎደለ እንጂ ቀረፃ ላይ ያሉ የህንድ ፊልም አክተሮች መምሰላቸው ሀቅ ነው።

እንዲህም እንዲያም እያሉ አራት ቀናት ምላቸው ትላንት በተነጋገሩት መሰረት ናቲ በጠዋት ወደ ቤቱ ካልተመለሰ አብረው ካረፋፈዱ መለያየቱ ስለሚደብራቸው የግዱን በጠዋት ለመሄድ ሲዘገጃጅ ሜሪ ሁሉንም የረሳች ይመስል አረፋፍደህ ትሄዳለህ ብላ ትጎተጉተው ጀመር ....ካረፈድኩ ተይ በሃላ ይደብረናል ..ፍንክች አልልም ብላ

ሀሳቡን አስቀየረችው። በማርፈዱ ተስማምተው ከያዙት ክፍል ወጡ።

ልክ 7:30 ምሳቸውን ቀማምሰው ፊልም ለማየት ተነጋግው ወደ ሲኒማ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ። ሜሪ ከፊት ለፊት ናቲን ትታው ምንቅር ምንቅር እያለች ትጓዝ ጀመር።

※ ምን ሆነሽ ነው የምትሮጪው ተረጋጊ እንጂ

※ ከኔ ጋር ምንም ማድረግ ደስ አይልህማ

※ ስለሚለኝ አይደል እንዴ የመጣሁት

※ እንደውም ተወው ወደ ቤቴ ሄጄ ባርፍ ይሻለኛል .....ብላ ወደሃለ ተመልሳ ጥላው ሄደች ናቲ አራቱንም ቀናት ወደቤቴ እያለች ሲመልሳት ስለቆየ ምርር ብሎት ባሁኑ አልተከተላትም እንደጠገቡ ወይፈኖች ሁለቱም በየአቅጣጫቸው እየዘለሉ ቻው ሳይባባሉ መለያየቱ የለመደባቸው ይመስላል።

እንደተለመደው ነገሮችን እስክትረሳ ብሎ አንድ ሶስት ቀን አሳልፎ ደወለላት።

※ ሜሪዬ

※ አቤት

※ ምን ሆነሻል ዛሬም ለንብጭሽን እንደጣልሽ ነሽ በይ አፍጥኝው ሚስቴ ናፍቃኛለች ወደ ቤቴ ተመለሽ ...አለ ፈገግ ብሎ

※ አልሰማህም እንዴ

※ ምኑን

※ ሁሉም ነገር እንደተባነነብህ ነዋ!! እረ በቃ ከተነቃብህም በሃላ ይደብራል...

※ ምን ማለት ነው ...

※ ሁሉንም ስሰራ የነበረውን አውቄያለሁ አንተ አይደብርህም አሁንም ግቢ ድረስ መጥቼ ላግኝሽ እፈልጋለው እያልክ እሷን እየጀነጀንክ እኔነን እንደምትወደኝ ስታባብለኝ .......

ብላ ጄሪ መሆኗን ፍንጭ ቢጤ ሰጥታው ስልኩን እላዩ ላይ ጥርቅም

አደረገችበት....ናቲ መብረቅ እንደመታው ሰው ድርቅ ብሎ ቀረ መልሶ ስልኳ ላይ ቢምክር ተዘግቷል። ምን እየሰራች ይሆን? እኔን ተበቀልኩ ብላ አንዳች ስህተት እንዳትሰራ ብቻ? የት ሆና ይሆን? ሀሳቡ ተዘበራርቆ ስልኳን ሲምክር ውሎ አመሻሹ ላይ ሰራለት።

※ ሜሪ ተረጋጊ ምንም አይነት ስህተት እንዳትሰሪ

በጣም ብዙ ከብረት የጠነከሩ ቃላት አዃጎደጎደችብኝ የእውነት በህይወቴ እንዲህ ቅስሜ የተሰበረበት ቀን በፍፁም ኖሮ አያውቅም....... ያደረኳቸው ነገሮች ተገለባብጠው ይህን በመሰለ መልኩ መቅረባችው በእጅጉን ቢያስገርመኝም አላደረኩም እንዳልል አድርጌያለሁ አድርጊያለው እንዳልል ተገለባብጠዋል። እንዳብራራላት እድሉን እንድትሰጠኝ ብጠይቃትም የኔ እወነት ዋጋ አጣ። እኔ ውሸታም መሆኔን የዋሸሁት ደግም ከሁለቱም ጋር ልወሰልት በመፈለጌ እንደሆነ ሁለቱም 100% አምነውበት ደምድመው ጨርሰዋል።

በነገራችን ላይ በጄሪ አንድ ቅራኔ የለኝም ምክንያቱም እሷ የተጎዳችውን ጉዳት ሜሪም እንዳትጎዳ በመፈለጓ ያደረገችው ነገር እንጂ ሆን ብላ እኔን ለመጉዳት አስባ ነው ብዬ በፍፁም አላምንም ምስክሬ ደግም የድሮው መልካም ባሃሪዋ ነው። እልኸኛ ሆና ሳለ

እልኸዋን ዋጥ አድርጋ ለቅሶዋን አፍና ብዙውን የሆነችልኝ ልጅ ከ 1 ቀን ጥፋቷ በላይ የ6 ወር መልካምነቷ ገዝፎ ቢታየኝ ልክ ነኝ ብዬ አምናለሁ።

ነገርግን እሷ የበደልኳትን ተመልክታ የሰጠዋትን ፍቅር ምነው ዘነጋችው

10 በግ + 3ፍየል= 13 ፍየል ተብሎ እንዴትስ ይደመራል።

10 መልካምነት + 3 መጥፎነት = 13 መጥፎነት

እንዴት መባል ይቻለዋል።

አውነት ናቲ ሙሉ ሂወቱን ክፋት ነው የሰራብሽ?

ቆይ ባልሽ አንቺን ከሆነ ክፉ ነገር ለማስመለጥ እራሱን መስዋት አድርጎ የውሸቱን ወሰለትኩ ማለቱን ከብዙ ጊዜ በሃላ ብትሰሚ ምን ሊሰማሽ ይችል ነበር?

ብዬ ብጠይቃት ደስ ባለኝ ነበር አሁን ግን ሜሪን ለመመለስ ብዙ የቤት ስራ ለሰጠችኝ ጄሪ ነገሮችን እራሷ እንዳበላሸች እራሷ እንድታስተካክላቸው ልጠይቃት ቀና ቀናውን ተመኝቼ እየደወልኩላት ነው......

※ ሄሎ ናቲ

.

.

.

---ይቀጥላል----

# ክፍል-36

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

※ ሄሎ ናቲ

※ ሰላም ነው ጄሪዬ

※ አለሁልህ ስለ ሜሪ ልታወራኝ ፈልገህ ነዋ

※ አዎ ያልሻት ነገር ........

ብዙ ካወሩ በሃላ ምንም አይነት ልታደርግለት ዝግጁ አለመሆኗን ገልፀችለት ቢቻላት እንደው ቢለያዩ እና ሜሪ እንደሷ ከመጎዳት ብታመልጥ ስሜቷ መሆኑን በቀጥታ ገለፀችለት። የጠበቀው ነገር ስለሆነ ያን ያህል በንግግሯ አልተገረመም ነገርግን በትንሹም ቢሆን ነገሮችን ታስተካክልልኛለች ብሎ አስቦ ስለነበር በመልሷ ተስፋ ቆረጠ። ከጄሪ ሌላ በምን የተጣመመ ፍቀሩን ማቃናት እንደሚቻለው ሲያስብ ቢቆይም ድካም ሆነበት ትርፉ።

☎ ናቲ ለሜሪ

※ አቤት

※ እንዴት ነሽልኝ

※ አለሁ ቆይ አልደከመህም

※ ትዳሬን በትኜ ምኑን ተኛውት?

※ በነገራችን ላይ ታውቃለህ አይደል

※ ምኑን

※ የፊሚኒስት አቀንቃኝ መሆኔን

ሳቅ አፈነኝ "ያኔ ስለ ጄሪ ሁሉን ነግሬሽ ትቻት ስመጣ..... ጄሪን ምን አደረካት? የሆነ ነገር አድርገህ ልታጠነክራት ይገባል እኮ እንዴት ዝም ብለህ ትተዋታለህ? እንደማለት ላረጋጋት ጥቂት ጊዜ ለሷ መስጠቴ ይህን ሁሉ ግርግር ፈጥሮ ትንሽ ሲጎዱ አጋጣሚውን ተጠቅም ፊሜኒስት መሆን አይከብድም?" ልላት ፈልጌ በእሳት ላይ ቤንዚን

መነስነስ እንዳይሆንብኝ ሰግቼ ሳቄን አፍኜ

※ አዎ.....አዎ አውቃለሁ

※ እና የጄሪ ጉዳት ማለት የኔም ጉዳት ነው አሁን ከሷ ጎን ነኝ .....

አሁን ከቅድሙ በላይ ሳቄ ይታገለኝ ተያይዟል ....የሳ ፊሜኒስት መሆን ሳይሆን የሷ እና የጄሪ አንድ ሀሳብ ሳይኖራቸው መግባባታቸው ግርምትን ፈጠረብኝ። የሜሪ ፍላጎት ለምን እርግፍ አድርገህ ትተሃት ሳትመጣ ለምን ያን ያህል መቆየቱ አስፈለገ እንደሆነ አውቃለሁ። የጄሪ ግን ምን ይሆን? ለምን እርግፍ አድርገህ ሳትተወኝ? ይሆናል ብዬ አላምንም ካልሆነ ከሜሪ በተቃራኒው ነው ማለት ነው። ምንድነው ያስማማቸው አልገባኝም?" ያሰብኩት አስቆኝ ሳቄን አፈን አድርጌ

※ እ... እሱማ ልክነሽ

ጥቂት ካወራን በሃላ ባለመግባባት ተግባብተን ስልኩ ተዘጋ።

ማረፍ ያለመደው ጭንቅላቴ ንዝንዙን ጀመረ .....

ቆይ ምኗን ወደህ ነው ይህን ያህል የምትጨነቅላት?

ቁንጅናዋን ነዋ ... መልሼ እረ አይደለም ከሷም በላይ ቆንጆዬ ከሆኑ ሴቶች ጋር አሳልፌያለሁ እኮ ግን የዚህን ያህል አልሆንኩም። አያድርግባት እና እሳት እዳየው ፌስታል ፊቷ ተጨማዶ ብትመጣ እንኳ ፍቅሬ እንደማይቀንስ አውቃለሁ። ታዲያ ምኗ ነው....

ስለምትለብስ ይሁን .....እረ በፍፁም ቡቱቶ ለብሳ አብዳ ብትመጣ ከልቤ አቅፌ እንደምቀበላት ልቤ ያውቀዋል ይህም በፍፁም አይሆንም።

በቃ ባህሪዋ ነው ብዬ ወስኜ ሳልጨርስ አሁን ቀንዴን እያስበቀለኝ ያለው ጭቅጭቋ እኔን አለማመኗ ትዝ ቢለኝ እሱም አብራት እያለ አብሪያት ለመኖር መጣሬ ምክንያቴን አፈረሰብኝ።......ኡኡኡኡኡ እረ እባካቹ አንድ የመውደዴን ምክንያት አፋልጉኝ እና እሳን ለመርሳት መላ ልፈልግ። .....እያለ ህሊናውን ሲምግት ቆይቶ ሲመረው ይደውልላት ጀመረ።

☎ ናቲ ለ ሜሪ

※ ቆይ ስራ የለህም እንዴ

※ ከዚህ የተሻለ ከየት ይመጣል ስራ

※ ካንተ ለመለየቴ ሰው አለማክበርህ ከበቂ በላይ እኮ ነው።

መሬት ወድቀሽ ብትነሺ ወርቅ አፍሰሽ ትነሺ ይመስል መሬት የወደቀውን የኔ ቢጤ ከመፀየፍ በላይ ሰው መናቅ የለም እኮ? የኔ ቢጤ ንቄ ለሀብታም አላሸረግድም። ለኔ ሰው ማለት በዳቦ እንደተያዘ ፌስታል ነው ውጫዊው የፌስታሉ ዋጋ ሳይሆን ወስጣዊዉ የዳቦ ዋጋ ነው የሚያሳስበኝ። በ500 ብር ፌስታል የ 1 ብር ዳቦ ከሚሰጡኝ በ1 ብር ፌስታል የ 500 ብር ዳቦውን እመርጣለሁ። በአጭሩ ከልብሱ ልቡ ውድ ለሆነ ሰው አጎነብሳለሁ ። አለማክበር ይሄ ከሆነ አዎ ሰው አላከብርም".... ለማለት ቢቃጣኝም ለጊዜው በዝምታ ማለፉን መረጥኩ .....ቀጠለች

※ ይህን ያህል የምትለማመጠኝ ለብር ፈልገኸኝ ነው አይደል? መደበሪያክ አደረከኝ እኮ። ካንተ ለመለየቴ የመጀመሪያ ምክንያቴ ምን

እንደሆነ ታውቃለህ ያኔ ብር ስላልነበረኝ ባንተ ብር መብላት ባንተ ብር ማደር ባለመፈለጌ ነው ነበር። ከዛ በሃላ ነው የታመምኩት አሁንስ ደና ነህ?

በሀሳቤ ሜሪ እየከሳችብኝ መጣች ቆሌዬን ሳይሆን ቆዳዬን የገፈፈችኝ ያህል ከባድ ህመም ሙሉ ሰውነቴን ተሰማኝ። ምንም ሳልናገር መልካም ህይወት ብዬ ስልኩን ዘጋሁት።

ቆይ ብር ከኔ ፈልገህ ማለት ምን ማለት ነው?

የቱን ብርእንደሆነ በፍፁም አልገባኝም። ሳላውቅ ኢንቬስተር ጠብሼ ሀብቷን ደብቃኝ ይሆን እንዴ? እረ ሀብቷን ከሰው የሰማው መስሏት እንዳይሆን ደውዬ የማውቀው ነገር አለመኖሩን ላሳውቃት .....እያልኩ በራሴ እቀልድ ጀመር ስበሳጭ መሳቅ ይቀናኛል በጣም እየሳቅኩ በጣም አንጀቴ እርርር አለብኝ። ከብር ያነሰ ለተራ ፍቅር ነው እንዴ ይሄ ሁሉ መልፋቴ ......

ቆይ እኔ ብር ፍለጋ ልምጣ አንደውም ጀግና ነኝ ባዶ ኪሴን መሆኔን አውቀሽ ወደሽኝ ያንን ወሰድክ የምትይውን ስባሪ ሳንቲም ጠቅልዬ መውሰድ ከቻልኩ። ቆይ ከያዝሺው ብር  አንሰሽ ነው ካንቺ በላይ ብሩን ፍለጋ እኔ ጋር መጣህ የምትይው? .......እያለ ናቲ የቆሰለ አንጀቱን በመጠጥ ሊያቃጥለው ወደ አንድ መጠጥ ቤት ጉዞውን

ቀጠለ። ብቻውን ሲጠጣ አምሽቶ ወደ ያዘው ክፍል ዘው ብሎ ገብቶ ከአልጋው ላይ ተዘረረ።

:

:

:

#ከ______በሃላ

※ ሜሪ የልጆቹ ቦርሳ የት ነው?

※ ሶፋው ላይ ናቲዬ

※ የረሃዋን አጊንቸዋለሁ የማርኮንን አጣሁት? ምን እየሰራሽ ነው ለምን ወተሽ አትሰጪውም ሹፌሩ ወደ ት/ት ቤት ሊወስዳቸው ውጪ ቆሟል እኮ ......

.

.

.ይቀጥላል

# ክፍል-37

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

#ከ_ተ___ በሃላ

※ ሜሪ ... ሜሪ የልጆቹ ቦርሳ የት ነው ያለው

※ ሶፋው ላይ ናቲዬ

※ የረሃዋን አጊንቼዋለሁ የማርኮን ግን የለም ምን እየሰራሽ ነው ለምን ወተሽ አትሰጫቸውም ሹፌሩ ቆሟል እኮ ት/ት ቤት ሊወስዳቸው

※ እሺ ነኔ ፍቅል ቁርስ እኮ እየሰራው ስለሆነ ነው

※ የሚሰበረውን ነው የሚቀቀለውን መቼም ካገባውሽ ወዲህ ሆዴ በእንቁላል ቢጫ መስራቱ ሀቅ ነው

※ ሂድዛ .... ባክህ ጥብስ ፍርፍር ነው

※ እኔማ የምታበስልልን ላምጣ ብል ከነዘበኛው ካልሆነ ስትይ ሌላ ክፉ ነገር አስቤ ሳይሆን ብሩን አስቤ ተውኩት

※ አሁን እረፍ

ሁለታችንም ወጥተን ልጆቹን በር ላይ ሳም ሳም አድርገን ሸኝተናቸው እየተላፋን ተመለስን አሁንም እንደድሮው ምንም የተቀየረ ነገር አልነበረም ......... ሜሪ የጣደቸውን እረስታ የልጆቹ አለመኖርን ተከትሎ እንደጀማሪ ጥንዶች ከሶፋው ላይ እንታገል ጀመረ። ሆሆሆሆ ሰው አግብቶ ወልዶ እንዴት እንዲ ይሆናል ትንሽ መሰለቻቸት እንኳን የምትል ይመስላል አስተያየቷ። ወዲያው አይሆኑ ፍትጊያ ውስጥ ገባን ልበሳችንን አወላልቀን .......(#ከተኛው_በሃላ) ከላይ ያለውን"

ኳ..ኳ...ኳ

※ 4 ሰአት ሆኗል ልናፀዳ ነው

የሚለው የፅዳቷ ድምፅ ናቲን ሰክሮ ከወደቀበት አልጋ ብቻ ሳይሆን በህልሙ እያጣጣመው ከነበረው የትዳር ህይወቱ አነቃው። የቀሰቀሰችው አጉል ቦታ ቢሆንበት ምና ___ አቋራጭ ናት ምናለ 5 ደቂቃ እንኳ ብዘገይ እያለ እየተነጫነጨ ክፍሉን ለቆ ወጣ። አይኖቹ ቀልተው ፀጉሩ እንደ ጃርት እሾህ ቆሞ ፊቱ ጨው በበዛበት የባህር ውሃ የታጠበ ይመስል ነጥቶ ለተመለከተው መካሪ ያጣ ቦዘኔ መምሰሉ አይቀርም።

እራስ ምታቱ ሚዛኑን አስቶ እያንገዳገደው ወደ ሰፈሩ ከሚወስደው ታክሲ ውስጥ ዘው ብሎ ገባ። ወንበሩን ደገፍ ብሎ ሳይፈልግ እየተከደነ ከሚያስቸግረው አይኑ እየታገለ የተለጠፉትን የታክሲ ላይ ፅሁፎች ይኮመኩም ጀመረ። ፈገግ በሚያሰኙት ፈገግ እያለ በሚያስተምሩት ለመማር እየመምከረ ሳለ ድንገት ከአንዱ ጥቀሱ ላይ አይኑ ቀረ።

"እያንዳንዱን ቀን በሰበሰብከው ምርት ሳይሆን በዘራኸው ዘር መዝነው"
እንደሰረቀ ሰው ሲደነግጥ ተሰማው አሀሀ ምን የሚያገናኘው ነገር አለ ከኔ ጋር እኔ እንደሆንኩ እያለ........እያልጎመጎመ ከሚወርድበት ቦታ ደርሶ ከቤቱ ገባ።

እቤት ሲገባ እህል እንኳ ለመቅመስ አልተመኘም ህልሙ ካቆመበት ይቀጥል ይመስል ከአልጋው መጣበቅን መረጠ ። ለረጅም ሰአታት ከተኛ በሃላ አመሻሹ ላይ ከእንቅልፉ ሲነቃ ሙሉ ቀን ባዶውን የዋለ አንጀቱን በምግብ አረስርሶ አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ሙዚቃውን ያዳምጥ ተያያዘ። ከጆሮው የተጣበቀው የዘፈን ማዳመጫው ጩኸት እንኳን ለሱ ከጎን ላለው ሰው ድምፅ ቢያስተጋባም ህሊናው ግን የሚጮኸው ሙዚቃ ሳያሳስበው ከቀኗ ጥቅስ ጋር ጨዋታውን ጀምሯል።

የዚህን አይነት የህሊና ውይይት ያወቀው ከጄሪ ሲሆን ብዙ ሀሳቦችዋን ለመጣልም ሆነ ለማፅደቅ ከራሷ ጋር መሟገት ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ ታምን ነበር። እናም የትኛውም ሰው ሀሳቡን ሲያካፍላት በደፈናው መቀበልን አትወደውም ከዚያም ይልቅ ከህሊናዋ ማህደር ምናባዊ ሰዎችን በሁለቱም ወገን አቁማ እነሱ ሲሟገቱ ትታዘባለች ሀሳቡ ታሽቶ ሲወጣለት መልካም የመሰላትን መርጣ ውሳኔዋን ታፀድቅ ነበር። ይህን ድርጊቷን ናቲም ይወደው ስለነበር ኮፒ ለማድረግ ጊዜ አላጠፋም ነበር ቢዙ ጊዜም ተጠቅምበታል።

አሁንም እየሆነበት ያለው ነገር ቢያስጨንቀው ውጥረቱን ለማርገብ ይህንን ሙግቱን ለማድረግ ተዘጋጀ። ለሊቱ ፀጥ ረጭ ያለ በመሆኑ ሙዚቃውን ዘግቶ አይኑን ገርበብ አድርጎ ከህሊናው ማህደር በሁለት የተከፈሉ በየቡድናቸውም አራት አባላት ያሏቸው ሰዎችን አቅርቦ እራሱን እንደ ዳኛ ጥቁር ካባ አጎናፅፎ ተቀመጠ።

ሁለቱም ተሟጋቾች መዘጋጀታቸውን መወልክት ሲሰጡት ናቲ መልካም ሰው ነው ለሚሉት የመጀመሪያ እድሉን ሰጣቸው።

※ ናቲ ማለት መልካም ሰው ነው ለሜሪ ብሎ ያልገባበት ገደል የለም ያላጣው ክብሩን መፈለግ ከባድ ነው። ለጄሪም ቢሆን

መልካሙን ሲሰራ ቆይቶ ግድ ቢሆንበት ነው መጉዳቱን የመረጠ። አለ ከ 4ቱ አንዱ ከጭንቅላቱ ምላሱ የቀደመበት ወጠጤ ......

ወደ ሰላሳዎቹ መጨረሻ የሚምላው ጎልማሳ በተቃውም የተጨማደደ ፊቱን ይዞ ተነሳ።

※ አንዳንድ ሰዎች የሰዎችን ድክመት በማሳየት እራሳቸውን ጠንካራ ያስመስላሉ። ለጊዜው ስለ ሜሪ እና ስለ ጄሪ እንተወወ እና ከ 1-9 ስለነበሩት ሚስቶችህ ጥቂት ልበል። እውነት እነሱ አምላክ የላቸውም ብለህ ታስባለህ? እውነት እነሱ ላይ የተጫወትከው ጨዋታ በይቅርታ ሳይፍቅ መልካም ትዳር እና መልካም ህይወት ይሰጠኛል ብለህስ ታስባለህ? ለ 6 አመታት እንክርዳድ ስዘራ ከርመህ አሁን እዚያ እና እዚያ ጠብ ያደረጋትን ሁለት ፍሬ ስንዴ ከሙሉ እርሻው መጠበቅህ አሳፋሪ ነው። ለምን እንደ ካሮት ቁልቁል ማደጉን መረጥክ?

.......... ናቲን ብለው የመጡት በሙሉ ዲዳ የሆኑ ይመስል ሁሉም ዝምታን መረጡ። ከዚያው ቡድን ከእድሜያቸው የተነሳ ድምፃቸው የሚርገበገብ አባት ቀበል አድርገው ንግግራቸውን ቀጠሉ።

※ ልጄ ለምን ስለመኮትኮትህ ታወራለህ ለምንስ ውሃ ማጠጣትህን እንደትልቅ ጀብዱ ቆጠርከው መጀመርያ ምን ስዘራ

እንደከረምክ መናዘዙ አይሻልም ነበር። እንዴት እንክርዳድ ስዘራ ኖረህ

ውሃ አጠጥተህ በመኮትኮትህ ስንዴ የምታጭድ ይመስልሀል? እንዴትስ እራስህ ቦታ ቆመህ ሁሉን መመልከቱን ወደድከው?

አንተ ቦታ ላይ ቆመህ ጄሪን ስታስቃኘኝ ጭንቀትህ አስጨንቆኝ እውነትም አሳዛኝ ሰው ነህ ብዬ ማሰቡን መርጬ ነበር። ነገር ግን በሷ ቦታ ሆኜ ስመለከትህ ፍፁም ክፉ ሰው ሆነህ አገኘሁህ። ጄሪ አንተን እንደ መልካም ሰው ተመልክታህ ያጋጠማትን ክፉ ነገር አጫወተችህ። በደካማ ጎኗ ገብተህ ልቧን አሸፈትከው ያሸፈትከው ልቧን ከባላ ነጥቀህ በእጅህ ካስገባህ በሃላ ግን መሃላህን ፈፅም እረስተህ የሰው ሁሉ መሳቂያ አደረካት። መልካም ሰው ብትሆን ግን ከባሏ ማስማማቱን እንጂ ከባላ ማሸፈቱን በተጠየፍክ ነበር።

ፈላስፋ የመሰሉ ጢማቸው የተንዠረገገ ትልቅ ሰው እጅ ነስተው መድረኩን ተረከቡ።

※ እንኳን ለዘጠኙ አፈቀርኳት ለምትላት ሜሪ እንኳ መልካም መሆን ያቃተህ ትንሽ ሆነህ ነው ያገኘሁህ። ሰው እንዴት አበድኩላት የሚላትን ልጅ ችግር አጋጥሟት ቀረች ብሎ ከሴት ጉያ ስር ይወሸቃል? ምን አይነት ህሊና ያለው ሰው ይሆን ከጓደኛው ሚስት

ጋር በንፁህ ህሊናው መጥቶ በስህተት ተዳራዋት ብሎ ማመን የሚቻለው። ናቲ አሁን ማድረግ የሚኖርብህ መልካም ሰው ነኝ

ማለቱን አቁመህ ቁጭ ብለህ የዘራኸውን እንክርዳድ ከስሩ ንቀል። ሙሉ ማሳህ ንፁ ሲሆን ስንዴውን መዝራት ትጀምራለህ አሁን እየዘረሃት ያለችው የፍቅር ስንዴ በእንክርዳድ ተውጦ ቀጭጭጮ እየሞተ መሆኑን ከደረሰብክ ነገር መረዳት ብትችል መልካም ነው።

እባክህ ያንተው አረም ሜሪን እንዳይውጣት ከሷ ራቅ። ክፉ የማታውቀውን ልጅ ክፉ ተናጋሪ አደረካት የዋህ የነበረችውን ልጅ የዋህነቷን ከቋፍ ላይ ነው። እባክህ ልጄ ላንተ ስትል ስንቱን ሆናለች ስንቴ የማይሆኑ ቀናትን አሳልፋለች ስንቱን ትዳር ትታለች አንተ ለሷ ስትል የምታደርገው መልካም ነገር ቢኖር ልትተዋት ብቻ ነው የሚገባህ። አብሬያት ሆኜ እስተካከላለሁ እንዳትል 1000 ጊዜ እድሉን ሰጥታህ 1 ነገርህም አልተቀየረም።

ናቲ ፈፅም ባላሰበው መልኩ ያላሰበውን ሀሳብ አንስተው የረሳውን የራሱን ክፋት አግዝፈው አስመለከቱት። ከዚህ በላይ የራሱን ክፋት ማዳመጡ ቢያስጨንቀው ገርበብ ያደረገው አይኑን ገልጦ ተቀመጠ።

በየቀኑ እንዲህ ያሉ ቁጣዎችን ማዳመጥ የሰራውን ሀጥያት ያቀልለት ይመስል ልምዱ ሆኖ ቀረ። በየቀኑ ስለበደላቸው

ስላስከፋቸው ሰዎች ሲመለከት እነሱ መልካም ሆነው እንጂ እሱ መልካም ሰው ሆኖ እንደማያውቅ ህሊናው እየቀጠቀጠ ያስረዳው ከጀመረ ድፍን አንድ

ወር አለፈው። እንደ ድሮው ለሜሪ ደውሎ ወደራሱ ለመመለስ መምከሩን ትቶ በእሷ ናፍቆት በእሷ ፍቅር ከመቼውም በላይ መሰቃየቱን መረጠ። አንዳንዴ ላጠፋኸው ነገር ስትቀጣ ቢያምህም ህሊናህ ግን በሰላም ይምላል የጎዳሀቸውን ሁሉ እየካስክ ይመስልሀል። አንዳንድ ሰዎች አብረውክ እንዲኖሩ ሳይሆን መጥፎነትህን ገለው መልካም የምትሆንበትን መንገድ ጠረገውልህ እንዲሄዱ ብቻ ነው የሚሰጡህ።

የእውነት የሰውን መጎዳት የምታውቀው የምትወደውን ሰው ማጣት ግድ ሲሆንብህ ብቻ ነው። ትላንት ያጠፋኸው ጥፋት ካለ ጊዜ ሳታጠፋ አሁኑኑ በይቅርታ ንቀለው ዛሬም ክፋትን እየዘራህ ከሆነ ደግም አሁኑኑ አቁም። አለዚያ ግን እንደኔ ከረፈደ በሃላ የሰራኸው ይገባሀል ያኔ ምንም ብታደርግ ምንም ትርጉም የለውም።

"እውነት ውስጥ ሆኖ መንቃት ውሸት ውስጥ ሆኖ ከመኖር በጣም ይበልጣል"

## ክፍል-38

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

★ሜሪ★

ታክሲ ውስጥ ከጓደኞቿ ጋር በመሄድ ላይ ሳለች አንዳች ነገር ታይ ይመስል ስልኳን ከቦርሷዋ አውጥታ መጎርጎሩን ተያያዘችው። fb ላይ ባሉት በሚያስቁት ፎቶዎች እየሳቀች አሰልቺ የፖለቲካ ወሬዎችን በጣቶቾ እያሯሯጠች በማሳለፍ ላይ ሳለች ★ናቲ ና ሜሪ★ የሚል ፅሁፍ ከተፃፈበት page ላይ አይኗ አረፈ። ሁሉም ሰው የፍቅር ታሪክ ማንበብ እንደሚወደው ሁሉ ሜሪም ለማንበብ አላመነታችም ጣቶቿ የፖለቲካው ፅሁፍ ላይ የነበራቸውን ፍጥነት ቀነስ አድርገው አይኖቿን ለአደን እንደወጣ ንስር ከፅሁፉ ላይ ተክላ የመጀመሪያውን ክፍል ማንበቧን ቀጠለች።

የመጀመሪያዋን ክፍል መቅኔ እንዳለው የበግ ቅልጥም ምጥጥ አድርጋ ለመጨረስ ደቂቃም አልፈጀባትም ነበረ ። ካነበበችው የፍቅር ታሪክ አንድ መስመር እንኳ የማታውቀው ነገር ማግኘት ቢያቅታት የኔ እና የናቲ ታሪክ አይደለም ብላ እራሷን ለማሳመን ከመፈለጓ የተነሳ ክፍል- ሁለትን ለማንበብ ትጣደፍ ጀመረ ነገር ግን ሊሳካላት አልቻለም ሙሉ ለሙሉ የራሷ ታሪክ ሆኖ አገኘችው።

ጅብ ጥላውን የጣለባት ይመስል ድንዝዝ ብላ የምታነበውን እንኳ ከጎኗ ለተቀመጡት ጓደኞቿ ማብራራት ተሳናት። ለማውራት ብትታገልም ምላሷ እንደፈለገው እንጂ እንደፈለገችው ሊሆንላት ባለመቻሉ ሳታስበው " ወራጅ ወራጅ " አለች በደመ ነብስ።

※ ሜሪ ገና አልደረስንም እኮ ምን ሆነሻል?

※ ናቲ .....ና...ቲ

※ ናቲ ምን ሆነ?

ረዳቱ በሩን ገርበብ ሲያደርገው ልምምድ ላይ እንዳለ ወታደር ዘላ ወረደች አንዷም ጓደኛዋ ተከትላት ወረደች። እራሷን ልታረጋጋ ከምክረች በሃላ ያየችውን አስረድታት አብረው ያነቡ ጀመሩ። እንኳን የራሷ የፍቅር ታሪክ ሆኖ አይደለም ማንም ሲያነበው ምስል ከሚከስተው ፅሁፍ ጋር ፍጥጫቸውን ቀጠሉ። ሜሪ እያነበበች እያንዳንዷ ቦታ እያንዳንዷ ሁኔታ ላይ የነበራትን ተሳትፎ ስታስበው ናቲ አይኗ ስር እንደ ምንጭ ውሃ ኩልል ብሎ ይታያት ጀመረ። ያሳለፋትን መለስ ብላ ስትቃኘው ምን ያህል ጣፋጭ እና አስደሳች እንደነበር በአይነህሊናዋ ተቀርፆ ከቀረው ምስል በተጨማሪም ከእጅ ስልኳ ላይ ሰፍሮ የምታነበው ፅሁፍ ምስክር ቢሆንባት ስለፅሁፉ

ልትጠይቀው ከወራት በላይ ከስልኳ ከተፃፉ የቆዩትን የስልክ ቁጥሮች ትደበድባቸው ጀመር።

ናቲ የሜሪን ስልክ ሲመለከት እንደ ህፃን ልጅ ደስታውን መቆጣጠር ፍፁም አቃተው። ከነበረበት የስቃይ አለም ልታወጣው የመጣች መለአክ መስላ ትታየው ጀመር። እራሰሱን ለመቅጣት ያንን ከባድ ውሳኔ ቢወስን እንኳ አንዲት ቀን ስለ እሷ ሳያስብ የዋለበት ቀን ኖሮ አያውቅም ነበር። ይቅርታህን ተቀብዬሀለው የሚል ቃል ለመስማት ጓጉቶ ሙሉ የስልክ ቁጥሯ እንኳ በውሉ ሳይገባ ቀርጨም አድርጎ አነሳው።

☎ ሜሪ ለ ናቲ

※ ሄ..ሎ ሜሪዬ (ድምፁ እየተቆራረጠ)

※ ወዬ ናቲዬ ሰላም ነው

※ አለን እ/ር ይመስገን

※ ናቲ fb የሆነ page ላይ የፍቅር ታሪክ አንብቤ ሙሉ ለሙሉ የኔ እና ያንተ ታሪክ ነው የምታውቀው ነገር አለ?

※ አዎ ጓደኛዬ ነው የሚፅፈው ምነው ደበረሽ እንዴ?

※  አይ ገርሞኝ ነው!

ናቲ ትንሽ እንኳ የመታረቅ አዝማሚያ ብታሳየው እሾሁን እንዳንዠረገገ ጨጎጊት መልሶ ሊጣበቅባት ቢዳዳውም ከ እሷ አፍ አንድም የመታረቅ አንድም የጥላቻ ንግግር ሳይወጣ ጥንት እንደሚተዋወቁ ጓደኛሞች ያነሷትን ሀሳብ ጨርሰው ተሰነባብተው ስልኩ ተዘጋ። ናቲ ስልኩ ሲደወል ከነበረው ደስታ ቀጥታ ወደነበረበት አርምም መመለስ ግድ ሆነበት ጭራሽ ደምፃን መስማቱ ከበፊቱ የባሰ ስቃይ ውስጥ ከተተው።

#ከ_3_ቀን_በሃላ

ሜሪ ከጓደኞቿ ጋር ለመዝናናት ወጥታ አንድ ብላ የጀመረችው የመጠጥ ጉዞዋ ባልተለመደ እና ባላሰበችው መልኩ በዝቶ አቅሏን አስቷታል። እሽክርክሮሽ በመጫወት ላይ እንዳለ ልጅ ለመራመድ ስትሞክር ከወዲያ ወዲህ ያንገዳግዳት ተያይዟል። በዚህ ሁሉ አዙሪት መሀል ናቲ ባነበበችው ፅሁፍ ላይ ተሳፍሮ ከህሊናዋ መሀደር የፍጥኝ እየጋለባት የስካሯን ጡዘት ያከረው ተያይዛል።

ስልኳን ከቦርሳዋ መዥረጥ አድርጋ ያለ አንዳች ማመንታት "እንገናኝ

ልትለው" ትደውል ጀመር። ሶስት ጊዜ ስልኩ ቢጠራም ባለተለመደ

መልኩ ናቲ ጧ ብሎ በመተኛቱ ሳቢያ ሲናፍቀው የነበረውን የሜሪን ስልክ ሳያነሳው ቀረ። ስለልኩን አላነሳ ቢላት ስካሩ ተጨማሪ ጉልበት ሆኗት Txt ትፅፍለት ጀመር።

ናቲዬ ናፍቀኸኛል ነገ ካላገኘሁህ አጉል ነገር ስለማርግ መጥተህ አግኘኝ!!

የሚል ማስጠንቀቂያ አዘል txt ልካለት ወደ ቤቷ ገብታ ለጥ አለች።

**#ጠዋት**

ከእንቅልፉ ነቅቶ እንደለመደው ከስልኩ ሊጣበቅ ስልኩን ሲያነሳ ሚስኮሉን ተመልክቶ ይደውልላት ጀመር።

※ ሄሎ ናቲዬ በጣም ይቅርታ ማታ ሰክሬ ሳላውቅ በስህተት ነው የደወልኩት!

ምን እንምታወራ እራሱ ግልፅ ሊሆንለት አልቻለም ሁሉም የሚያስበው ነገር ወጣ ገባ እያለ የህልም እንጀራ ሆነበት። ከዚያም ቀጥላ ልቡን ፀሀይ እንዳየው በረዶ ልታቀልጠው አስባ ስላሰበችው

መጥፎ ነገር ታወራለት ጀመረ። ናቲ ሰይጣን የያዘው ይመስል

ሊያኳራ ምንም አልቀረውም። ምንም ክፉ ነገር እንደዳታረግ ይማፀናት ተያያዘ።

የባሏን ምስ የምታውቀው ሜሪ በንግግሯ አሽመድምዳ ዛሬውኑ ልታገኘው መፈለጓን ገለፀችለት። ናቲም ሳያቅማማ እሷን ለማግኘት ይጣደፍ ጀመረ። ምንም እንኳን ይቅርታውን ተቀብላው አብራው ለመሆን በዋሻት ውሸት ምክንያት ፍላጎቱ እንደሌላት ስለነገረችው ቢከፋውም ሊገናኙ በመሆኑ ግን ትልቅ ደስታ እንደተሰማው በደስታ የተወጠረ ፊቱ ምስክር ነው።

☎ ናቲ ለ ሜሪ

※ ሄሎ ሜሪ

※ ወዬ ናቲ

※ ደርሻለሁ....

.

.

ይቀጥላል

# ክፍል-39

✍ ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ)

☎ ናቲ ለ ሜሪ

※ ሄሎ ሜሪ

※ ወዬ ናቲ

※ ደርሻለሁ....

ናቲ ሜሪ ጋር ከመምጣቱ በፊት እንደ ድሮው ባል እና ሚስት የመሆናቸው ጉዳይ ማክተሙን ስላወጋችው ቢቻለው በሳቅ በጫዋታ እያዋዛ በቅጡ ያልተቋጨ ፍቅራቸውን እንደ አዲስ መንገዱን ሊያቀና አልያ እሱ አልሆንልህ ቢለው ጥቂት ጊዜን አብሯት ሊያሳልፍ ስለሆነ አመጣጡ በሀሳቡ እሷን ወደ ድሮው ፍቅሯ ለመመለስ የሚጠቀምባቸውን ቃላት በመፈለግ ተጠምዶ ሳለ ሜሪ ከ ማዶ እሱ ወደተቀመጠበት ቦታ እያቀናች "ናቲ ...ናቲ" እያለች ትጠራው ጀመር።

ናቲ እሷን ለማሳመን የመራረጣቸውን ቃላት ዶሮ እንዳየው ስንዴ በትኖ ስሙ ወደ ሚጠራበት ቦታ በአይኑ ያማትር ጀመረ። ፍፁም ያልጠበቀውን አይነት አለባበስ ለብሳ ቢመለከታት ግርምትን ፈጠረበት። ይህን አይነት አለባበስ በምትልክለት ፎቶች ላይ ካልሆነ በቀር በፍፁም በአካል ተመልክቶባት ስለማያውቅ ምን ልታደርግ ፈልጋ ይሆን? እያለ እንደ እንጨት የተወደሩ እግሮቹን እያፍታታ አጠገቧ ደረሰ።

እቅፍ አድርጎ ከንፈሯን ለመሳም ቢዳዳም አለባበሷ ይህን መንገድ ላይ ለማድረግ የሚጋብዝ ሆኖ ስላላገኘው እቅፍ አድርጎ አንገቷ ስር በስሱ ሳም አደረጋት።

※ የኔ ጣፋጭ እንዴት ነሽልኝ

※ አለሁልህ ናቲዬ አንተ ደህና ነህ አአ..

※ አለሁልሽ ያንቺ ናፍቆት አናቴ ላይ ወጥቶ አረንጓዴ ሰራብኝ እንጂ እኔማ ምናባቴ እሆናለሁ

※ እኔም ናፍቀኸኛል ግን አሁን የምወስድህ ቦታ አለ።

ሳልጠይቅህ ግን ከኔ ጋር መመለስ ትፈልጋለህ አይደል??

※ ምን ጥያቄ አለው ... እንዴት እንደናፈቅሽኝ እኔ እና ፈጣሪ ነን የምናውቀው

※ እንደዛ ከሆነ መልካም እንሂድ በቃ እሺ...

ብላው ወደ ሚሳፈሩበት ታክሲ ይዛው አመራች። ናቲ ሁሉም ነገር እንቆቅልሽ ቢሆንበትም እንኳ ጥቂት ነገር ግን ከአለባበሷ ለመረዳት ሳይችል አልቀረም ነገር ግን የሰጠችውን የመታረቅ ተስፋ እንዳያዳፍንበት በመስጋት የት ነው የምንሄደው ብሎ ሊያስጨንቃት ስላልፈለገ ለግዜው እሱን ገታ አድርጎ የባጥ የቆጡን እያወጉ የመኪና ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

ከ 40 ደቂቃ የመኪና ጉዞ በሃላ ሜሪ ካሰበችበት ቦታ ስትደርስ ለረዳቱ ስተነግረው እንደ አበባየሁሽ ከበሮ መኪናዋን ይደልቃት ተያያዘ ሀሳቡን የተረዳው ሹፌርም የመኪናውን መዘወሪያ አዙሮ ጥግ ላይ መኪናዋናን አቆማት። ናቲ ከመኪናዋ እንደ ፌንጣ ፈንጠር ብሎ ወርዶ የት ይዛው ልትሄድ እንደሆነ ለመገመት እንደ ጉጉት አይኑን 360° ይዘውረው ጀመር። የሚያየው ሰፊ በሳር የተሸፈነ መሬት በዙሪያው ድንበራቸውን በካብ ድንጋይ ካሰመሩት ትንንሽ የቆርቆሮ ቤቶች ውጪ አንዳች የመጡበትን ምክንያት ሊያሳበቅ የሚቻለው ነገር ፈልጎ አጣ።

ሜሪ ከመኪናው ስትወርድ በለበሰችው እረጅም ቀሚስ ላይ ከላይ ጣል ያደረገችው ነጠላ ቢወርድባት ጊዜ ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ አጣፍታ ካስተካከለች በሃላ ወደ መንደሮቹ ወስጥ መጓዟን ቀጠለች። ናቲም እንደተፈረደበት ወንጀለኛ በዝምታ ወደምትመራው መንገድ እያወጋት ጉዞውን ቀጠለ።

መንገዱን እያሳበረች እየመራችው እረጅሙን የእግር መንገድ ከተጓዙ በሃላ ከ አንዲት አነስ ካለች የገጠር ቤተ ክርስትያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ይዛው ወደ ውስጥ ዘለቀች።

ከአውደምህረቱ ፊት ለፊት ከሩቁ ቆመው ከተሳለሙ በሃላ ራቅ ብለው በዛፎች ተከበው ከተቀመጡት የድንጋይ መቀመጫዎች ላይ ሄደው ተቀመጡ። ጥቂት በዝምታ ከተቀመጡ በሃላ የናቲን ግራ መጋባት ተመልክታ ለምን እንዳመጣችው ትነግረው ጀመረ።

※ አሁን እያንዳንዷን ጥፋትህን ሳትዋሽ ነግረኸኝ ለሁሉም በደልህ ከልቤ ይቅር ልልህ ዝግጁ ነኝ። አንተንም በአፌ ስቼ ለተናገርኩህ ክፉ ነገር በሙሉ ይቅርታ አድርግልኝ።

ናቲ የሜሪ ነገር ፍፁም ከአይምሮው በላይ ሆነበት አንዳንድ ሰው ጥቂት በድለኸው እንኳን ይቅር ሊልህ ቀርቶ አንተን ለመጣል ደካማ

ጎንህን ፍለጋ እታች እላይ ይዋልላል። አንዳንድ ሰው በደልህን

እረስቶ መልካም መንገድን ይመራሀል አይ ሰው ሰው ሁሉ እንደሜሪ ንፁህ ልብ ቢኖረው.......

ሙሉ ሰውነቱ በሀሴት ተምላ አይቶት የማያውቀው ደስታ ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ውርር ሲያደርገው ተሰማው። ሲመኘው የነበረውን እውነተኛ ከልቧ የሆነ ይቅርታዋን የማግኘት ህልሙ ዛሬ እንደተሳካለት በፍፁም ማመን አቃተው።

እንባ እየተናነቀው ያደረገውን ሁሉ አንዳች ሳይደብቅ አስረዳት እጆቿን በእጆቹ ይዞ እየሳማቸው ከልቧ ይቅር ትለው ዘንድ ከልቡ ጠየቃት። እሷም በሚያሳሱ አይኖቿ አይን አይኑን እየተመለከተች ይቅርታ እንዳደረገችለት በፍፁም ያለፈ ታሪካቸውም ካሁን በሃላ እንደማይረብሻቸው ገለፀችለት።

"አንዳንድ ሰዎች ቀዳዳህን ሊያሳዩህ በክፍተትህ በኩል ወርውረው ይፈነክቱሀል። እንዴት መልሰህ ወርውረህ እንደምትጎዳቸው ማስበህን ትተህ ቀዳዳህን በተወረወረብህ ድንጋይ ለመድፈን መምከሩ መልካም ነው በባይ ነኝ። ይህን ሁሉ ጊዜ የተወረወረብኝ ድንጋይ ደካማ ጎኔን በደንብ አሳይቶኛል። አሁን የራስህን ድንጋይ ተጠቅመህ ሳይሆን የራሴን ተራራ የሚንድ ድማሚት ሰጥቼህ እንኳን ልትንደው

ቀርቶ ትንሽ ልታንቀጠቅጠው በፍፁም የማይቻልህን ፍቅር ገንብተን

የጨረስንበት ቀን ነው ..." እያለ በህሊናው በሚያየው በሚሰማው ነገር በሙሉ በደስታ ሰከረ።

ከዚህ በሃላ ታማኝ ባሏ እንደሚሆንላት ምሎ ነገራት እሷም ለተናገረችው ክፉ ቃላት በሙሉ ይቅርታ ከጠየቀችው በሃላ ካሁን በሃላ የሰው ወሬ ፍፁም እንደማትሰማ የምትደብቀው ነገር ፍፁም እንደማይኖር እሱም እንደድሮዋቸው ፍፁም ግልፅ እንደሚሆንላት ተማምለው እንደድሮዋቸው ያለ አንዳች ጭቅጭቅ በሚያስቀና ፍቅር መኖር ከጀመሩ ዛሬ 23ኛ ቀናቸው ላይ ደርሰዋል። ዛሬ ጠዋት ናቲ ሜሪን ሊያገኛት መሄዱን እና አብረው መሆናቸውን ነግሮኛል....

እኔ በበኩሌ መልካም አዳር ተመኘሁላችሁ!!

.

.

በተረፈ የሰው ልጅ መጨረሻው ሲያምር ነው እና ደስ የሚለው እስቲ እነዚህን ጥንዶች መጨረሻችሁን ያሳምርላችሁ ከአይን ያወጣችሁ መልካም የፍቅር ዘመን ይሁንላችሁ በሉልኝ .....❤❤❤

# ተፈፀመ

ሌሎች ፅሁፎቼን በ Telegram channel ላይ በየጊዜው
ስለምለቅ እንዳያመልጥዎ ቻናሌን ተቀላቅለው ይከታተሉኝ!!

## Telegram channel

★ @yefikir_tireka

**ቃልአብ ነጋሲ (ቃኮ ★ፍ) --ነኝ አመሰግናለሁ ስለተከታተላችሁኝ**